# ኢትዮ ቶርናመንት

Dec 2012

ታህሣሥ 2005

## Ethio Tournament



## ይድነቃቸው በካድሬ የሚተካ አይደለም !

### እንጋፋው የስፖርት ጋዜጠኛ
### አቶ ፍቅሩ ኪዳኔ







" የምንጫወተው ለውጤት
እንጂ ለተሳትፎ አይደለም "
አዳነ ግርማ

" ልዩነቶች ቢኖሩም ለፌዴሬሽኑ ህልውና
ሲባል በውይይት ይፈታሉ!! "
ተካበ ዘውዴ

" በአካልም በሞራልም
ጥሩ ሁኔታ ላይ ነን "
ጀማል ጣሰው

# SHININGFRESH
carpet :: tile & grout :: upholstery

0412 646 621

## Our Services

- Residential Carpet Cleaning
- Commercial Carpet Cleaning
- Tile and Grout Cleaning
- Upholstery Cleaning
- Pet Odor Control and Removal
- Stain Removal
- Natural Stone, Limestone...



Carpet



Tile & Grout



Upholstery

We provide all our customers in Melbourne (especially in Bundoora or Northen Western and Eastern area) by professionally quality to clean your carpet, tile & grout and upholstery. Our team have been trained by Jena Dyco which is approved by Australian government. Every single service will be completed step by step. There is many things you do not know about your carpet but our experience will help you to understand how to deal with your carpet problems.

## Hot Promotion

### Cleaning Specials

Deluxe Carpet Cleaning
Only $35 per room
*standard room 10sqm.

Carpet and Upholstery Cleaning
Tile and Grout Cleaning
For $5.50 p/sqm*

**Address** : 8 Riley Court
Burnside/ Caroline Springs
VIC 3023

Email : admin@shiningfresh.com.au ---www.shiningfresh.com.au

# AFRICAN TOWN
አፍሪካን ታውን
CAFE BAR & RESTAURANT

**Gezahagn Yedete**
Manager
Mobile : **0401 331 652**

161 - 163 Nicholson Street
Footscray, Victoria 3011

Phone : (03) 9689 1599
Phone : (03) 9689 9660
Fax : (03) 9689 9490
gezahagn@africantown.com.au
www.africantown.com.au

## AFRICAN TOWN RESTAURANT

Doro Wat $10
*(Chicken)*
Lega Tibes $10
*(Roasted Lamb)*
Kitfo $10
*(mince meat seasonal with herbed butter and hot red pepper)*
Gored gored $10
*(Chunks of raw, fresh beef seasoned with special butter mitmita and pepper)*
Zil Zil Tibes $10
*(Grilled meat)*
Key Wot $10
*(Beef stew)*
Minchet Abish $10
*(minced beef stew)*
Kurt $10
*(Raw meat)*
Vegetarian $10
*(Lentils, Yellow split peas, beans, chick peas, beetroot, potato)*

**Vegetarian & non-vegetarian combination**

16ኛው

# ኢትዮ - ቶርናመንት

## ሜልበርን ዲሴምበር 2012




## አንድነታችን

መልካም ዕድል በ29ኛው አፍሪካ ዋንጫ ለሚወዳደረው ብሄራዊ ቡድናችን!!
መልካም የዕረፍትና የመዝናኛ ግዜ በሜልበርን 16ኛው ዓመት
ቶርናመንት ለሚታደመው ወገናችን!!

በቪክቶሪያ የኢትዮጵያዊያን ማሕበረሰብ ጽ/ቤት አስተባባሪነት
ታትማ የምትወጣ አመታዊ የስፖርት መጽሄት

December 2012
Melbourne



# ኢትዮ-ቶርናመንት

በሜልበርን የኢትዮጵያዊያንን አመታዊ የስፖርት ውድድር ምክንያት በማድረግ በቪክቶሪያ የኢትዮጵያዊያን ኮሚኒቲ ጽ/ቤት አስተባባሪነት ታትማ የምት ወጣ ዓመታዊ መጽሄት።

**አዘጋጆች**

ሳምሶን አስፋው
መስፍን ማሞ
ዓብይ አፈወርቅ
Email: quatero@gmail.com

**ማስታወሻ**

በዚህ መጽሄት የወጣን ማንኛውንም ዘገባም ሆነ ቃለ መጠይቅ በሌላ የዜና አውታር ሊያወጣ ወይም በሌላ መልክ ሊጠቀም የሚሻ በቅድሚያ አዘጋጆቹን ማማከር ይገባዋል።

የኢትዮጵያዊያን አመታዊ የስፖርት ውድድር ከታህሣሥ 26 - 30 ሜልበርን

## ኢትዮ- ቶርናመንት በውስጥ ገጾቿ

ገጽ



"...በስፖርት አመራር ውስጥ በአፍሪካና በዓለም አቀፍ ደረጃ አቶ ይድነቃቸውን የተካ ኢትዮጵይያዊ የለም።ይድነቃቸው በካድሬ የሚተካ አይደለም እኔ በበኩሌ በመጀመሪያ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ባልደረባ...." **አቶ ፍቅሩ ኪዳኔ** 6



"...በመጀመሪያ ልገልጽ የምሻው የኛ ፌዴሬሽንም በጥንካሬ ጀምሮ በጥንካሬ የኖረና እዚህ የደረሰ አይደለም። ስንጀምር ብዙ ብዙ ችግሮች ገጥመውናል። ጓደኛሞች ከሃገር ሃገር .እየሄዱ የጀመሩት እንቅስቃሴ ነው ዛሬ..." **ተካበ ዘውዴ** 10



"...አንድ የማረጋግጥልህ ነገር ቢኖር ደቡብ አፍሪካ የምንሄደው ለተሳትፎ ሳይሆን ለውጤት መሆኑን ነው። ሁላችንም አንድ አይነት መንፈስ ነው ያለን።... " 11



"...የአፍሪካ እግር ኳስ ፌዴሬሽንን አባላት በማስተባበር አፍሪካ በዓለም እግር ኳስ ማጣሪያ ለሚኖራት ምደባ /ኮታ/ ይድነቃቸው ባደረጉት ትግል የወቅቱ ፓን አፍሪካኒስት ..."**ይድነቃቸው ተሰማ ሲታወሱ** 13



"...ሲያሻው "ወጣት ደምሴ" ሲለው ደግሞ ""ተማሪ ደምሴ "እያለ ነበር ለአድማጮቹ የሚያስተዋውቀው። ያም ሆኖ ግን እንደዚያ የሰከኑ ሪፖርቶች የሚያስተላልፍለት ወጣት የ13 አመት ..." **ደምሴ ዳምጤ ማነው?** 14



"...ከሁለቱ አንዱ ወሎ ነበር፡፤ እዚያም የክፍለ ሃገሩ የስፖርት ኮሚሽን ተጠሪ ሆኜ የተመደብኩት እኔ ነበርኩ፡፤ ይህ እንግዲህ ከፍተኛ የሆነ የስራ ሃላፊነት ነው። ከዚያ በፊት ከቦታ ቦታ እየዞርን በግሩፕ የምንሰራው" **አቶ ተስፋ** 15



"...ልክ ነህ ብዙ አስቂኝ ነገር አለ። በራሴ ላይ የደረሰውን ላስቀድም፡፤ገና ቦክስ ጀምረን ብዙም ሳልጫወት ብሄራዊ ቡድን ተመረጥኩ።እናም ለሎሳንጀለስ ኦሎምፒክ ልምድ ያግኙ ተባልንና... "**ሳህሉ መኩሪያ** 19



" ...የጊዮርጊሱ ተጫዋች ሙሉጌታ ከበደ ከጊዮርጊስ በፊት ለወሎ ምርጥ እና ለወሎ ፔፕሲ ክለብ ነበር የሚጫወተው፡፡ በጉብዝናው ወደ ጊዮርጊስ ተዛውሮ መጫወት እንደ ጀመረ በጨዋታ መሀል ...." **ለፈገግታ ከኳስ ሜዳ** 24



"...አንድ መቶ አንድ ደቂቃዎችን ባስቆጠረው ጨዋታ የታዩት ድራማዊ ክስተቶች ብዙ ናቸው፡፡ ከነዚህ ክስተቶች መካከል ቀዳሚው ኳስ ወዳዱ ኢትዮጵያዊ የዘጠና ደቂቃውን ጨዋታ ለማየት ከቅዳሜ ሌሊት ጀምሮ"**ልዩ ዘገባ** 26




"...የሚገርምህ ገና ነሽ እደጊ ተብዬ ከተመለስኩበት ከኤሌትሪክ ጋር ተጫወትንና ሁለቴም 2 ለ 1 አሸነፍናቸው ..."**ለማ ክብረት** 31

**"ሌሎችም ዝግጅቶች**

- መልካም ልደት ................................22
- ቅኝት በብሄራዊ ቡድናችን ዙሪያ ....32
- የሃዘን መግለጫ ...............................35

መልካም ንባብና የዕረፍት ግዜ ይሁንልዎ!



# ይድረስ ለአንባቢያን

ተላከ
ከአዘጋጆች

እንደምን ከርማችሁልናል ውድ የኢትዮ - ቶርናመንት አንባቢያን ? እኛ በሰላም ስንጽፍ ከረምን! እናንተም በጥሞና ስታነቡ እንደምትሰነብቱ ተስፋችንም ምኞታችንም ነው።

ውድአንባቢያን፡- ይህችን መጽሄት ለማዘጋጀት ያነሳሳን፡- ኢትዮጵያዊነት የሚያንገሸግሸው፤ አንድነታችን የሚያስፈራው፤ አብሮነታችን የሚያቃዠው አጥፊ ሁሉ! ዘንድሮስ ለየላቸው፤ አሁንስ አቃታቸው፤ ፈዘዙ፤ ደነዘዙ....በሚል የሞራል መሰላል ላይ መንጠላጠሉን በሰማን ግዜ ነዶን ነው።እናም ዘንድሮም ንቁ ነን አልፈዘዝንም! ሳተና ነን አልደነዘዝንም፤ አሁንም ተችሎናል አላቃተንም፤ የሚል መልዕክት ለማስተላለፍ ተነሳን። ኢትዮ ቶርናሜንትን ፍሪዳ ጥለን አመታዊ የስፖርት ውድድሩን አውዳ አመት ልናስመስለው ወደድን። አንድነታችን ላይ ያፈጠጠ ቡዳ አይኑ ይፍሰስ ብለን ሽር ጉድ አልን።

እናም ሃሳባችንን ዳር ለማድረስ የቻልነውን ስናደርግ ሰነበትን። አዘጋጆቹ ሶስት ነን። ታዲያ ሶስታችንም ወዳጅነታችን ተብዕር እንጂ ተኳስ አይደለምና የስፖርት መጽሄት ማዘጋጀት አይቻለን ይሆን ብለን መስጋታችን አልቀረም። ግና የቶርናመንቱ አብይ አላማ በኳስ ውስጥ ኢትዮጵያዊነትን ለማየት እንደመሆኑ እኛም በብእር ጫፍ ኳስን መጠቆም አይከብደንም ብለን ገባንበት።ተሳክቶልን ከሆነ ማለፊያ። ለከርሞም እንደግማለን።

ውድአንባቢያን ኢትዮ - ቶርናመንት በርካታ ዝግጅቶችን አካታለች። እውቁና ተወዳጁን አለም አቀፍ የስፖርት ሰው አቶ ፍቅሩ ኪዳኔን ከፈረንሳይ በክብር እንግድነት አስተናግዳለች። የብሄራዊ ቡድናችን የቀድሞው ግብ ጠባቂ ተካበ ዘውዴንም ከአሜሪካ በእንግድነት ጋብዛለች፡፡ ምነው ደጅ ደጁን እንዳንባልም ከሜልበርን ደግሞ የቀድሞው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቅርጫት ኳስ ፌዴሬሽን ዋና ጸሃፊና የአውስትራሊያ ስፖርት ፌዴሬሽን ፕሬዘዳንት የሆነውን አቶ ተስፋ የሸዋሉልን አነጋግረናል።

ወደ ኢትዮጵያም ተጉዘናል። የብሄራዊ እግር ኳስ ቡድናችን ተጨዋቾች አዳነ ግርማንና ጀማል ጣሰውን ጋብዘን ከወር በኋላ ደቡብ አፍሪካ ላይ ስለሚደረገው 29ኛው የአፍሪካ ዋንጫ ውድድር እያደረጉት ስላለው ዝግጅት አንስተንባቸዋል።የሞራሉንም የብቃቱንም ጥያቄ ...ሰንዝረናል።

ሱዳንን አሸንፈን ለአፍሪካ ዋንጫ ያለፍንበትን ጨዋታ ከዋዜማው ጀምሮ የነበረውን የስፖርት አፍቃሪ የተስፋና በኋላም የደስታ ድባብ በስፋት የቃኘው የአዲስ አበባው ተባባሪያችን የላከውን ልዩ ዘገባም ይዘናል። ሳህሉ መኩሪያና ለማ ክብረትም በእንግድነት ቀርበዋል።

በህይወት የሌሉ የስፖርት ቤተሰቡን ባለውለቶችም አልዘነጋንም። በቅርቡ ያለፈው ተወዳጁ የስፖርት ጋዜጠኛ ደምሴ ዳምጤና ታላቁ የስፖርት ሰው ይድነቃቸው ተሰማ ተዘክረዋል። ይህ ብቻ አይደለም። የዕረፍት ግዜ መሆኑን ሳንረሳ ከኳስ ሜዳ የተሰበሰቡ በርካታ አዝናኝና አስቂኝ የስፖርተኞችን ገጠመኞች፤ ይህን ያውቁ ኖሯል ቅንብሮች፤ ሰንቀናል።

ውድ አንባቢያን ሆይ! እንግዲህ የወለደውን ሲስሙለት .... ይባላልና ዝግጅታችን ቢያስደስታችሁ ደስ ይለናል። ቅሬታም ካለ የከርሞ ሰው ይበለን እንጂ እንክሳለን፡፤ በኛ በኩል እዚህ ጋ ጨርሰን ወጥተናል ! እናተ ደግሞ እንሆ ግቡና ተጋበዙ፡-

**መልካም ንባብና የእረፍት ግዜ ይሁንልዎ!!!**

**አዘጋጆቹ** ሳምሶን አስፋው፤ መስፍን ማሞና አብይ አፈወርቅ

ሀገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ሃገራቸውን ብቻ ሳይሆን አህጉራቸውንም ያኮሩና ያስጠሩ ጥቂት የማይባሉ ድንቅ ልጆች አፍርታለች። አቶ ፍቅሩ ኪዳኔም አንዱ ናቸው። ከጉለሌና ፒያሳ ተነስተው በአለም አቀፍ ደረጃ የሚደረጉ ታላላቅ የስፖርት እንቅስቃሴዎችን ለመምራት ለማስተባበርና ለማማከር የበቁ ኢትዮጵያዊ ናቸው።አቶ ፍቅሩ የአለማችን የስፖርት እንቅስቃሴ በበላይነት ከሚመራበት ከፍተኛ የሃላፊነት ማማ ላይ ለመውጣት ከበቁ በጣት ከሚቆጠሩ አፍሪካዊያን አንዱ ናቸው።



አንጋፋው የስፖርት ጋዜጠኛ
አቶ ፍቅሩ ኪዳኔ

# “ይድነቃቸው በካድሬ የሚተካ አይደለም !”

ኢትዮ-ቶርናመንት መጽሄት እኝህን ታላቅ ሰው በእንግድነት ለማስተናገድ በመብቃቷ ኩራትና ክብር ይሰማታል፡፡ ተጽፎ ከማያልቀው፤ ተነግሮ ከማይዘለቀው ልምዳቸው ጥቂቱን ያቋድሱን ዘንድ ያቀረብንላቸውን ግብዣ የተቀበሉት በደስታ ነው። ለአቶ ፍቅሩ ኪዳኔ ልናነሳ የምንሻቸው ጥያቄዎች ደግሞ አንድ መጽሄት ቀርቶ መጽሀፍም የሚበቃቸው አይደሉም። ይሁንና ወቅታዊነታቸውና ቁምነገራቸው ሚዛን ይደፋል ባልናቸው ጉዳዮች ላይ በርካታ ጥያቄዎችን አንስተንላቸዋል።እንሆ፡-

# ይድነቃቸው በካድሬ .....

**ጥያቄ: በቅድሚያ ግብዣችንን በመቀበልዎ በአንባቢያን ስም ከፍ ያለ ምስጋና ልናቀርብ እንወዳለን። በመቀጠልም በአውስትራሊያ በሚደረገው የኢትዮጲያዊያን ስፖርት ውድድር ተሳታፊ ለሆኑ ፣ በተለይም ታሪክዎንና ልምዶን በተመለከተ በቂ መረጃ ላላገኙ ወጣቶች ራስዎን ቢያስተዋውቁልን?**

**መልስ፡-**ፍቅሩ ኪዳኔ አንድ ተራ ኢትዮጵያዊ ነው የእግዚአብሔር ፍቃዱ ሆኖ በሁለት እግሩ ቆሞ ሃገሩንና አህጉሩን ለማገልገል በቅቷል።የአንድ ልጅ አባት የሁለት ልጆች አያት ነው። ተወልዶ ያደገው የተማረው የኖረው አዲስ አበባ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ነው። የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ የስፖርት ጋዜጠኛ! ባገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ከዛሬ 53 ዓመት በፊት በሬዲዮ በቀጥታ የእግር ኳስ ጨዋታ (ኢትዮጵያ V ሱዳን) ከስታዲዮም ያስተላለፈ፤ የኦሎምፒክ ጨዋታ የሚል መጽሀፍ ከ51 ዓመት በፊት ያሳተመ ነው።

ኢ.ኤ.አ በ1956 አውስትራሊያ ሜልበርን ኦሎምፒክ የሚካፈለውን የኢትዮጵያ አትሌቶች መታወቂያ ፎርም የሞላ አልሞትባይ ተጋዳይ ሽማግሌ ነው ። አውስትራሊያ ባለፉት 30 ዓመታት ውስጥ በስራ በመመላለስ ሲዲኒ፤ሜልበርን፤ብሪዝበን አደላይድ፣ ፐርዝ፣ካንቤራ፣ ዳርዊንን ጎብኝቻለሁ።

**ጥያቄ:** በስፖርቱ ዓለም ከፍተኛ እውቅናና ክብር አግኝተው በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች በመስራት ሃገራቸውን ካስጠሩ ኢትዮጵያውያን መካከል ቀደም ሲል ክቡር ይድነቃቸው ተሰማ ፣ ተከትሎም እርስዎ ትጠቀሳላችሁ። ለመጪው ጊዜስ እናንተን ተክቶ በተመሳሳይ ደረጃ አገሩን የሚያስጠራ ባለሞያ የማየት ተስፋ ይኖረን ይሆን? ካለን እነማን መስመር ላይ ናቸው? ከሌለንስ ችግሩ ምን ይመስሎታል..?

**መልስ፡-** በዓለም ደረጃ የታወቀው የተከበረው ለኢትዮጵያና ለአፍሪካ ከፍተኛ አገልግሎት ያበረከተው ሰፊ ዕውቀት የነበረው አቶ ይድነቀቸው ተሰማ ነው። የኢትዮጵያን ስፖርት ያቋቋመ ልዩ ልዩ ሕጎችንና መተዳደሪያ ደንቦችን በአማረኛ የተረጎመ ለአፍሪካ የታገለ ትልቅ ሰው ነው።በስፖርት አመራር ውስጥ ወሳኙ በተለይ በአፍሪካና በዓለም አቀፍ ደረጃ አቶ ይድነቃቸውን የተካ የለም።



ከግራ ወደ ቀኝ አበበ ቢቂላ ማሞ ወልዴና አቶ ይድነቃቸው ተሰማ በሚክሲኮ ኦሎምፒክ ማሞ ወልዴ በመራቶን ድል ተቀዳጅቶ

ይድነቃቸው በካድሬ የሚተካ አይደለም። እኔ በበኩሌ በመጀመሪያ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ባልደረባ ከዚያም ለብዙ ኢንተርናሽናል የፕሬስ ድርጅቶች በጋዜጠኝነት ሞያ ቀጥሎም ለኢንተርናሽናል ኦሎምፒክ ኮሚቴ በዳይሬክተርነት ደረጃ የማገልገል እድል ገጥሞኛል። እኛን ለመተካትና ለመታወቅ ቢያንስ ሁለት የውጭ ቋንቋ ማወቅ ያሻል ተተኪ ሊሆኑ የሚችሉት ሁሉ አፍሳይድ ስለሆኑ ለግዜው ግብ ሊያስገቡ አልቻሉም።

**ጥያቄ:**ከአፍሪካ ዋንጫ መስራች 3 አገራት አንዷ ኢትዮጵያ ነበረች



**ከፕሬዘዳንት ፑቲን ጋር ሞስኮ ክሪምሊን ቤተ መንግስት እ.አ 2001**

ላለፉት 31 ዓመታት ግን ወደ ውድድር ማለፍ እንኳ ሳትችል ቆይታለች። ዓይነተኛ ችግሮቻችን ምን ነበሩ ይላሉ?

**መልስ፡-**የአፍሪካ ዋንጫ መስራቾች አራት ናቸው ።ኢትዮጵያ፣ ግብጽ፣ሱዳን፣ደቡብ አፍሪካ። ደቡብ አፍሪካ ነጭና ጥቁር ተጨዋቾች ያሉበት ቡድን አላሰልፍም በማለቷ በአፓርታይድ የተነሳ ነው ከመጀመሪያው የአፍሪካ ዋንጫ የተገለለችው ። የኢትዮጵያ እግር ኳስ ችግሮች አንድ ጆኒያ ይሞላሉ። በመጀመሪያ ወጣቱ የሚጫወትበት ስፍራ የለም። የት/ቤት ስፖርት ሞቷል ለማለት ይቻላል።

በጥንት ጊዜ ቡዙዎች በየክለቡ የሚጫወቱት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተማሪዎች ነበሩ። በየሰፈሩ በጨርቅ ኳስ በመጫወት ነበር። አሁን እንዲያውም በየት/ቤቱ ክፍል ቢያንሳቸው ኳስ ሜዳው ላይ ወይም መጫወቻ ስፍራው ላይ ነው የሚገነቡት። ከአዲስ አበባና ከአንዳንድ ከተሞች ውጭ የእግርኳስ ጨዋታ የሚባል የለም። አገሪቱ አሰልጣኞች አላፈራችም። ሜዳዎች አላሰራችም። ሕዝቡ በመዋጮ ክለብ ማቋቋም ልምዱ የለውም። ከአፍሪካ ውስጥ ዘመናዊ ስታዲዮም የሌላት ኢትዮጵያ ብቻ ነች። ትልቁም ችግር የስፖርት መሪዎች ማጣት ነው ።

**ጥያቄ፡-**አሁን ስናልፍ ምን ተሰማዎት?

**መልስ፡-** ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ዋንጫ ማለፏ ሁላችንንም አስደስቶናል። እኔ አዲስ አበባ በ1968 ዓ.ም እና በ1976 ዓ.ም ኢትዮጵያ ባዘጋቸችው የአፍሪካ ዋንጫ ውድድር የአዘጋጅ ኮሚቴው ፀሃፊ ነበርኩ ። ከዚህ በቀር ወደ 25 የሚጠጋ የአፍሪካ ዋንጫ ውድድር ተከታትያለሁ። አሁንም ወደ ደቡብ አፍሪካ ለመጓዝ እያተዘጋጀሁ ነው። ለጊዜው የአፍሪካ ፉትቦል ኮንፌዴሬሽን ፕሬዘዳንት አማካሪ ነኝ። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ሲጫወት ለመጨረሻ ጊዜ ያየሁት የዛሬ 31 ዓመት ቤንጋዚ ሊቢያ ላይ ነው ።

**ጥያቄ፡-** አንዳንዶች ከ31 ዓመታት በኋላ ለአፍሪካ ዋንጫ ውድድር ያለፍነው ስለተሻሻልን ሳይሆን በዕድልም ጭምር ነው ይላሉ። ለዚህ ደግሞ የውድድሩ ዘመን ከዓለም ዋንጫ ጋር እንዳይደራረብ በሚል ጊዜውን ያልጠበቀ ጫወታ ከመካሄዱ ጀምሮ አንዳንድ አጋጣሚዎችን ያነሳሉ። እርሶስ የቡድናችንን ይዞታ ከቀደምት የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድኖች ጋር እንዴት ያነጻጽሩታል? ደቡብ አፍሪካስ ላይ ከቡድናችን ምን ይጠብቃሉ?በምድቡ ካሉት ሌሎች ቡድኖች ጋርስ እንዴት ያስተያዩታል?

**መልስ፡-**ግራም ነፈሰ ቀኝ ማጣሪያውን አልፎ ከዚያም በላይ ናይጀሪያና - ቡርኪናፋሶ ጋር ተመድበዋል። ሦስቱም ቀላል ቡድኖች አይደሉም። ሱዳንን የመሰለ ቡድን ማሸነፍ ቀላል አይደለም። መከራው የኛ ብሔራዊ ቡድን ልክ እንደሌሎቹ የልምምድ ዕድል ማጣቱ ነው።

**መልስ፤-** የሚያሳዝነው አንድም የወዳጅነት ግጥሚያ ያለማዘጋጀቱና ተጫዋቾቹም ገና እንዳልተሰባሰቡ አስልጣኞቹ ለሪፖርተር ጋዜጣ ገልጸዋል። ፌዴሬሹኑም ገንዘብ የለኝም ይላል። ባይኖረውም ከመንግስት ዕርዳታ ጠይቆ ቡድኑን የማዘጋጀት ሃላፊነት አለበት።ከየመንደሩ የተሰበሰበውን የሱሜሌ ቡድን አሸንፉ ብሎ ሼራተን ሆቴል ኮክቴል ግብዣ የሚየደርገው ፌደሬሽን ይኸው ለፍርፍርም የሚሆን የለኝም ይላል። በኛ ዘመን ከድህነት ት/ቤቶች በተማርነው ጥበብና ብልሃት ራሳችንን እንችል ነበር። ስለዚህ የኢትዮጵያ ቡድን በደቡብ አፍሪካ ጥሩ ውጤት ያመጣል ለማለት የሚያስችል ምንም አይነት መጠቆሚያ የለም ። እስከዚያ ታምር ይፈጥር እንደሆነ አላውቅም ።

**ጥያቄ፡-** ባለፉት አስርት ዓመታት ለኛ አይሳካልን እንጂ የአፍሪካ እግር ኳስ ግን ማደጉ ነው የሚታመነው።በዚህም አህጉሯን ወክለው በዓለም ዋንጫ የሚሳታፉ ቡድኖች ቁጥር መጨመሩ ብቻ ሳይሆን የሚያደርጉት ፉክክርና የሚያስመዘግቡት ውጤትም አበራታች ነው በሚል ብዙዎች ይስማማሉ።ለእድገቱ በዓይነተኝነት የሚጠቀሱ ምክንያቶች ምንድናቸው ይላሉ?

**መልስ፡-**የአፍሪካ ሃገሮች ለስፖርት ማስፋፊያ በቂ ባጀት የሌላቸው ሁሉ ቡድናቸው ለአፍሪካና ለዓለም ዋንጫ ውድድሮች ሲያልፉ ገንዘብ ከወዴት አግኝተው ለዝግጅቱ እንደሚያወጡ የሚገርም ነው ።

ስለዚህ ካሜሮን፣ ናይጀሪያ፣ ጋና፣ ቱኒዚያ፣ አልጄሪያ፣ ሞሮኮ፣ ቡድናቸውን ለዓለም ዋጫ ለማዘጋጀት መንግስቶቻቸው ዋና ስፖንሰሮች ስለሚሆኑ ውጤቱ አያስከፋም። ዋናው ምክናያት አብዛኞቹ አፍሪካዊያን ተጨዋቾች በአውሮፓ ሊግ ውስጥ ስለሚጫወቱ ጥሩ ተወዳዳሪዎች ሆነዋል። በወጣቶቹ የዓለም ሻማፒዮንም ከመሆን በላይ ውጤታቸው ባጠቃላይ ያማረነው። መከራው ግን ወጣቶቹን ተንከባክቦ በመያዝ ሕይወታቸውን ማራዘሙ ላይ ነው ።

**ጥያቄ፡-** ክቡር አቶ ይድነቃቸው ተሰማ ለሃገራችን የእግር ኳስ እድገት ከፕሮፌሽናሊዝም ይልቅ አማተሪዝም ነው የሚጠቅመው የሚል አመለካከት እንደነበራቸው ይጠቀሳል። ይሁንና ባሁኑ ወቅት ውጤት እያሳዩ ያሉት በተለይም የምዕራብ አፍሪካ አገራት ፕሮፌሽናል ተጫዋቾቻቸውን ነው እየተጠቀሙ ያሉት። ለመሆኑ የፕሮፌሽናሊዝምና አማተሪዝም ጠንካራና ደካማ ጎኖች ምንድን ናቸው? ለእኛስ አገር በዚህ ዘመን የቱን ማጥበቁ የሚበጀን ይመስሎታል?

**መልስ፡-** አቶ ይድነቃቸው ተሰማ ከፕሮፌሽናሊዝም አማተሪዝምን የሚደግፍበት ምክንያት ነበረው።

አፍሪካ ኢትዮጵያንም ጭምር በኢኮኖሚ ደካማ በነበርንበት ወቅት ፕሮፌሽናል ሊግ ማቋቋም ስለማይቻል ነበር። አሁንም ቢሆን አፍሪካ ውስጥ ደንበኛና የረቀቀ ሳይሆን ርካሽ ፕሮፌሽናሊዝም ነው ያለው።

ስለዚህ አቶ ይድነቃቸው ጭራሽ አልተሳሳተም። በዓለም ደረጃ ብንሄድ 95% አማተሪዝም 5% ፕሮፌሽናሊዝም ነው ያለው። እነርሱም የሚኖሩት በቴሌቬዥንና በንግድ ኩባኒያዎች ስፖንስርሺፕ ገንዘብ ነው።

የዓለም ሕዝብ ጤንነቱን የሚጠብቅበት የሚዝናናበት ስፖርት በየመንደሩ፣ በየቀበሌው ፣በየአውራጃው፣ ...... የሚከተለው ውድድሩ በጠቅላላው ያማተር ስፖርት ነው።

አቶ ይድነቃቸው በዛ ዘመን በነበረው ሁኔታ የሚከራከርበት ፍልስፍና እኔም እራሴ የምደግፈው ነው። በአሁኑ ዘመን መንግሥታቶች ራሳቸው ስለሚጠቀሙበት በማንኛውም የስፖርት ዓይነት ውጤት ለማግኘት እንደ ፕሮፌሽናል መዘጋጀት ያስፈልጋል።

ማለትም ከስራ በኋላ ሳይሆን ስራዬ ብሎ መሰልጠን መዘጋጀት ያሻል። ስፖርት በመላው ኢትዮጵያ ተስፋፍቶ ወጣቶች በፈለጉት መስክ የመሰለፍ ዕድል ገጥሟቸው ለማየት ነው የምንጓጓው።

ለማንኛውም አማተር ነው ፕሮፌሽናል የሚሆነው የማንችስተር፣ ባርሴሎና፣ ማድሪድ፣ ለንደን ነዋሪዎች ሁሉ በቡድኖቻቸው እንደሚደሰቱ የቡታጅራ ፣ ውልንጭቴ ፣ጎሞጎፋ፣ካራቆሬ ከተሞች ነዋሪዎች በአማተሩ ቡድኖቻቸው የማይደሰቱበት ምክንያት የለም።



አቶ ፍቅሩ ኪዳኔ እ.አ 2001 ሶልት ሌክ ሲቲ የኤስ ኤ የክረምት ውድድር በወቅቱ የተ.መ.ዋና ጸሃፊ ኮፊ አናን ጋር

**ጥያቄ፡-**በውጪው ዓለም የሚገኘው ኢትዮጵያዊ በያለበት ዓመታዊ የስፖርት ቶርናመንቶችን እያዘጋጀ ሲገናኝ ይታያል።እርሶም በተለይ በሰሜን አሜሪካው ውድድሮች ወቅት ቀርተው እንደማያውቁ ነው የምንሰማው። ጠቅለል ባለ መልኩ የዚህ ዓይነቱን ፕሮግራም ፋይዳ እንዴት ይገልጹታል? በተለያዩ አገራት የሚኖረው ኢትዮጵያዊ እግር ኳስን ከስፖርታዊ ፋይዳው ባሻገር የአገር ልጆች መገናኛ ፣ የማንነትና የባህል መዘከርያ መድረክም አድርጎ እየተገለገለበት ይገኛል።ይሁንና ባለፈው በሰሜን አሜሪካ ስፖርት ፌዴሬሽን ላይ የመከፋፈል አደጋ ደርሶ ብዙዎችን አሳዝኗል።እዚህ አውስት ራሊያም እንዲሁ ተመሳሳይ ችግር አለ። ይህን በተመለከተ ለኢትዮጵያዊው ወገንዎ ምን ይመክሩታል?

**መልስ፡-**በመጀመሪያ ዓመታዊ የስፖርት በዓል ማዘጋጀት የጀመሩት የሰሜን አሜሪካዊያኖች ናቸው። ከዚያም አውሮፓ አሁን ደግሞ አውስትራሊያ። እኔ እድሜዬ የገፋ ስለሆነ እኩዮቼን የማገኘው አሜሪካ ስለሆነ በተለይ ዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ በየዓመቱ በእግር ኳስ አማካይነት ብቅ እላለሁ።ባለፈው ዓመት ብጥብጥ ተነስቶ ባንድ ቱዣር ወጪ ዋሽንግተን ላይ የሃብታሞች ፌሽታ አዘጋጅተው ነበር።እኔ እንኳን ከሰፊው ህዝብ ጋር ዳላስ ነበርኩ ።

የኢትዮጵያን ሕዝብ በሰላም የሚያሰባስብ ስፖርቱ ነበረ። እስፖርቱንም የፖለቲካ መሳሪያ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ነው።የስፖርቱ ህብረተሰብ ጠንካራ ከሆነ ማንም አይገፈትረውም ተንኮለኞች፣ ሰላዮች፣ ደላላዎቹ የታወቁ ስለሆኑ በቆራጥነት መቋቋም ነው።ሃምበርገር ለመብላት መዋረድ አያስፈልግም።

**ጥያቄ፤** በስራዎ ምክንያት የተለየዩ አገራት መሪዎችን የማግኘትና የመወያየት ዕድል እንዳጋጠሞት ይታወቃል። በተለይ ግን "ለእግር ኳስ ስፖርት ልዩ ፍቅር ያለው ሰው ነው" በሚል ያስደመሞት ማንኛቸው ይሆኑ? እኚህ የአገር መሪ ለኳስ ያላቸውን ፍቅር ለማመላከት ይረዳ ዘንድ ከትዝታዎ ጨልፈው ከተግባራቸውና ከውይይታችሁ መሀል ቢያጫውቱን?ከቶም የኳስ ፍቅር የሌለውና ለውይይት አስቸጋሪ የሆነቦት መሪስ አላጋጠሞትም? ካጋጠሞት አስቲ ጥቂት ያውጉን?

[ወደ ገጽ 17 ይዞራል]

# ☆ ቆይታ ከተካበ ዘውዴ ጋር ☆

ልክ የዛሬ 25 ዓመት ታህሳስ ወር የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ለምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ ዋንጫ አዲስ አበባ ላይ ያደረገውን የፍጻሜ ውድድርና የተገኘውን ውጤት ለሚያስታውሱ ጎልማሶች ተካበ ዘውዴን ማስተዋወቅ የሚያስፈልግ ባይሆንም፤ በግዜው ሕጻናት ለነበሩ አልያም ላልተወለዱ ለዛሬ ወጣቶች ተካበ ዘውዴ ሁለት ፍጹም ቅጣት ምት አድኖ ቡድናችንን ለዋንጫ ያበቃ ባለውለታ ተጫዋች እንደሆነ ማስተዋወቅ ተገቢ ይመስለናል። ዛሬ ከተካበ ዘውዴ ጋር ቆይታ ማድረግ የፈለግነው ግን በዚህ ምክንያት አይደለም። ከተካበ ጋር በምናደርገው ቆይታ የምናነሳው ጉዳይ በአሁኑ ወቅት በሚገኝበት በሰሜን አሜሪካ የስፖርት ፌዴሬሽን ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ኃላፊነቱ ዙሪያ ነው።እግረ መንገዳችንንም በመጪው ወር ደቡብ አፍሪካ ላይ በ29ኛው አፍሪካ ዋንጫ ስለሚወዳደረው ቡድናችን አንዳንድ ጥያቄ አንስተንለታል። መልካም ቆይታ!

ጤና ይስጥልኝ! ተካበ በቅድሚያ ስለግዜህ በአንባብያን ስም ከፍ ያለ ምስጋና እናቀርባለን! ወደ ውይይታችን ስንገባ፦ የሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያዊያን ስፖርት ፌዴሬሽን ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል መሆንህ ይታወቃል። ፌዴሬሽኑ ዘንድሮ የተመሰረተበትን 30ኛ ዓመት በድምቀት ለማክበር እንቅስቃሴ መጀመሩ ተሰምቷልና እስኪ ምን እያደረጋችሁ እንደሆነና የዘንድሮው ከቀዳሚዎቹ 29 ዓመታት ለየት የሚልበትንም ጭምር ዘርዘር አድርገህ ብትነግረን?

**መልስ፦** እኔም ስለተሰጠኝ ዕድል በጣም አመሰግናለሁ። አዎ! ዘንድሮ ፌዴሬሽናችን 30ኛ ዓመቱን ያከብራል። ይህንንም ምክንያት በማድረግ በመጪው ሃምሌ ወር ውስጥ ዋሽንግቶን ዲሲ ላይ ልዩና ደመቅ ያለ ውድድር ለማድረግ ከወዲሁ ዝግጅት ጀምረናል። እንደምታስታውሰው ባለፈው አመት ማለትም 29ኛውን ዓመት የስፖርት ውድድር ዳላስ ላይ ስናደርግ የተፈጠረ ችግር ነበር። ችግሩ ግን በአሜሪካና በመላው አለም ያለው ኢትዮጵያዊ ባደረገው ርብርብ ተወግዷል።



ተካበ ዘውዴ የቀድሞ ብሄራዊ እግር ኳስ ቡድን ተጫዋችና የወቅቱ የሰ.አ.ስ.ፌ. የውድድር አስተባባሪ።

ኢትዮጵያዊው ወገን ያደረገልን ድጋፍ መቼም ቃላት ሊገልጸው የሚችል አይመስለኝም፡፤ እናንተም ተከታትላችሁታል የዳላስ ዝግጅት ከመቼውም በበለጠ ድምቀት ነበር ከጅምር እስከ ፍጻሜው የተከናወነው። አሁንም ያ የትብብርና የድጋፍ መንፈስ ከኛም ከሕዝባችንም ጋር እንዳለ ነው 30ኛውን አመት ዝግጅት የጀመርነውና በጣም በደመቀና በተሳካ መልክ እንደሚከናወን እርግጠኛ ነኝ።

ምን ለየት ያለ ነገር አለ? ላልከው እኔ የምሰራው የውድድር ፕሮግራምና ድልድል ኮሜቴ ውስጥ በመሆኑ በቂ ኢንፎርሜሽን ልሰጥህ መቻሌን እጠራጠራለሁ። በውድድር ረገድ ግን ከአውሮፓም ቡድን ይዘው እንደሚመጡ እየተነገረን ነው። ለአብዛኛው የዋሽንግቶን ነዋሪ ማዕከል በሆነ ቦታም ስቴድዮም ተገኝቷል። ሌላው በውድድሩ መሃል አርብ ቀን በሚከበረው የኢትዮጵያ ቀን ላይ በዘመናዊና ባህላዊ ሙዚቃዎች የሚያዝናኑ በርካታ አርቲስቶች ካሁኑ ዝግጅት ጀምረዋል፡፤ ዘንድሮ እንዲያውም የኢትዮጵያ ቀን በዘፈን ብቻ መከበር የለበትም! ልዩ ልዩ ዝግጅቶችም መካተት አለባቸው ተብሎም እየተሰራበት እንደሆነ አውቃለሁ። በበለጠ ዝርዝር ኢንፎርሜሽን ሊሰጥህ የሚችለው የውጭ ግንኙነት ሃላፊው ነው።

በዚህ አጋጣሚ ግን ባለፈው አመት ፌዴሬሽናችን ችግር በገጠመው ግዜ ከጎናችን በመቆም ኢትዮጵያዊው ሁሉ ያኛውን ፌዴሬሽን ቦይኮት እንዲያደርግ በማስተባበር ከአውሮፓና ከናንተም ከአውስትራሊያ ለተደረገልን ድጋፍ በፌዴሬሽናችን ስም ከልብ የመነጨ ምስጋና ላቀርብ እወዳለሁ።

**ጥያቄ፦** 30ኛ አመታችሁን ስታከብሩ ከአውሮፓም ቡድን ይመጣል ብለሃል፤ ምናልባት ሜልበርን ወይም ከአውስትራሊያ የመምጣት ፍላጎትና ተነሳሽነት ቢኖር ፌዴሬሽናችሁ ምን ድጋፍ ያደርጋል በውድድርስ ረገድ እንዴት ነው እንግዳ ቡድኖች የሚሳተፉት?

**መልስ፦**ይህ በጣም ደስ የሚል ነገር ነው፤ በተለይ አህጉር አቋርጠው ለሚመጡ እንግዳ ቡድኖች ትልቅ ክብርና ልዩ ግምት ነው የምንሰጠው። እንደምታውቀው ፋይናሻሊ እንዲህ እናደርጋለን የምንለው ነገር የለም። አቅሙም ስለሌለ። ነገር ግን ልናደርግ የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ ደስተኞች ነን። እንግዳ ቡድን በምን መልክ ነው የሚወዳደረው ላልከው፦ ኤግዚብሽን ጌም የሚባል ልዩ ውድድር አለ; በዚያ ውስጥ ይሳተፋሉ፡፤ በጣም ብዙ ሰው የሚወደውና የሚያየው ውድድር ነው፡፤ በተለይ ከአውስትራሊያ የሚመጣ ቡድን ካለ ለኛ ስፔሻል ኬዝ ስለሆነ እንነጋገርበታለን።

**ጥያቄ፦** የፌዴሬሽናችሁ ጥንካሬ ከስራ ውጤታችሁ እየታየ ነው። እኛጋ ደግሞ የነበረው ፌዴሬሽናችን ገና ከጅምሩ እንደናንተ የገጠመውን የመከፋፈል አደጋ እንደምንም ለማለፍ ቢችልም በጥንካሬ መቀጠል ግን አልቻለም። አሁንም በዘንድሮው ውድድር ላይ እንደገና ለማቋቋም እየታሰበ ነውና፡፤ እስኪ ከአሰራርም ከመዋ ቅርም አንጻር ልምድ ብታካፍለን።

**መልስ፦**በመጀመሪያ ልገልጽ የምሻው የኛ ፌዴሬሽንም በጥንካሬ ጀምሮ በጥንካሬ የኖረና እዚህ የደረሰ አይደለም። ስንጀምር ብዙ ብዙ ችግሮች ገጥመውናል። ጓደኛሞች ከሃገር ሃገር እየሄዱ በመጫወት የጀመሩት እንቅስቃሴ ነው ዛሬ ትልቅ ፌዴሬሽን የሆነው። 30 ዓመት ቀላል ዕድሜ አይደለም። ብዙ ተደክሞ በታል። ብዙ ችግሮች ገጥመውናል። ከጠዋቱ 2 ሰአት ጀምረን ማታ 4 ሰአት ድረስ ስብሰባ የደርግንባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው። ዋናው ነገር ግን የሃሳብ ልዩነቶችን ለፌዴሬሽኑ ህልውና ስንል አቻችለን ለማለፍ በመቻላችን ነው ዛሬ ላይ ለመድረስ የቻልነው።

# ቆይታ ከተካበ ....

[ከገጽ 9 የዞረ]

**መልስ፡-** በርግጥ አንዳንዴ መለያየትም መፍትሄ የሚሆንበት ግዜ አለ። ፈጦ ከመጣ ትለያያለህ። ነገር ግን ብዙ ግዜ የሚገጥሙን ችግሮች እኔ ያልኩት ካልሆነ በሚል ግትር አመለካከት እየተለጠጡ እንጂ ለመለያየት የሚያበቁ ሆነው አይደለም፡፤ እናም ከኛ ልትማሩት ይገባል የምለው ምንም አይነት የሃሳብ ልዩነት ቢኖር ለፌዴሬሽኑ ሲባል ተቻችሎ የመሄድን ልምድ ማዳበር ነው።ቀና ውይይትና ተግባብቶ የመስራት ልምድ ካለ በችሎታ ማነስም ሆነ በኮሚቴ አወቃቀር ጉድለት የሚከሰቱ ችግሮች ሁሉ በቀላሉ ይወገዳሉ። ዋናው ተግባብቶ ተቻችሎ ለመስራት ሁሉም ዝግጁ ሆኖ መገኘቱ ነው። የፌዴሬሽኑን አወቃቀር ላልከው ለናንተ የሚጠቅም ከሆነ ልገልጽልህ እችላለሁ፡፤

በመጀመሪያ በውድድሩ የሚሳተፉ ቡድኖች እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ተወካይ ይልኩና የፌዴሬሽኑ ቦርድ ይቋቋማል፡፤ እነዛ የቡድን ተወካዮች የቦርድ አባላት ይሰበሰቡና ከውስጣቸው 7 አባላት ያሉት የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይመርጣሉ፡፤ ያ ኮሚቴ ፌዴሬሽኑን ይመራል ማለት ነው። ለምሳሌ እኔና አንድ ሰው ከቡድናችን ተወክለን የቦርድ አባል ሆንን። ቦርዱ ተሰብስቦ ስራ አስፈጻሚ ሲመርጥ እኔ በመመረጤ ከሰባቱ አንዱ ሆኜ እየሰራሁ ነው። ሰባቱ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ደግሞ የራሳቸው የሆነ ምድብ ሃላፊነት ይኖራቸዋል።

እኔ ለምሳሌ የውድድር ፕሮግራምን የመምራት ሃላፊነት ስለተሰጠኝ የምሰራው ይህንን ነው። ይህን ሃላፊነት ለመወጣት ደግሞ አብረውኝ የሚሰሩ ሰዎችን መርጬ ከወጣትም አንድ ቀላቅዬ ስራችንን እንሰራለን ማለት ነው፡፤ ሁሉም የተመደበበትን ሃላ\ፊነት እየተወጣ እንደ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በጋራ ልንሰራቸውና ልንወስናቸው በሚገቡ ነግሮች ላይ፡ደግሞ አብረን እንሰራለን። የአገልግሎት ዘመናችንን ስንጨርስ አሁንም ሁሉም ቡድን ተወካይ ይልክና ቦርድ ይቋቋማል በዚሁ መልክ፡ ይቀጥላል ማለት ነው፡፤

**ጥያቄ፡-** ፌዴሬሽኑ የሚዋቀረው ከየስቴቱ በመጡ ወኪሎች ሳይሆን ከየቡድኑ በሚወከሉ ሰዎች ነው ማለት ነው። የኛ ደግሞ ለየት የሚለው ፌዴሬሽኑ የሚቋቋመው የየ ስቴቱ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበራት በሚልኳቸው ወኪሎች ነው፡፤ እናንተ ጋር ያኢትዮጵያን ኮሚኒቲ የሚወክሉ የለም ማለት ነው?

**መልስ፡-**አሉ! እኛ ጋ አሁንም ትንሽ ችግር እየፈጠረ ቻሌንጅ እያደረገን ያለው የቡድ ኖች አወቃቀር ልዩነት ነው። 3 አይነት ቡድ ኖች አሉ፡፤ <u>1ኛው</u> ማንም ግለሰብ በስሙ ማስመዝገብ ስለሚችል የእገሌ ቡድን ተብሎ የሚቋቋም ቡድን ነው። <u>2ኛው</u> በቡድን መልክ ተቋቁመው የራሳቸው ቦርድና አመራር ያላቸው ናቸው። <u>3ኛዎቹ</u> እናንተ ጋ እንዳለው በኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ስር ያሉ ቡድኖች ናቸው። እናም በቦርድ አሰራርና አወካከል ላይ አጨቃጫቂ ጉዳዮች ስለሚከሰቱ ይህንን በቋሚነት ለማስወገድ እየሰራንበት ነው። የናተ ግን አንድ ወጥ አወካከል ስለሆነ ጥሩ ይመስለኛል።

**ጥያቄ፡-**ወጣቶችን እየቀላቀልን እንሰራለን ስትል እዚህም እኛ ጋ ወጣቶችን ቀላቅሎ ለማሰራት እየተሞከረ ነው።ለወጣቶች ኃላፊነት የምትሰጡት እንዴት ነው?

**መልስ፡-**እኛ ሁሌም በዚህ ሁኔታ አንቆይም ስለዚህ ወጣቶች በኛ እንዲተኩ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። በመሆኑም በየስራ ሃላፊነቱ አንድም ሁለትም ወጣቶች ከአዋቂዎች ጋር እየተመደቡ ስራውን እንዲለምዱ እናደ



ተካበ ዘውዴ ከነገው ትውልድ
ከሳይመን ተካበ ጋር በልምምድ ላይ

ርጋለን። ለምሳሌ ከኔ ጋር አብረውኝ ውድድርና ፕሮግራሙን የሚመሩት እንደ ፍስሃ ወልደ አማኑኤል አይነት የበርካታ አመታት ልምድ ያላቸው ናቸው ። ቀደም ብዬ እንደነገርኩ አንድ ወጣት ልጅም አብሮን እንዲሰራ አድርገናል ልምድ እንዲያገኝ ማለት ነው፡፤ ከጥቂት አመታት በኋላ ይህ ወጣት ራሱን ችሎ ሰርቶ ሊያሰራ ይችላል ማለት ነው።

**ጥያቄ፡-**አሁን ደግሞ ከፌዴሬሽኑ ወጣ ልበልና ወቅቱ በፈጠረው አጋጣሚ ላይ ጥያቄ ላንሳ፤ ብሄራዊ ቡድናችን በሚቀጥር ለው ወር ደቡብ አፍሪካ ላይ ለሚደረገው የአፍሪካ ዋንጫ አልፏል ;። በመጀመሪያ ቡድኑ ከ31 አመታት በኋላ ለዚህ በመብቃቱ ምን ተሰማህ ከሱዳን ጋር ያደረጉትን ጨዋታስ ተከታትለህው ነበርን? ደቡብ አፍሪካ ላይስ ውጤት ያመጣል ብለህ ትጠብቃለህ? አንዳንዶች በእድል እንጂ በችሎታ ስላላለፉ ደቡብ አፍሪካ ላይም ውጤት አንጠብቅም እያሉ ያሚርታሉ አንተስ ምን ትላለህ?

**መልስ፡-**ቡድናች ሱዳንን 2-0 ያሸነፈበትን ጨዋታ ከልጄ ጋር ሆኜ ነው ያየሁት። በተለይ ሁለትኛው ጎል ሲገባ የተሰማኝን ደስታ ቃላት አይገልጸውም። ከልጄ ጋር እየጮህን ነበር ደስታችንን የገለጽነው። እኔ በምጫወትበት ግዜ ለአፍሪካ ዋንጫ አልፈን ለመጫወት በጣም እጓጓ ነበር። እንደ ስፖርተኛ የራስህ ድሪም ይኖርሃል እናም የኔ ድሪም አንዱ ለአፍሪካ ዋንጫ አልፈን ለመጫወት ነበር ግን አልሆነም።

አሁን ግን ከ31 ዓመታት በኋላ ተሳክቶ ሳየው በጣም ነው ደስ ያለኝ።እድል የሚባለውን ነገር እኔ ብዙም አላምንበትም ምክንያቱም ለውጤት የሚያበቃህ በሜ ዳው ላይ ያምታደርገው እንቅስቃሴ ብቻ ነው። በርግጥ አንዳንዴ እድል ሊያጋጥም ይችል ይሆናል እኔ ግን አላምንበትም።

ይሁንና ቡድኑ ጠንካራ ጎንም ደካማ ጎንም አለው። ለምሳሌ በፊት መስመር ላይ ያሉት ሰላዲንና አዳነ ጥሩ ናቸው። ሰላዲን ቦታ ይዞና ራሱን ክፍት አድርጎ በመጫወት ረገድ ጎበዝ ነው;። አዳነም ኳስ በመያዝ ጥሩ ይንቀሳቀሳል። ሳሳ ብሎ ያየሁት መሃል ላይ ነው። የኛ ቡድን ከዚህ በፊት የሚታ ወቅበት ጠንካራ ቦታ መሃል ላይ ነው፡፤ አሁን ግን ሳስቷል። ሱዳን ላይ የገቡትም ሁለት ክሮስ የተደረጉ ኳሶች ናቸው እንጂ መሃል ላይ ያሉት ብዙም ሲደግፉ አልታ ዩም ይህንን ጉድለት አሰልጣኞችም እንደ ሚያዩት ተስፋ አለኝ። ደቡብ አፍሪካም ውጤት ሊያመጡ ይችሉ ይሆናል።

[**ወደ ገጽ 20 ዞሯል**]

# አንድ አፍታ ከብሄራዊ ቡድናችን ተጫዋቾች ጋር

**ኢ.ቶ** ጤና ይስጥልኝ አዳነ በቅድሚያ ስለትብብርህ በአውስትራሊያ ስፖርት አፍቃሪ አንባቢያን ስም ምስጋና አቀርባለሁ። ከ31 አመት በኋላ ደቡብ አፍሪካ ላይ ለሚደረገው የ29ኛው አፍሪካ ዋንጫ አልፋችኋል፡፤ይህ ደግሞ በውጭም በሃገር ውስጥም ያለውን ኢትዮጵያዊ የስፖርት አፍቃሪ አስደስቷል። አሁንስ ዝግጅታችሁ እንዴት ነው?



አዳነ ግርማ (አጥቂ)

**አዳነ ግርማ፡-** እኔም ከአውስትራሊያ ድረስ ደውላችሁ፤ እዚያ ያለውን ስፖርት አፍቃሪ ለመድረስ እንድችል ስላደረጋችሁ በጣም አመስግናለሁ። በጣም ጥሩ ዝግጅት አድርገናል አሁንም በቀረን ግዜ እየተዘጋጀን ነው። ቡድናችን በጣም የተሟላ ቡድን ነው። በዚያ ላይ በአሁኑ ሰአት ከህዝብ በምናገኘው ከፍተኛ የሞራል ድጋፍ በጣም እየተበራታን ነው፡፤ ዛሬ እንዲያውም በጣም ከፍተኛ ወደ ሆነ ሆቴል ተዘዋውረናል፡፤ የሚደረግልን እንከብካቤ በጣም ጥሩ ነው። ከሁሉም በላይ ግን ቡድኑ ውስጥ ያለነው ልጆች በሙሉ ጓደኛሞች ሆነን ለረዥም ግዜ የተጫወትን በመሆኑ ተግባብቶ በመጫወት ረገድ ምንም ችግር የለብንም፡፡

**ኢ.ቶ** ምድባችሁ ውስጥ ዛምቢያና ናይጀሪያን የመሰሉ ጠንካራ ቡድኖች አሉበትና ትንሽም ቢሆን ስጋት አልፈጠረባችሁም?

**አዳነ ግርማ፡-** ምንም ስጋት አልፈጠረብንም። በርግጥ ጠንካራ ምድብ ነው። ነገር ግን እኛም ተዘጋጅተናል። በዚያም ላይ ኳስ ጨዋታ ስለሆነ ሜዳ ውስጥ ገብተህ እስከትፈታተን ድረስ ምንም ማለት አይቻልም። አንድ የማረጋግጥልህ ነገር ቢኖር ደቡብ አፍሪካ የምንሄደው ለተሳትፎ ሳይሆን ለውጤት መሆኑን ነው። ሁላችንም አንድ አይነት መንፈስ ነው ያለን። ጥሩ ተጫውተን ውጤት ማምጣት ነው ዓላማችን። ስጋትና ፍርሃት የሚባል ነገር የለብንም።

**ኢ.ቶ** ለምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ ዋንጫ 2ኛው ቡድን ከሚሄድ እናንተ ብትሄዱ ጥሩ ልምድ ይሆናችሁ ነበር የሚል አስተያየት እየሰማን ነው? ለምን አልተሳተፋችሁም ምናልባት ተጫዋች ሊጎዳ ይችላል ብላችሁ ይሆን?

**አዳነ ግርማ፡-** እንጎዳለን ብለን አይደለም። ምን መሰለህ፡ ለብሄራዊ ቡድን ብዙ ተጨዋቾች ያስመረጡት ክለቦች ጊዮርጊስና ደደቢት ስለሆኑ እነዚህ ቡድኖች ብሄራዊ ቡድኑ ባለበት ጨዋታ ምክንያት በተከታታይ ተጫዋቾቻቸውን እያጡ ውጤት እየጣሉ ነበር፤ በዛም ላይ ብዙ ጨዋታዎች ስላደረግን ደክመን ነበር፡፤ እንደገና እዚያ ውድድር ውስጥ መግባት ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናልና ሌሎች እድሉን ያላገኙ ደግሞ ሄደው ልምድ ይውሰዱ በሚል ታስቦ ነው። ድካም እንጂ እንጎዳለን ብለን አይደለም፡፡

**ኢ.ቶ** ቡድናችን የተሟላ ቡድን ነው ብለሃል፡፤ ከሱዳን ጋር ባደረጋችሁት ጨዋታ ግን አማካኝ ቦታ በጣም ሳስቶ እንደነበር አስተውለናል። ዕለታዊ ድክመት ነው ወይስ አማካኝ ቦታው አሁንም ..?

**አዳነ ግርማ፡-** በአማካኝ ቦታ የሚጫወቱት ልጆች ከማናችንም የማያንሱ ጎበዞችና ልምድ ያላቸው ናቸው፡፤ የዛን ቀን ልክ ነህ ትንሽ መዳከም ነበር። ለነገሩ የህዝቡ ለውጤት መጓጓት የሚፈጥረው ፕሬዠር አለ፤፡ አንዳንድ ተጫዋች መቋቋም ይችላል አንዳንዱ ደግሞ ይጨነቃል። በህዝብህ ፊት ስትጫወት ደግሞ ጭንቀቱ ትንሽ ይበዛል፡፤ በተረፈ ቡድናችን በሁሉም በኩል የተሟላ ቡድን ነው፡፤

**ኢ.ቶ** በሱዳን ላይ የመጀመሪያውን ጎል ስታስቆጥር ምን ተሰማህ እናሸንፋለን ብለህ አስበህ ነበር?

**አዳነ ግርማ፡-** ባይገርምህ እኔ ብቻ ሳልሆን ሁላችንም እንደ ምናሸንፍ እርግጠኞች ነበርን፡፡ አሸንፈን ከተደሰትነው የበለጠ ብንሸነፍ ነበር የምንጎዳው። ጎል ስታገባ ምን ተሰማህ ?ላልከው፡ እኔ የመጀመሪያውን ሳገባ በግዜው ደስ ብሎኛል። ነገር ግን ያቺ አንድ ጎል ብቻ ለማሸነፍ ስለማታበቃን ደስታዬ ሙሉ አልነበረም፡፤ ደስታዬ የተሟላው ሰላዲን ሲያገባ ነው፡፡ በህይወቴ በምንም ነገር እንደዛ ቀን ተደስቼ አላውቅም፡፡ ማሸነፋችን እጅግ በጣም በጣም ያስደሰተኝ ለምን መሰለህ? ከክፍለ ሃገር መጥቶ ቅዳሜ ሌሊት ስቴዲየም ያደረውን ህዝብ ማስደሰት መቻላችን ነው። ለዚህ ህዝብ ከዚህም በላይ ይገባዋል፡፤ለደስታው ምክንያት የሆነቺውን አንድ ጎል በማግባቴ ደግሞ በግሌ ደስ ብሎኛል።

**ኢ.ቶ** ሱዳንን ስታሸንፉ የነበረውን የህዝብ ስሜት አይተናል። እንኳን እዛ እኛም እዚህ ጨፍረናል፡፡ አሁንስ ምን ይመስላል የህዝቡ ስሜት ከደቡብ አፍሪካ ጉዟችሁ ምን ይጠብቅ ይመስ ልሃል?

**አዳነ ግርማ፡-** ህዝቡን ከምንም በላይ ያስደሰተው ከ31 አመታት በኋላ ለአፍሪካ ዋንጫ ማለፋችን ነው፡፡ የኢትዮጵያ ስፖርት አፍቃሪ እንደምታውቀው ለረዥም አመታት ያለውጤት ብንቆይም ሳይሰለችና ተስፋ ሳይቆርጥ ሁሌም ድጋፍ ሲሰጥ የቆየ ህዝብ ነው፡፡አሁን ደግሞ በማለፋችን በጣም በጣም ተደስቷል፡፡ ደቡብ አፍሪካ ላይ ሄደን ውጤት ብናመጣ ደግሞ ደስታው እጥፍ ድርብ እንደሚሆን ምንም ጥርጥር የለኝም። ውጤት ይጠብቃል ወይ ላልከው? ውድድር እንደመሆኑ ውጤት መጠበቁ አይቀርም እኛም እንዳልኩህ የምንሄደው ለተሳትፎ አይደለም ጥሩ ተጫውተን ውጤት ለማምጣት ነው፡፡

**ኢ.ቶ** የወዳጅነት ጨዋታ ታደርጋላችሁ የሚባል ነገር ሰምተናል እውነት ነው?

**አዳነ ግርማ፡-** ተብሏል ግን እስካሁን በግልጽ የተነገረን ነገር የለም።

**ኢ.ቶ** ውጭ አገር ያሉ ተጨዋቾች ቡድኑን ሊቀላቀሉ ይችላሉ የሚባል ነገር አለ ፤ እስካሁን ከውጭ መጥቶ የተቀላቀለ አለ ወይም በቅርብ የሚመጣ ይኖራል?

**አዳነ ግርማ፡-** እስካሁን የተቀላቀለን የለም ሲባል ግን ሰምቻለሁ።

**ኢ.ቶ** በጣም አመስግናለሁ አዳነ መልካም ውጤት እመኛለሁ

**አዳነ ግርማ፡-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ!

[ከጀማል ጣሰው ጋር የተደረገው ቃለ ምልልስ በገጽ 12 ይቀጥላል]

# አንድ አፍታ ከብሄራዊ ቡድናችን ...

**ኢ.ቶ** ጤና ይስጥልኝ ጀማል! ስለ ግዜህ በዝግጅት ክፍላችንና በአንባቢያን ስም አመሰግናለሁ፡፤ እንዴት ነህ አሁን ከሱዳን ጋር ባደረጋችሁት ጨዋታ መጨረሻ ላይ ጉዳት ደርሶብህ ወጥተህ ነበር?


ጀማል ጣሰው (ግብ ጠባቂ)

**ጀማል፡** በጣም አመስግናለሁ ስለተሰጠኝ እድል፡፤ አዎ ከሱዳን ጋር ስንጫወት መጨረሻ አካባቢ ግዜ አባክናለሁ ብዬ ወድቄ የምርም ለካ ተጎቼ ነበር፡፡ በቃሬዛ ወጣሁና አረፍኩ። አሁን ግን በጣም ተሸሎኝ ቡድኑን ተቀላቅዩ ልምምድ እያደረግን ነው።

**ኢ.ቶ** ልምምድ እንዴት ይዞችኋል? ከ31 አመታት በኋላ በተገኘው በአፍሪካ ዋንጫ የመካፈል እድል። ኢትዮጵያዊው ሁሉ ተደስቷል። ውድድሩንም በጉጉት እየጠበቀ ነው። ምን ትላለህ?

**ጀማል፡** ለአፍሪካ ዋንጫ ማለፋችን በጣም በጣም ነው ያስደሰተን። እኔ እንዳየህው 2 ለዜሮ እየመራን ጨዋታው ሳያልቅ ተጎድቼና ራሴን ስቼ በመውጣቴ ማሸነፋችንን እንኳ ያወቅኩት ሆስፒታል ውስጥ ከሰመመን ስንቃ ነው። አሁንም ድረስ ህልም ህልም ይመስለኛል። በርግጥ እናሸንፋለን! ማሸነፍም አለብን ብለን በሙሉ ልብ ነበር የገባነው፡፡፡ ግን ሆኖ ስታገኘው ደግሞ ደስታው ትንሽ ለየት ይላል። ህዝቡ ይሰጠን የነበረው ሞራል ነው ለዚህ ያበቃን። አሁንም በዛው ሞራል ውስጥ ሆነን ጠንካራ ልምምድ እያደረግን ነው፡፡፡ ደቡብ አፍሪካም ጥሩ ተጫውተን ህዝባችንን ለማስደሰት ነው ጉጉታችንና ፍላጎታችን።

**ኢ.ቶ** ናይጀሪያ ዛምቢያ ቡርኪናፋሶ ቀላል ምድብ ውስጥ አይደላችሁምና እንዴት ነው ?

**ጀማል፡** ሶስቱም ቡድኖች በጣም ከባድ ናቸው፡፡፡ ግን ኳስ ጨዋታ በመሆኑ እኛም የበኩላችንን ልምምድ አድርገን ጥሩ ተፎካካሪ ለመሆን ነው እየሰራን ያለነው። ተጋጣሚያችን ከባድም ይሁን ቀላል እኛ በበኩላችን ማድረግ የምንችለውን ሁሉ በማድረግ የራሳችንን ዝግጅት አድርገን መግባት ነው ያለብን፡፡የምናደርገውም እንደሱ ነው። ስለ ውጤት አሁን እያሰብን የምንጨንቅበት ምክንያት የለም፡፡ 90 ደቂቃው ይበቃል ለጭንቀቱ። ሲገባብህ ለማግባት መሯሯጥ ፤ ካገባህም እንዳይገባብህ መከላከል፤ ይህን አይነቱ ጭንቀትና ትግል እዚያው ሜዳ ውስጥ ስትገባ የምታደርገው ነው፡፡ የተጋጣሚን ጠንካራ ጎንና ደካማ ጎን ቀድሞ አውቆ ቡድኑን በዛ መሰረት ማዘጋጀት አስፈላጊ እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ይሁንና ይህ ደግሞ የአሰልጣኝ ስራ ስለሆነ እኔ ምንም ማለት አልችልም። ያደረግነው ዝግጅት ግን በጣም ጥሩ ነው።

**ኢ.ቶ** መጽሄታችን ስርጭቷ አውስትራሊያ ውስጥ ነውና በአውስትራሊያ ለሚገኘው ኢትዮጵያዊ የስፖርት አፍቃሪ ምን የምታስተላልፈው መልእዕክት አለህ

**ጀማል፡** ያው ሃገራችንን ወክለን የምንጫወት በመሆኑ በውጭም በውስጥም ያለው ኢትዮጵያዊ ውድድሩን በጉጉት እንደሚጠብቅና ጥሩ ውጤት እንድናመጣ እንደሚፈልግ የታወቀ ነው፡፡ እኛም ጉጉታችን ሃገራችንንና ህዝባችንን ለማስደሰት ነው፡፤ ስለዚህ እስካሁን ያልተለየን ድጋፋችሁ አሁንም አይለየን በጸሎት አግዙን ኢንሽ አላህ እኛም እንበረታለን፡፡

**ኢ.ቶ** በጣም አመሰግናለሁ ጀማል
**ጀማል፡** እኔም በጣም አመሰግናለሁ።



# የአፍሪካ ስፖርት አባት ክቡር ይድነቃቸው ተሰማ ሲታወሱ....!




የኢትዮጵያ ስፖርት ታሪክ ጉዞና ዕድገት ሲነሳ አብረው ከሚነሱት አንጋፋ ባለታሪኮች መካከል አንዱና ዋናው አቶ ይድነቃቸው ተሰማ ናቸው። መስከረም አንድ ቀን 1914 ዓ/ም በዕለተ እንቁጣጣሽ ጅማ ከተማ ውስጥ ከነጋድራስ ተሰማ እሸቴና ከወ/ሮ ሙላቷ ገብረ ሥላሴ የተወለዱት አቶ ይድነቃቸው እንደ ስማቸው ሁሉ የህይወት ዘመን ምግባራቸውም በአስደናቂነቱ በታሪክ ደምቆ ተፅፏል።

*'የኢትዮጵያ ዘመናዊ ስፖርት አባት'* በሚል ሀገርኛ መጠሪያ ብቻ ሳይሆን ***'የአፍሪካ ስፖርት አባት'*** በሚል አህጉራዊ ስም የሚታወቁትም አቶ ይድነቃቸው ገና በልጅነት ዕድሜያቸው አዲስ አበባ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ተማሪ እያሉ ነበር በስፖርት በተለይም በእግር ኳስ ልዩ ተሰጥዖ እንዳላቸው የተመሰከረላቸው።

በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነውን የቅዱስ ግዮርጊስ የእግር ኳስ ቡድን ከ14 ዓመት ዕድሜያቸው ጀምረው ተቀላቅለው ተጫውተዋል። ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድንም በተደጋጋሚ ተሰልፈዋል። በወጣትነት ዘመናቸው በብስክሌት ውድድር፤ በአጭር ርቀት ሩጫና በቦክሰኝነት ቢሳተፉም እግር ኳስ ግን ከሁሉም የስፖርት ዘርፎች ተሳትፏቸው በላይ አክሊል ተሰጥዖዋቸው ነበር።

ይድነቃቸው ቅዱስ ጊዮርጊስ ቡድን ውስጥ ከወጣትነት ዘመናቸው አንስቶ በድምሩ ለሃያ ሶስት ዓመት በተጫዋችነት የቆዩ ሲሆን ይህም በሀገራችን ትልቁ ሪከርድ ሆኖ ተመዝግቧል። ቅዱስ ጊዮርጊስ ቡድን በእሳቸው ዘመን ካደረጋቸው 365 ግጥሚያዎች ውስጥ ካስቆጠራቸው ግቦች 318 ጎሎች የተገኙት በይድነቃቸው ተሰማ ነበር። ይህም የቡድኑ ኮኮብ ግብ አግቢ የሚል መጠሪያን አስገኝቶላቸዋል።

የኢትዮጵያ ብሄራዊ የእግር ካስ ቡድን ተቋቁሞ ዓለም ዐቀፍ ግጥሚያዎችን ማድረግ በጀመረበት ወቅት (1947 እአአ) አቶ ይድነቃቸው ዕድሜያቸው 28 ዓመት ደርሷል። ይሁንና በነበራቸው ችሎታና አካላዊም ብቃት በብሄራዊ ቡድን ውስጥ ለአስራ አምስት ጊዜ የተሰለፉ ሲሆን በጅቡቲና ኢትዮጵያ ግጥሚያም ኢትዮጵያ ጅቡቲን 5 ለባዶ አሸንፋለች።

ዘመናዊውን የኢትዮጵያ ስፖርት ፅ/ቤት ከአቶ አምደ ሚካኤል ደሳለኝ ጋር በ1943 ሲመሰርቱ ዕድሜያቸው ገና 22 ዓመት ነበር። አቶ ይድነቃቸው ከተጫዋችነት ሌላ ለክለባቸው እና ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን በአሰልጣኝነት ያገለገሉ ሲሆን በ1962 እአአ በተደረገው የአፍሪካ ዋንጫ ውድድር ኢትዮጵያ አሸናፊነቱን የተቀዳጀችው በእሳቸው አሰልጣኝነት ነበር።

ከሁሉም በላይ ግን አቶ ይድነቃቸው በሀገራቸው በኢትዮጵያ፤ በአህጉረ አፍሪካና በመላው ዓለም ስፖርት ታሪክ ውስጥ የሚታወቀው ቋሚ ዓለም ዐቀፋዊ የታሪክ ሌጋሲያቸው፤- *ስፖርት ለፍቅር፤ ለሠላምና ለወንድማማችነት የውድድር መድረክ እንዲሆን የዘር መድልዖን ከስፖርት ተቋማትና የውድድር መድረኮች ለማስወገድ ያደረጉት ታላቅ አርአያዊ ትግልና ትግላቸውም ያስገኘው የድል ውጤት ነው።* ይድነቃቸው በስፖርት ተቋማትና መድረክ የህይማኖት መድልዖ እንዳይኖር በግንባር ቀደምትነት ተፋልመዋል። አፍሪካ በዓለም የስፖርት ውድድር መድረኮች (በኦሎምፒክና በዓለም እግር ኳስ ውድድር) ላይ ተገቢው ውክልና እና ቦታ እንዲኖራት ካደረጉት አንዱና ዋነኛው አቶ ይድነቃቸው መሆናቸውን ታሪክ በደማቁ አቅልሞላቸዋል።

በ1964 እአአ የተቋቋመው የአፍሪካ እግር ኳስ ፌዴሬሽን (CAF) መስራች ከሆኑት አንዱ ይድነቃቸው ናቸው። የዚህ ድርጅት መተዳደሪያ ደንብ በአብዛኛው በአቶ ይድነቃቸው የቀረበ መሆኑን የድርጅቱ ምስረታ ታሪክ ይገልፃል። ከ1964 እስከ 1972 ተቋሙን በምክትል ፕሬዚዳንትነትና ከ1972 እስከ 1987 ደግሞ በፕሬዚዳንትነት አገልግለዋል።

አቶ ይድነቃቸው ህይወታቸውን በሙሉ ለስፖርት ዕድገትና መስፋፋት ያዋሉ አንጋፋ ስፖርተኛና ዓለም ዐቀፍ የስፖርት መሪ የነበሩ የኢትዮጵያ ልጅ ናቸው።



ይድነቃቸው የአፍሪካ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ፕሬዚዳንት፤ የአፍሪካ ስፖርት ኮንግረስና የዓለም ዐቀፍ ኦሎምፒክ ኮሚቴ አባል፤ ከ1966 እስከ 1974 የፊፋ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባል በመሆን ስፖርቱንና የዓለም ስፖርት ቤተሰብን ያለመታከት አገልግለዋል።

ይድነቃቸው ተሰማ ከእኒህ አህጉራዊና ዓለም ዐቀፋዊ የስፖርት ድርጅቶች አባልነትና መሪነታቸው ሌላ የኢትዮጵያ እግር ኳስና ስፖርት ፌዴሬሽን ዋና ፀሀፊ፤ የብሄራዊ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ፕሬዚዳንትና የስፖርት ፌዴሬሽን ኮሚሽነር በመሆን ሀገራቸውን በከፍተኛ ትጋት በማገልገል እያሉ ስፖርታዊ ለውጦችንና ውጤቶችን ለማስገኘት በቅተዋል። አቶ ይድነቃቸው ለኢትዮጵያ አትሌቲክስ ማበብና መጎልበት አልፎም ሀገራችን የድል አንፀባራቂ መሆን እንድትችል ካደረጓት አንጋፋ ባለውለተኞች አንዱ ናቸው።

የአልኮልና የትንባሆ /ሲጋራ/ ካምፓኒዎች በአፍሪካ ስታዲየሞችና በስፖርት የውድድር መድረኮች የንግድ ማሻሻጫ ማስታወቂያ ዎቻቸውን እንዳያቀርቡ በብረቱ ይቃወሙና ይታገሉ የነበሩ ብቸኛ ድምፅ ናቸው።

በእንግሊዝኛ በፈረንሳይኛና በስፓኒሽ ቋንቋዎች የተካኑት አቶ ይድነቃቸው በ1966 የፊፋ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባል ከሆኑ በሁዋላ በፊፋ ውስጥ አፍሪካ ሊኖራት ስለሚገባው ድርሻና አባልነት ያደረጉት ከፍተኛ ትንቅንቅ ዛሬም ድረስ በድርጅቱ ታሪክ ጉልህ ሥፍራን ይዞ ይገኛል።

ለምሳሌ አውሮፓውያን በፊፋ ውስጥ በነበራቸው/ባላቸው ከፍተኛ ተደማጭነት አፍሪካውያን ቡድኖችን በማሳተፍም ሆነ አፍሪካ በሚኖራት የውክልና /ኮታ/ ቁጥር የነበራቸው አመለካከት የተዛባና አድሏዊ መሆኑን በመገንዘባቸው ይህ የፊፋ አሰራርና ደንብ እንዲቀየር በግንባር ቀደምትነት የታገሉት አቶ ይድነቃቸው ነበሩ።

የአፍሪካ እግር ኳስ ፌዴሬሽንን አባላት በማስተባበር አፍሪካ በዓለም እግር ኳስ ማጣሪያ ለሚኖራት ምደባ /ኮታ/ ይድነቃቸው ባደረጉት ትግል የወቅቱ ፓን አፍሪካኒስት መሪዎች ድጋፍ የነበራቸው ሲሆን በተለይ የጋናው ፕሬዚዳንት ኩዋሚ ኑክሩማ ዋነኛ ደጋፊያቸው ሆነዋል።

ወደ ገጽ 34 ዞሯል

# ተወዳጁ የስፖርት ጋዜጠኛ ደምሴ ዳምጤ ማን ነበር ?

[በዝግጅት ክፍሉ]

ባለፈው ጥቅምት 26፤2005 ዓ.ም በሞት የተለየን ዕውቁ የስፖርት ጋዜጠኛ ደምሴ ዳምጤ በመላው የስፖርት አፍቃሪ ልብ ውስጥ ልዩ ትዝታ ጥሎ ያለፈ የሙያው ታላቅ ሰው ነው። በተሰለፈበት ሙያ ከማንም የላቀ ዝና አትርፏል።ከ 40 ዓመት በላይ በስሜት እንደነደደ፤



ብዙዎቹ ስለደምሴ የኳስ ፍቅርና ስሜት ሲያስቡ በተለይ የሚታሰባቸው ታህሳስ 17 ቀን 1880 ዓ.ም ነው።

በፍቅር እንደቀለጠ ኖሮ ከተሰናበተን እነሆ 2 ወር ደፈነ።

በ1945 ኢ.ም ድሬዳዋ ወስጥ የተወለደው ደምሴ ከኳስ ጋር የተዋወቀው ገና በሰስት አመቱ ጀምሮ መሆኑ ይነገራል። በዚያ እድሜው ወላጅ አባቱ አቶ ዳምጤ ሰንለው ወደ ስታዲዮም ሲሄዱ ያስከትሉት እንደነበር የሚያውቁ ይመሰክራሉ።

ከሙያው ጋር ፍቅር የወደቀው ግን « የመንፈስ አባቱን »ታላቁን ጋዜጠኛና ገጣሚ ሰለሞን ተሰማን መስማት ከጀመረ ወዲህ ነበር። ደምሴና ስፖርት - ደምሴና ሬድዮ ሚስጥራዊ ውል የተፈጣጠሙበት ምእራፍ። በወቅቱ ንጉሴ በድሬዳዋ ራስ መኮንን ት/ቤት ቀይቶ ደግሞ በከዚራ ት/ቤት የ 1ኛ ደረጃ ተማሪ ነበር።

## በሰለሞን መንገድ፤ በሰለሞን ዜማ

የእውቁን ጋዜጠኛ የሰለሞን ተሰማን የሬዲዮ ፕሮግራሞች ሲሰማ ትንሿ ልቡ  በስሜት ትቀልጣለች። የአነባበብ ስልቱን እየተከታተለም እሱኑ አስመስሎ ቤቱ ውስጥ ያንበለብለው ጀመር ። እያደር የሰለሞን ዘገባዎች ዘፈኖቹ ሆኑ። ደግሞ ደጋግሞ የሚያዜማቸው። ይህ ሙከራው ደግሞ ቤቱ ውስጥ ታፍኖ አልቀረም። ለቀለም ጓዶቹም ተረፈ እንጂ። መጪውን ስኬት በሚጠቁም መልኩ የት/ቤት ጓደኞቹ የትላንቱን ዜና እንዲደግምላቸው ይጠብቁት ጀመር።

በወቅቱ ሃረርጌ ግሩም የእግር ኳስ እንቅስቃሴ የሚታይባት ክ/ሃገር ነበረች። የድሬዎቹ ጨርቃ ጨርቅና ሲማንቶ ሁነኛ ተጫዋቾችን አፍርተዋል። እራሱ ደምሴ እንደሚያስታውሰው ከሆነ ሁለቱ ቡድኖች ሶስተኛውን የአፍሪካ ዋንጫ ለበላው ቡድናችን በርካታ ተጫዋቾችን ያፈሩ ነበሩ።

ይሁንና ድሬ የሜዲያ ሽፋን አታገኝም ነበር። የኢትዮጲያ ሬዲዮ በተለይም በአዲስ አበባ አንደኛ ዲቪዚዮንና የሸዋ ውድድሮች ላይ ነበር ትኩረት ሰጥቶ የሚዘገበው።

ይህ ደግሞ በኳስና በሰለሞን ሙያዊ ክህሎት ልቡ የቀለጠውን ወጣት በቁጭት የሚንጥ ሆኖ ተገኘ። ትንሹ ደምሴ መላ መታ።በሚጢጢ ጓደኞቹ ላይ የሰለጠነበትን ልምዱን ተጠቅሞ ያንበበበውን ክፍተት ለመሙላት ቆርጦ ተነሳ።እና የድሬን ውድድሮች እየተከታተለ ወደ አዲስ አበባ ይልክ ጀመር።«ጥሩ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል»

እንዲሉ ብርቱው ጋዜጠኛ ሰለሞንም አላሳፈረውም ነበር።

በእርግጥ አዲሱ አማተር የድሬዳዋ ዘጋቢ በዕድሜው ወጣት ሰው መሆኑ ገብቶታል። ሲያሻው "ወጣት ደምሴ" ሲለው ደግሞ ""ተማሪ ደምሴ "እያለ ነበር ለአድማጮቹ የሚያስተዋውቀው። ያም ሆኖ ግን እንደዚያ የሰከኑ ሪፖርቶች የሚያስተላልፍለት ወጣት የ13 አመት ብላቴና ይሆናል የሚል ግምት ከቶ አልነበረውም።

«ጋሽ ሰለሞን የልጅነቴን ልክ ቢያይ ኖሮማ -«አንቺማ ገና ነሽ ትንሽ እደጊ ባለኝ ነበር።» ሲል ደምሴ ባንድ ወቅት የተናገረውም ለዚህ ይመስላል።

## ጨሎው ከንቲባ

የድሬዳዋው አማተር ጋዜጠኛ በኢትዮጵያ ሬድዮ ዘገባዎቹን ማቅረቡን ቀጥሏል። ዝነኛው አለቃውም ‹ተማሪ ደምሴ›፣‹ወጣቱ ደምሴ› እያለ ማስተዋወቁን አላቆመም። የደምሴ ስም በመላው ከተማ እየታወቀ በተለይ ደግሞ በድሬዳዋ ላይ እየገነነ ሄደ። . . . ድፍን አራት አመት።

ድንገት ግን አማተሩ የ17 አመት ወጣት ለመጀመሪያ ግዜ ከአለቃው ጋር በአካል የሚገናኝበት እድል ተፈጠረ።የመንፈስ መምህሩና ደቀመዝሙሩ ከፖስታና ከስልክ ውጪ ለአይነ ስጋ የሚበቁባት የመጀመሪያዋ አጋጣሚ።

ሰለሞን ድሬ ላይ በሚካሄድ አንድ የስፖርት በአል ላይ ተጋብዞ ለመገኘት ሲመጣ ደምሴ ከአየር ማረፊያ ሆኖ ነበር የተቀበለው ፦እንደደረሰም አማተሩ የፕሮፌሽናሉን ሻንጣ አፈፍ አርጎ ወደሚጠብቀው መኪና አደረሰለት።

ይሄኔ ነው ያለተጠበቀ ጉዳይ የተፈጠረው። ጋዜጠኛ ሰለሞን ሻንጣውን አፈፍ አድርጎ የወሰደለት ወጣት ተሸክሞ አዳሪ ስለመሰለው የተወሰኑ ብሮች ሸጉጦለት በሚጠብቀው መኪና እብስ አለ። ጉዞው ሃረርጌ እስፖርት መምሪያ ነበር፦ ዝምታን የመረጠው ደምሴም ታክሲ ይዞ ወደዚያው ተከትሎ ነጎደ።

ቢሮው ውስጥ ሲተያዩ ግን ሰለሞንን ሳይገርመው አልቀረም።

«አንቺ ጨሎ ቅድም ከፈለኩሽ አይደል? ለምን ተከተልሽኝ ታድያ?" ማለት።  ይሄኔ የስፖርት መምሪያው ሹም የሆኑ ሰው ጣልቃ ገብተው የደምሴን ማንነት ለመግለጽ ይገደዳሉ። ሰለሞን ይደነግጣል። ‹ከ4 አመት ዘገባ በኋላ ገና ወጣት ከሆነ መዘገብ ሲጀምር ምን ሊያክል ኖሯል?› በሚል ሃሳብ የተናጠ ይመስላል።

. . .ያኔውኑ ከቢሮ ወጥተው ወደ ገበያ ያመራሉ። የድሬ ሰው ዝነኛውን ዘጋቢያቸውን ባገኙት ቁጥር «ደምሴ" "ደምሴ»እያሉ በፍቅር መጥራታቸውን ያስተዋሉት የመምሪያው ሹም ታድያ፦

«አንተ በራዲዮህ ወጣቱ፣ተማሪው እያልክ ጥራው እንጂ፣ እሱ እዚህ ከንቲባ ደምሴ ነው የሚባለው» ሲሉ ለሰለሞን ሹክ ይሉታል።

ገበያ ሲደርሱ ካኔተራና ቁምጣውን አስወልቆ በህይወቱ ለመጀመሪያ ግዜ የለበሰውን ሙሉ ልብስ እንደገዛለት ስለተወዳጁ የትላንት አለቃው በስሜት የሚያስታውሰው ንጉሴ አውስቶ ነበር።

ወደ ገጽ 29 ዞሯል

# አቶ ተስፋ የሸዋሉል የቀድሞ የኢትዮጵያ ቅርጫት ኳስ ፌዴሬሽን ዋና ጸሃፊ

**ኢ.ቶ፡-** ጤና ይስጥልኝ አቶ ተስፋ የሸዋሉል! በቅድሚያ ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ ሆነው በመቅረብዎ በአንባቢያን ስም ከፍ ያለ ምስጋና ላቀርብ እወዳለሁ። እስኪ ለአንባቢያን ራስዎን ያስተዋውቁ አቶ ተስፋ የሸዋሉል ማናቸው?

**አቶ ተስፋ፡-** እኔም ስለተሰጠኝ ዕድል አመሰግናለሁ።ተስፋ የሸዋሉል እባላለሁ። ተወልጄ ያደኩት በአዲስ አበባ ነው። ሰፈሬም በአራት ኪሎና ቀበና መካከል ነው። አውስትራሊያ እስከመጣሁበት ግዜ ድረስ የኢትዮጵያ ቅርጫት ኳስ ፌዴሬሽን ዋና ጸሃፊ ሆኜ እሰራ ነበር፡፤ ወደዚህ ሃገርም የመጣሁት በዚሁ ሃላፊነት እየሰራሁ ሳለ ባገኘሁት ነጻ የትምህርት እድል ነበር፡፤ በአሁኑ ሰአት ባለትዳርና የሁለት ልጆች አባት ነኝ።

**ኢ.ቶ፡-** የኢትዮጵያ ቅርጫት ኳስ ፌዴሬሽን ዋና ጸሃፊ ለመሆን ብዙ ስፖርታዊ የሃላፊነት ጉዞዎች የግድ ናቸው። እስኪ ለዚህ ሃላፊነት ከመብቃትዎ በፊት በስፖርቱ አለም የነበርዎትን ቆይታና እንቅስቃሴ ቢገልጹልን?

**አቶ ተስፋ፡-** ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደሞከርኩት ትውልዴና እድገቴ በአራት ኪሎና ቀበና መካከል በመሆኑ የአካባቢው ወጣት በሙሉ ውሎው በዚሁ አካባቢ ይገኝ በነበረው ወወክማ (ወጣት ወንዶች ክርስቲያናዊ ማህበር) ነበር፡፤ በወወክማ በርካታ የስፖርት ልምምዶችና፤ ውድድሮች ይደረጋሉ። ቅርጫት ኳስ፤መረብ ኳስ፤ ጅዶ፤ ባድሜንተን፤ ቴብል ቴኒስ ቦክስ በመሳሰሉት ስፖርት አይነቶች ልምምዶችና ስልጠናዎች ይሰጡ ስለነበር የማህበሩ አባል የሆኑ ወጣቶች በፈለጉት የስፖርት አይነት መሳተፍ እድል ነበራቸው፡፡ እኔም የዚሁ እድል ተጠቃሚ በመሆን በቅርጫት ኳስ እሳተፍ ነበር፡፤ እንዲህ እንዲህ እያልን በስፖርቱ ጥሩ ችሎታ እያዳበርን ሄድን በግዜው የወወክማ ልጆች በየትኛውም ስፖርት አይነት ከፍተኛ ችሎታ የነበራቸው ነበሩ፡፤ ይህ በእንዲህ እያለ ደርግ ስልጣን ሲይዝ ወወክማውን አፈረሰው። ክርስቲያናዊ ማህበር የሚለው ከአይዲዎሎጂው ጋር ስለማይጣጣም ይሁን ወይም የወጣቶች መሰባሰብ በፈጠረው ስጋት ባላውቅም ደርግ ወወክማውን አልፈለገውም አፈረሰው።

በመሆኑም የወወክማ ወጣት በተለያዩ ስፖርት ክለቦች ገብቶ መወዳደር ጀመረ። እኔም በግዜው በድል ብርሃን ስፖርት ክለብ ገብቼ መጫወት ጀመርኩ፡፤ የድል ብርሃን ስፖርት ክለብ በሙሉ የወወክማ ልጆች ስለነበርን ከሌላው ክለብ ጋር በፍጹም የተመጣጠነ ጨዋታ ማድረግ ስላልተቻለ እንደገና ቡድኖችን አፍርሶ በድርጅቶች የታቀፉ አዲስ የቡድን መዋቅር መፍጠር አስፈለገ። እኔም በአዲሱ መዋቅር የሼል ክለብን ተቀላቀልኩ። ሼል ክለብ እነ አካለወልድ መኩሪያ ዘሪሁን ቢያድግልኝ አይነት ጠንካራ ተጫዋቾች የነበረው ቡድን ነበር።



አቶ ተስፋ የሸዋሉል የቀድሞ የኢትዮጵያ ቅርጫት ኳስ ፌዴሬሽን ዋና ጸሃፊ

እንደነገርኩህ ወወክማ እያለን በብዙ አይነት ስፖርት የመሳተፋ እድል ስለነበር ሁሉም ተጫዋች ቢያንስ ሁለትና ከዚያ በላይ በሆነ የስፖርት አይነት ችሎታ የነበረው ነው፡፤ ከፍ እያልክ ስትመጣ ነው አንዱን መርጠህ የምትይዘው፡፤ እኔም ከቅርጫት ኳስ በተጨማሪ እግርኳስና እጅ ኳስ እጫወት ነበር። በእግርኳስ በክለብ ደረጃ ለአንበሳ ቢ ተጫውቻለሁ በእጅኳስም በሼል ቡድን ውስጥ ተጫውቻለሁ፡፤ ለብሄራዊ ቡድንም አንዴ የመሰለፍ እድል አጋጥሞኝ ነበር። እዚህ ጋ አንድ ከእጅ ኳስ ጋር ያቆራረጠኝን አጋጣሚ ልንገርህ፡፤ ብሄራዊ ቡድናችን ከጀርመን ጋር ሲጫወት እኔ በሪዘርቭነት ጨዋታ እያየሁ ነበር። በረኛው ጉዳት ደረሰበትና እኔ እንድገባ ተደረገ ብዙም ሳልጫወት አንድ የጀርመን ተጫዋች አክርሮ የሰደዳትን ኳስ ሳልይዛት ፊቴ ላይ አረፈች፡፤ ከዚያ ድብልቅልቁ ወጣብኝ ህብረ ቀለማት ....ራሴን ሳትኩ፡፤ ከዚያ ቀን በኋላ ጎመን በጤና ብዬ በቅርጫት ኳስ ላይ ረግቼ ቀረሁ።

ወደ ቅርጫት ኳስ ስመለስ እንዳልኩህ ሼል ቡድን በሃገሪቱ ከፍተኛው ቡድን ነበር፡፤ በተደጋጋሚ ሻምፒዎን የሆነ እነ ተስፋዬ ጃንጋን አይነት ድንቅ ተጫዋቾች የያዘ ቡድን ነበር። ተስፋዬና ዘሪሁን ቢያድግልኝ እንዲሁም ፍቅሬ ለጥይበሉ ለኢትዮጵያ እጅ ኳስ ስፖርት መሰረት የጣሉ ስፖርተኞች ነበሩና በዚህ አጋጣሚ አመስግኜያቸው ማለፍ እሻለሁ፡፤ሼል እየተጫወትኩ ለረዥም ግዜ ባይሆንም ብሄራዊ ቡድን ገብቼ ለመጫወት ችያለሁ፡፡ የስፖርት አለም የተጫዋችነት ቆይታዬ ከብዙ በጥቂቱ ይህን ይመስላል።

**ኢ.ቶ፡-** ወደ ስራው አለም እንመለስና፡- የኢትዮጵያ ቅርጫት ኳስ ፌዴሬሽን ጸሃፊ ማለት በቅርጫት ኳስ ስፖርት የመጨረሻው የሃላፊነት እርከን ማለት ነውና ለዚህ ሃላፊነት ከመብቃትህ በፊት ምን ነበር የምትሰራው?

**መልስ፤-** ስራ የጀመርኩት በ1970 እ.ኢ.አ ነው። መስሪያ ቤቱም የስፖርትና አካል ማሰልጠኛ ኮምሽን ነው። በግዜው ክቡር አቶ ይድነቃቸው ተሰማ ዋና ኮሚሽነር ነበሩ አቶ ጸጋው አየለ ምክትል ኮምሽነር ነበሩ።

ስሙ እንደ ሚያመለክተው የአካል ማሰል ጠኛና ስፖርት ኮሚሽን በግንባር ቀደምነት የሚሰራው ጤነኛ ዜጋ ለማፍራት የአካል እንቅስቃሴ ወይም ጅምናስቲክ ለመላው ህዝብ በትምህርት ቤት ለተማሪው በገጠር ለገበሬው በየፋብሪካው ለሰራተኛው ማዳረስ ነው፡፤ የስፖርት ውድድር በሁለተኛ ደረጃ የሚሰራ ነው፡፤ ተግባራዊነቱ ላይ ብዙም የተሳካ አልነበረም፡፤እቅዱ ጥሩ ነበር።

እንግዲህ ይህ አዲስ እቅድ ተነድፎ ወደ ተግባር ለመለወጥ እንቅስቃሴ ሲጀመር በየክፍለሃገሩ በመሄድ ስልጠና የሚሰጡ በተለያዩ ስፖርቶች ልምድ ያላቸው ሰዎች ያስፈልጉ ነበርና በተለይ በወወክማ ያደግነው ወጣቶች እድሉን ለማግኘት ብዙም አልተቸገርንም።

ይህ በእንዲህ ቀጥሎ በየክፍለሃገሩ እየዞርን የስፖርት ህጎችን በማስተማር ልዩልዩ ስልጠናዎችን በመስጠት የውድድር አመራርና እቅድ አወጣጥን በማስተማር ለሁለት አመት ያህል መሰረት የመጣሉን ስራ ስንሰራ ቆየን።

በ1972 ዓመት ምህረት ላይ ይህ ከአዲስ አበባ እየተንቀሳቀሱ በየክፍለሃገሩ ስልጠና የመስጠቱ ተግባር በቋሚነት እንዲቀጥል በየክፍለሃገሩ የስፖርት ኮሚሽን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ለመክፈት እቅድ ወጣ፡፤ እንደ ሙከራም በመጀመሪያ በሁለት ክፍለ ሃገሮች የስፖርትና አካል ማሰልጠኛ ኮምሽን ጽ/ቤት እንዲከፈት ተደረገ፡፤

ከሁለቱ አንዱ ወሎ ነበር፡፤ እዚያም የክፍለ ሃገሩ የስፖርት ኮሚሽን ተጠሪ ሆኜ የተመደብኩት እኔ ነበርኩ፡፤ ይህ እንግዲህ ከፍተኛ የሆነ የስራ ሃላፊነት ነው። ከዚያ በፊት ከቦታ ቦታ እየዞርን በግሩፕ የምንሰራው ስራ ስለነበር ብዙም ፈታኝ አልነበረም።

ሁሉንም የስፖርት እንቅስቃሴ የመምራት ሃላፊነት ከባድ ነው። በዛም ላይ ወሎ ውስጥ ቀደም ሲል የተፈጠረ ችግር ስለነበር እሱንም ማስተካከል ሌላው ሃላፊነቱን ያከበደው

ጉዳይ ነበር። የሆነው ሆኖ ወጣትነቱም የመስራት ፍቅሩም ስለነበር እንቅስቃሴውን ጀመርን፡፤ በ1974 ዓመተ ምህረት የኢትዮጵያ ትቅደም ዋንጫ ማዘጋጀቱን ከፍተኛ ሃላፊነት በስሬ ከነበሩ 18 የኮሚሽኑ ሰራተኞች ጋር ሆኜ በጥሩ ሁኔታ ተወጣን፡፤ ወሎም በውድድሩ ሻምፒዮን ሆኖ አስደሰተን፡፤

በሚቀጥለው አመት የኢትዮጵያ ሻፒዮና ውድድር ጅማ ላይ ሲደረግም የወሎን ምርጥ ወደ ጅማ ይዤ ሄጄ በግዜው የወሎ ምርጥ ቡድን ተጫዋቾች በነበረው በኋላ የብሄራዊ ቡድናችን ኮከብ ተጫዋቾች ሙሉጌታ ከበደ ድንቅ ጨዋታ በጅማም ድጋሚ ሻምፒዮን ሆንን፡፡ በቀጣይ አመ ትም በጎጃም ተደርጎ ወሎ ምርጥ ለሶስተኛ ግዜ ሻፒዮን ሆነ፡፤ ትዝ ይለኛል ጎጃም ላይ ውድድር ከመጀመሩ በፊት ነፍሱን ይማረውና ተወዳጁ የስፖርት ጋዜጠኛ ደምሴ ዳምጤ ወደ ወሎ ቡድን ጠጋ ብሎ "ወሎዎች ዘንድሮስ የጅማው ድል ይደገም ይመስላችኋል?" ብሎ ሲጠይቀኝ፣ የሰጠሁት መልስ 'ጊቤን የተሻገረ ዋንጫ አባይን አያቅተውም" የሚል ነበር። እንዳልኩትም ተሳካልን። ሙሉጌታ ከበደ ለብሄራዊ ቡድን የታጨው ለወሎ ምርጥ ባደረገው ድንቅ እንቅስቃሴ ነበር።

በወሎ የስፖርት ኮምሽን ተጠሪ ሆኜ በሰራሁት ሥራ ሁሉ እኮራለሁ። ሕዝቡም በጣም የሚያስደስት ደግ ተባባሪና ቀና ህዝብ ነው። እኛም በህዝብ ድጋፍ ብዙ ስራዎችን ሰርተናል። አስፋልት ሜዳ አልነበረም አሰርተናል ስቴድየም እንዲሰራም ከፍተኛ ጥረት አድርገናል። ይህ በእንዲህ እያለ ቡልጋሪያ ለ7 አመት የትምህርት እድል አገኘሁና ወሎን በፍቅር ተሰናብቼ ከፍተኛ አሸኛኘት ተደርጎልኝ ወደ አዲስ አበባ መጣሁ።አዲስ አበባ መጥቼ ወደ ቡልጋሪያ ለመሄድ ስዘጋጅ በሆነ ምክንያት እድሉ ተሰረዘ ተባልኩ። ትንሽ ተበሳጨሁ፡፤ በግዜው ኮምሽነር የነበሩት ጸጋው አየለ ቀጣይ እድል ሲመጣ እንደሚሰጠኝ ቃል ገብተውና አጽናንተው ወደ ስራዬ እንድመለስ አግባቡኝ።

ወደ ስራዬ ለመመለስ ፈቃደኛ ብሆንም ተሸኝቼ ወደ ወጣሁበት ወደ ወሎ ለመመለስ ግን አልፈለኩም። እናም የኢሊ ባቡር ተጠሪ ሆኜ ሄድኩ እዛም እንደወሎ ባይሆንም መጠነኛ እንቅስቃሴ ሳደርግ ቆየሁ፡፡

ከኢሊባቡር ቀጥሎ የድሬደዋ ራስ ገዝ ተጠሪ ሆኜ ተሾምኩ። ድሬደዋ እየሰራሁ እያለሁ ያመለጠኝን የትምህርት እድል በተከታታይ አገኘሁ፡፤ በመጀመሪያ ሶፌት ህብረት የእጅ ኳስና ቅርጫት ኳስ አሰልጣኝነት ኮርስ ወስጄ ተመለስኩ። ቀጥሎም ጀርመን የስፖርት ማኔጅመንት ውድድር አመራርና ቡድን አወቃቀር ዲፕሎም ከዚያም በሃንጋሪ የባስኬት ቦል ከፍተኛ ደረጃ አሰልጣኝነት ኮርስ ወሰጀአለሁ፡፤

ዋናው ነገር የስፖርት ኮርስና ስልጠና ወስደህ ስትመጣ ትምህርቱ በቀጥታ ወደ ተግባር የሚለወጥና ከዕለት ተዕለት ስራህ ጋር የሚገናኝ ስለሆነ በጣም ትልቅ ልምድ ነው የምታዳብረው፡፤ የትኛውም የስፖርት አይነት በእቅድና በፕላን በተነደፈ ልምምድ ተጀምሮ የልምምዱ ውጤታማነትና የእቅዱ ስኬታማነት የሚለካው ደግሞ በውድድር በመሆኑ በእያንዳንዱ እስቴፕም ስራህን የመፈተሽና የመገምገም አጋጣሚዎች ስላሉህ በስራህ ሁሌም ትረካለህ። በስራህ ካልረካህ ደግሞ ችግርክን ለይቶ በማውጣት ለማረም ትሰራለህ።

በብዙ የሙያ ዘርፎች የሚታዩ ችግሮች ትምህርቱና ስራው ያለመገናኘታቸው ነው፡፤ ስፖርት ላይ ግን ይህ ችግር ስለሌለ በስፖርት አለም እንደ ስፖርተኛም ሆነ እንደ ቢሮ ሰራተኛ በቆየሁበት አመታት ሁሉ ደስተኛ ነበርኩ።

**በወሎ ስፖርት ኮምሽን ተጠሪ ሆኜ በሰራሁት ሥራ ሁሉ እኮራለሁ! ሕዝቡም በጣም የሚያስደስት ደግ፤ተባባሪና ቀና ህዝብ ነው።**

እንግዲህ ይህ ሁሉ ተዳምሮ ነው በመጨረሻ የኢትዮጵያ ባስኬት ቦል ፌዴሬሽን ዋና ጸሃፊነቱን ስፍራ ያገኘሁት፡፡ እንዳልከው ቦታው በኢትዮጵያ ቅርጫት ኳስ ረገድ ከፍተኛውና የመጨረሻው የሃላፊነት ቦታ ነው፡፤ ለዚህም ያበቃኝ በስፖርቱ ውስጥ የቆየሁበት ስራ ልምድና የወሰድኩት ስልጠና በተለይም በየክፍለሃገሩ የስፖርትና አካል ማሰልጠኛ ኮምሽን ሃላፊ ሆኜ የሰራሁት ስራ ተደማምሮ ይመስለኛል። እዚህም አገር የመጣሁት ለከፍተኛ ትምህርት ነበር፡፤ ይሁንና ተመልሶ መሄዱ ብዙም ስላልታየኝ እዚሁ ቀርቻለሁ፡፤

<u>**ኢ.ቶ**</u> አሁን ደግሞ እዚህ አውስትራሊያ ከመጣህ በኋላ የአውስትራሊያ ስፖርት ፌዴሬሽን ፕሬዘዳንት ሆነህ መስራትህን አውቃለሁ። ፌዴሬሽኑ አሁን አለ ወይ? ከሌለ ወይም ከተዳከመ ለማጠናከር ምን የታሰበ ነገር አለ?

<u>**አቶ ተስፋ፡-**</u> ርግጥ ነው የአውስትራሊያ ስፖርት ፌዴሬሽን ፕሬዘዳንት ሆኜ ሰርቻለሁ፡፤ ከፌዴሬሽኑ አመራር አባላት ጋር ሆነን በጣም የተዋጣለት ስራም ሰርተናል። ምን ሆነ መሰለህ፡- የኃላፊነት ግዜያችንን በጨረስንበት ወቅት የየስቴቱ ኮሚኒቲ አመራሮች ተተኪ እንዲያዘጋጁ በደብዳቤ አሳውቀን ነበር፡፤ እኛ በተመረ ጥንበት መንገድ ተተኪ ፌዴሬሽን እንዲቋ ቋምና እንዲረከቡን ነበር የጠበቅነው። ይሁንና ምንም ምላሽ ሳናገኝ ተተኪውም ሳይመረጥና ርክክብ ሳይደረግ ቆየ እኛም አልቀጠልንም ተተኪም አልተመረጠም። ይህ መሆኑ እንቅስቃሴውን አዳክሞታል፡፤ በመሆኑም እንደገና በጠንካራ መሰረት ላይ ማቋቋም አስፈላጊ መሆኑን አምነንበታል፡፤ በአሁኑ ሰአት የዘንድሮውን 16ኛውን ቶርናመንት በሜልበርን የኢትዮጵያን ኮሚኒቲ አስተባባሪነት እያዘጋጀን ነው።

በቀጣይ ግን ልክ እንደ ቀድሞው ከሁሉም እስቴቶች የተውጣጡ አባላት ያሉት ፌዴሬሽን ለማቋቋም አስፈላጊ የሆነውን ሁሉ ለማድረግ በኔ በኩል ሙሉ ፈቃድና ዝግጁነት አለኝ፡፤ የቀድሞ ፌዴሬሽን ጥቂት አባላቶች አሁንም አለን። ከየኮሚኒቲው አመራሮች ጋር ተመካክረን በጎደለው አሟልተን አዲስ ካስፈለገም አስገብተን በሚቀጥለው አመት ቶርናመንቱን የሚያዘጋጀው ፌዴሬሽኑ እንደሚሆን ተስፋ አለኝ፡፡

በሌላ በኩል ሳልገልጽ የማላልፈው ጉዳይ በአሰራር ረገድ የቡድን አወቃቀር የውድድር ዝግጅትና አመራር የራሱ የሆነ ህግና ደንብ አለው። ሁሌም ያንን ተከትሎ ወይም አክብሮ መስራትና ለህጉም ተገዢ መሆን ያስፈልጋል። ያለበለዚያ ሁሉም እንደ መሰለው ከተንቀሳቀሰ ዛሬ የምናቋቁመው ነገ መፍረሱ አይቀርም።

የተሰሩ ስህተቶች ሲኖሩ በግዜው አርሞና ተራርሞ መቀጠል እንጂ እየተወቃቀሱ መክረም ውጤት አያመጣም። እኛ በበኩላችን በበፊቱ እንቅስቃሴያችን ቅር ያሰኘናቸው ስቴቶች እንዳሉ ተረድተናል ስለሆነም ራሳችን ሄደን ይቅርታ ልንጠይቃቸው አስበናል። ከዚያ በኋላ በአዲስ መልክ በአዲስ መንፈስ አብረን ለመስራት ዝግጁ ነን፡፡

<u>**ኢ.ቶ**</u> ስለዘንድሮው ውድድርና ዝግጅት የሚነግሩን ነገር ካለ?

<u>**አቶ ተስፋ፡-**</u> ጠቅላላ የውድድሩ ፕሮግራምና የቡድኖች ዝርዝር በዚህ ሁለት ቀን ውስጥ ይሰራል በቅርቡ ታገኘዋለህ።አሁን ልነግርህ የምችለው 3 ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ስራዎችን ተከፋፍለን እየተንቀሳቀሱ መሆኑን ነው። ሁሉም የተሰጠውን ሃላፊነት እየተወጣ በመሆኑ ዝግጅቱ በታሰበው መሰረት እንደ ሚከናወን ላረጋግጥልህ እችላለሁ።

<u>**ኢ.ቶ**</u> በጣም አመስግናለሁ አቶ ተስፋ

እኔም ስለተሰጠኝ እድል በድጋሚ አመስግናለሁ።'——////——

# ይድነቃቸው በካድሬ . . .

[ከገጽ 9 የዞረ]

**መልስ፡-**ኢ.ኢ. በ1966ዓ.ም በእንግሊዝ ሃገር በተደረገው የዓለም ዋንጫ ውድድር ከአቶ ይድነቃቸው ተሰማ ጋር ሄጄ ነበር። የብሪታኒያው ጠቅላይ ሚኒስትር ዊልሰን እራት ጋብዘውን ሲቀበሉን በወሬ ወሬ ከኪሳቸው አውጥተው እርሳቸው የሚደግፉትን የጥንት ክለባቸውን ቡድን ፎቶግራፍ አሳይተውኛል። ደንበኞች የእግር ኳስ አፍቃሪዎች ግን ሔኔሪ ኪስንጀር የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የነበሩትና የፊያት አውቶሞቢል ፋብሪካ ባለቤት የነበሩት ጂዮቫኒ አፔሊ ናቸው ።ይልቁንም የኦሎምፒከን ጨዋታ የሚከታተሉ የስዊድን፣ የእስፔን፣ የኖርዌይ ንጉሦችና ነገሥታቶች ናቸው። ጃንሆይ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ሻምፒዮን ፍጻሜ ግጥሚያዎች፣ የአፍሪካ ዋንጫ፣ የትምህርት ቤቶች የአትሌቲክስ ውድድሮች ስታዲዮም በመግባት ይከታተሉ ነበር። ጃንሜዳም እየሄዱ የፈረስ እሽቅድምድም ይመለከቱ ነበር እስከ 1966። የኢትዮጵያ ብሔራዊ እግር ኳስ ቡድን በዳኛ ስህተት በግፍ ለኦሎምፒክ ጨዋታ ያለማለፉ ሲነገራቸው ግድ የለም በማለት ወጪያቸውን ችለው ቡድኑ ከኛ ጋራ እንዲሄድ የፈቀዱ ንጉስ ናቸው። ከብዙ የአፍሪካ መሪዎች ጋር ተገናኝቼለሁ ሁሉም ኳስ ጨዋታን እንደ ፖለቲካ



**አቶ ፍቅሩ ኪዳኔ ከፕሬዘንዳንት ኔልሰን ማንዴላ ጋር በደቡብ አፍሪካ ኬፕታውን 1995**

መሳሪያ ለመጠቀም በመፈለግ በጣም ቸር ይመስላሉ። ኔልስን ማንዴላን የመሰለ መሪ ጭራሽ እዚህ ዓለም ውስጥ የለም። ማንዴላ ከእግር ኳስ ይልቅ ቦክስ ነው የሚወዱት ።

**ጥያቄ፡-**ከኛስ አገር ባለስልጣናት መሀል ልዩ የሆነ የእግር ኳስ ፍቅር የነበረው ያስታውሳሉ? የኳስ ፍቅር ስላልነበረው ለጥረታችሁ ዕንቅፋት የሚያበዛስ?- ከትዝታዎ ቢያካፍሉን?

**መልስ፡-**ከእኛ ሃገር ባለስልጣናት በተለይ ከጦር ሃይል የተውጣጡ መኮንኖች የስፖርት ኮንፌደሬሽን ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባል በመሆን አገልግለዋል። ለብዙ ዓመታት የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌደሬሽን ፕሬዘዳንት የነበሩት ክቡር ኮለኔል ታምራት ይገዙ ነበሩ። አንድ ሰሞን እስከ ሰባት ሚኒስቴሮች የፌደሬሽኑ አባል ነበሩ በኛ ግዜ ሁሉም ባለስልጣናት ይተባበሩን ነበር ።

**ጥያቄ፡-**በአገራችን የእግር ኳስ ታሪክ በተለያዩ ምዕራፎች ይህ ነው የሚባል ችሎታ የነበራቸው ተጫዋቾች ታይተዋል። በተለይ ግን መንግስቱ ወርቁ ድንቅ ነበር በሚል ዛሬም ድረስ የሚናገሩ ሰዎች ብዙ ናቸው። እስቲ ስለመንግስቱ ጥቂት ትውስታዎችን ያካፍሉን?

**መልስ፡-**ብዙ ጊዜ የኳስ ቲፎዞ የሚያስታውሰው ጎል የሚያገባውን ተጫዋች ነው እንጂ ተከላካይ ወይንም በረኛውን አይደለም። በዚህ የተነሣ መንግስቱ ወርቁ ታዋቂ ሆኗል። ግን ከሱ የሚያንሱ ድንቅ ተጫዋቾች ነበሩ ። ነፀረ ወልደስላሴ ፣ከበደ መታፈሪያ ፣ ብርሃኔ አስፋው ፣ጻጋዬ በቀለ ፣እልፍአግ ጎበና፣ፒኮ ፣ኢታሎ ፣ወዘተ... መሃል አከፋፋይ ሊቻኖ ቫሳሎ ፣ልኡልሰገድ በቀለ ፣ፍስሃ ወ/አማኑኤል ፣አዳሙ ዓለሙ ከተከላካይ አዋድ መሃመድ ፣ አየለ ተሰማ ፣ ( ጆቦ ) ነጋሽ ወ/ጊዮርጊስ ፣ አብረሃ ባህሩ ፣ አዳል ተከለስላሴ ( ድሬ )የመሳሰሉ ነበሩ። ለማንኛውም አንድ የእግርኳስ ቡድን አስራአንድ ተጨዋቾች ያሉበት ነው። የሚገኘው ውጤት በአስራ-አንዱ ብርታት መኋኑን መርሳት አይገባም ።ኢ. ኢ. በ1960 ዎቹ ውስጥ በአዲስ አበባ .አስመራ ድሬደዋ የነበሩት ቡድኖች በጣም ተወዳዳሪዎች ስለነበሩ ሻምፒዮናው ለዛ ነበረው ብሔራዊ ቡዱኖቹም በአፍሪካ ደረጃ ተፎካካሪ ነበሩ ።

**ጥያቄ፡-**እንደ ቡድንስ ጠንካራ ቲም የነበረን በየትኛው ዘመን ነው ይላሉ? የጥንካሬውን ልክስ በንጽጽር እንዴት ይገልጹታል?

**መልስ፡-**ከሃገሬ ከወጣሁ 36ዓመት ስለሆነኝ ካሁኑ ሁኔታ ጋር ለማስተያየት ያስቸግረኛል። ያው የራሴ ክለብ ቅዱስ ጊዮርጊስ አሁን ከሚጨወቱት ቡድኖች አንዱ ነው እኔን የሚያሳዝነኝ ግን በሃገራችን ተጫዋቿች ማፍራት አቅቶን የኔው ክለብ ከውጭ ሃገር ተጨዋቿች ቀጥሮ ማስመጣቱ ነው ።

**ጥያቄ፡-**አብዛኞቹ የአፍሪካ መሪዎች አምባገነኖችና በብስለታቸው ሳይሆን ‹ጡንቻቸውን› በማፈርጠማቸው ብቻ ለገዢነት የበቁ መሆናቸው ነው ሲመሰከር የኖረው። እርሶስ የስራዎ ጸባይ በፈጠረሎት ዕድል ቀርበው ካወያዩአቸው ወይም ታሪካቸውን በቅርብ ከሚያውቋቸው መሪዎች መሀል የግንዛቤው አናሳነት በእጅጉ ያስገረሞትና “ዕውን ይህም ሰው አገር ይመራል?” ያሰኞት ሰው ይኖር ይሆን? ከአቻዎቹ በተለየ የላቀ ራዕይ የሰነቀ ፣ በሳልና ሩቅ ተመልካች ሆኖ ያገኙትስ ማንን ይሆን? ጥቂት የሚያወጉን ቢኖር?

**መልስ፡-** ላገራቸው ነጻነት የታገሉትና የተዋጉት ሁሉ ሥልጣን ላይ ጉብ ካሉ በኋላ በጣም የሳባቸው ዲሞክራሲ ሳይሆን ዲክታተሪዝም ነው።ከኩዋሜ ንክሩማን ጭምር። ከዚያም የሚሊቴሪ ኩዴታ አሃጉሩን አናጋው ይህም ሆኖ ከሴንጎር ጊዜ ጀምሮ በዲሞክራሲ የተጠቀመች ሃገር ሴንጋል ብቻ ነች። እኔ የማከብረው ኔልሰን ማንዴላን ቢሆንም በምርጫ ተሸንፈው ሥልጣን በሰላም ያስረከቡትን የሴኔጋሉን መሪን አብዱ ዲዮፍን አደንቃለሁ። ከዚያም የስልጣን ጊዜያቸውን ፈጽመው በሰላም የተሰናበቱና የአፍሪካ ሕብረት ኮሚሽን ፕሬዘዳንት ሆነው ያገለገሉት የማሊው ተወላጅ ዓልፍ ኡማርኮናሬ እንዲሁም የካፕቬርድ ሳዋቶሜ ኢፒሪንጋን ጋና ቦትስዋና ሞዛምቢክ ሞሪሺየስ መሪዎች የሚከበሩ ናቸው ።

**ጥያቄ፡-**እስቲ ደግሞ ጋሽ ፍቅሩ ከስፖርቱ ወጣ እንበልና “የፒያሳ ልጅ” በተሰኘው ተወዳጁ መጽሃፍዎ ውስጥ ከበአሉ ግርማ ጋር አብሮ አደግ እንደነበሩ ፣ ጳውሎስ ኞኞ ደግሞ ኳስ እንደማይወድ ጠቀስ አድርገው ነበር። እንደው በዚህ አጋጣሚ የነዚህን ተወዳጅ ሰዎች ቀዳማይ ስብዕና ለማወቅ እንዲረዳን ከትዝታዎ ቢያቋድሱን?

**መልስ፡-**በዓሉ ግርማ እንደኔ የጉለሌ ልጅ ከመሆኑም በላይ አጥር ብቻ የሚለየን ጎረቤቶች ነበርን። እሱ ግን ልዕልት ዘነበወርቅ ት/ቤት አዳሪ ስለነበር ወደ ቤቱ የሚመጣው በሳምንቱ መጨረሻ ላይ ነው እኔ ደግሞ የምማረው ተመላላሽ ሆኜ ሊሴ ገ/ማሪያም ነበር። እሱ የእንግሊዝ ተማሪ እኔ የፈረንሳይኛ ። ቅዳሜ ቅዳሜ ጉለሌ ወንዝ ውስጥ ውሃ ዋና ከዚያም ጣሊያን ጀምሮ ባልፈጸመው ራስ ደስታ ሆስፒታል አጠገብ በሚገኘው የካቶሊክ ቤተክሪስቲያን ሜዳ ላይ

በጨርቅ ኳስ ወይንም ኀፈሬው ባለቀ የቴኒስ ኳስ መጫወት ነው። ሳንቲምም ካለችን ወደ መስፍን ሐረር መንገድ ብቅ ብሎ ሽሪፍ ቤት ፓስቲ መብላት ነው። በዓሉ ግርማ ታዋቂ ኢትዮጵያዊ ነው። በግፍ የተገደለ መሆኑን ሁሉም ያውቃል። እኔ ከማስታወቂያ ሚኒስቴር ለቅቄ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከሆንኩ በኋላ በዓሉ ነበር ጋዜጠኛ ሆኖ ማገልገል የጀመረው። ጳውሎስ ኞኞ ግን አብረን ባንሰራም በማስታወቂያ ሚንስቴር የሚታተሙ ጋዜጦች ሁሉ የስፖርት ዓምድ እንዲኖራቸው በምታገልበት ወቅት የማይደግፍ እሱ ብቻ ነበር። ለኳስ ጨዋት ንቀት ነበረው ለፊኛ ጥለዛ ስፍራ መስጠት ግፍ ነው ይል ነበር። ዳሩ ግን እሱም የፒያሳ ልጅ ስለነበር በሚገባው ቋንቋ እመልስለት ነበር። ጳውሎስ ኞኞ ያው በሃገራችን የታወቀ ትልቅ ደራሲ ነው።ሁሉም በየፊናው የሚወደውና የማይወደው ነገር አለ ።

**ጥያቄ፡-**“የፒያሳ ልጅ” የሚለው መጽሀፍዎ እዚህ አውስትራሊያ ሳይቀር ከፍተኛ ተወዳጅነትን አትርፏል። ቀሪ ትዝታዎችዎን የምንቋደስበት ቀጣይ ስራስ የለም እንዴ? ካለስ መቼ እንጠብቅ? በተለይስ በየትኛው ዘመንና በምን ዓይነት ነጥቦች ዙርያ እንደሚያጠንጥን ጠቆም ሊያደርጉን ይፈቅዳሉ?

**መልስ፡-**የፒያሳ ልጅ መጽሃፍ ለሦስተኛ ግዜ ታትሞ ተሸጦ አልቋል። ያውም ምንም አይነት ፐብሊሲ ሳይደረግለት። በአጼ ምንሊክ አዋጅ መሰረት የሰማ ላልሰማ ያሰማ ሥነስረአት ተጠቅሜያለሁ። የመሶሎኒን ፋሽሽት ጦር ከሃገራችን ካስወጣን በኋላ ወጣቱ ትውልድ ምን ዓይነት ኑሮ እንደነበረው ባጭሩ የሚገልጽ መጽሃፍ ነው። አውስትራሊያ እንደ ዓለም መጨረሻ ነበር የምንቆጥረው አዲስ አበባ የተተከለውን ባህር - ዛፍ በአጼ ምኒልክ ግዜ ከአውስትራሊያ ያመጣው ሞንዶን-ቮዲዮ የተባለ ፈረንሳዊ ተወላጅ መሆኑን ሊሴ ተምረናል። ከዚህ በቀር በጃንሆይ ግዜ ክቡር ዘበኛ የሚጠቀምባቸው ፈረሶች ከአውስትራሊያ የተገዙ መሆናቸውን እናውቃለን። እዚያ ድረስ ሄደው የገዙት ኮለኔል ኮስትሪፍ ቦጎሲያን የኢትዮጵያ ስፖርት ኮንፌደሬሽን ገንዘብ ያዥ የነበሩትና ኢ.ኢ.ኢ. በ 1956ዓ.ም በሚልበርን ኦሎምፒክ ጫወታ የኢትዮጵያን ዴሌጋሲዮን የመሩት ናቸው። የኛ ትውልድ የሃገራችንን ባሃል በመከተል ራሱን በራሱ ለማስተማር ሃገራችንን ለማበልጸግ ታታሪ ነበር የአሁኑ ትውልድ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታነጸ ስለሆነ በሁሉም ረገድ ከኛ የተሻለ ሁኔታ ውስጥ ነው ።

እኛ የነበረን ሐብት ክብራችን ነበር። ከኛም መወረስ የሚቻለው ጨዋነትና ራስን የማስከበር በሃል ነው። ጋዜጣ ላይ አንድ ኢትዮጵያዊ ወይንም ኢትዮጵያዊት ተወላጅ ይሄ ወንጀል ፈጸመ/ች ተብሎ ስናነብ አሁንም እናፍራለን አሁንም ኩሩነን ። ስለኢትዮጵያ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች ብዙ መጽሃፍ ታትመዋል። እነኚህን መጽሃፎች የሃገራችን ህዝብ አያውቃቸውም ባይሆን እኔ ካነበብኳቸው ውስጥ በእንግሊዝኛ በፈረንሳይኛ በጣሊያንኛ በስፓኒሽ የተጻፉ አሉ። በነገራችን ላይ እነኚህን ቋንቋዎች ሁሉ የተማርኩት ሃገር ቤት ነው። ጥሩ ጥሩውን በተለይ አስቂኝ የሆነውን አረፍተ ነገር በመተርጎም ከልዩ ልዩ ሰነዶችና ማስረጃዎች ጋር የኢትዮጵያ ታሪክ በሚል አርእስት ለማሳተም ሃሳብ አለኝ ።

ፍላጎቴ ያገሬ ሕዝብ የጥንት ታሪኩን እንዲረዳ ነው። ነገር ግን አሁንም ኮንሳልታንት ሆኜ ስለምሰራና ሽምግልና ስለተጫነኝ መጓተትን አስከትልዋል። ከዚህ በቀር ስፖርትና ፖለቲካ የሚል በፈረንሳይኛ ተጽፎ በእንግሊዘኛና በሌላ ቋንቋዎች የሚተረጎም መጽሃፍም እያዘጋጀሁ ነው። የፍርድ ቤት ቀጠሮ ስለሌብኝ ደስ እንዳለኝ ነው የምሰራው ግዴታና መቻኮል የለም ።

**ጥያቄ** ጋሽ ፍቅሩ እስቲ አሁን ደግሞ ጥቂት ስለ አኗኗር ዘይቤዎ እናንሳ። የመኻታ ሰዓትዎ እንዴት ነው? ቤተሰብስ?...ከሃገር አገር መዞሩ ሲቆም ቤት ውስጥ መቀመጥን እንዴት ተላመዱት? ግዜዎንስ በምን ያሳልፋሉ ጤንነትዎስ?

**መልስ** ሰባ (70) ውስጥ የሚዋኝ ሽማግሌ ከአምስት ሰዓት በላይ መተኛት አይችልም ሲዩስታ ማድረግ ግን አለበት ከዚህ የተነሳ አስራ-አንድ ሰዓት ላይ ተነስቼ በፈረንሳይኛ ስለአፍሪካ ወሬ እሰማለሁ ቀጥሎም መድሃኒቶቼን ውጬ ኔስ ፐሪስ ቡናዬን እጠጣና ከኮምፑዩተሬ ጋር ሰላምታ እንሰጣጣለን። ወሬና ቀልዶች ካሉኝ በመላው ዓለም ለሚገኙ ጓደኞቼ እልካለሁ ከዚያም ተጣጥቤ ወደ ሦስት ሰዓት ላይ ወደ ጎረቤቴ ቡና ቤት ሄጄ አንድ የስፖርት ሁለት የግራና የቀኝ የፖለቲካ ደጋፊዎች የዝርዝር ወሬ ጋዜጦች አነብና ወደ ቤቴ እመለሳለሁ። ስሰራ ውዬ ለምሳ ወደቤት እመለሳለሁ ወይንም ራሴ እቤት አብስዬ እመገባለሁ ከዚያ ቢያንስ አንድ ሰአት ሲዩስታ አደርጋለሁ በወር ቢያንስ አንድ መጽሃፍ አነባለሁ።

በተለይ አዲስ አበባ ስሄድ የምገዛቸውን የአማርኛ መጽሃፍቶች አነባለሁ።ሥራዬ ብዙ ግዜ ወደ አፍሪካ ስለሚወስደኝ በተቻለ መጠን በአዲስ አበባ ለማለፍ እሞክራለሁ የኢትዮጵያ አየር መንገድ አፍሪካን ያካልላል። ቁርጥና ክትፎ ስለምወድ ነው መሰለኝ ዋጋውን ከፍ ያደረጉብኝ ። በአንድ ብር ቅቤ ውስጡ ይዋኝ የነበር። ክትፎ እበላ የነበረው ሰውዬ በመጨረሻ የከፈልኩት መቶ ሃያ ብር ነው ራሴን ለማታለል በዩሮ መመንዘር ጀምሬአለሁ። የፓሪስ ኑሮ በሥራ ፣ ንባብ፣ ቴሌቬዥን ፣ ሙዚቃ ቲያትር ፣ ሲኒማ የተከበበ ነው። ልጄ ከኔ ጋራ ሲድኒ ለኦሎምፒክ ጨዋታ የነበረውና ሁለቱ የልጅ ልጆቼ ( የ 19 እና 15) ዓመት እድሜ የሚኖሩት ቤልጊክ ሃገር ሊዬዥ ከተማ ውስጥ ነው። ወንዱ የልጅ ልጄ ከኔ ጋራ ቤዢንግ ኦሎምፒክ ጨዋታ ላይ የነበረው የዩንቨርስቲ ሁለተኛ ተማሪ ነው። መላው ቤተሰቤ እ.አ.አ በ 1998 ዓም በፓሪስና በ2006 ዓም በጀርመን ኮለን ከተማ የተደረጉትን የዓለም ዋንጫ የእግር ኳስ ውድድሮች ተመልክተዋል። እኔ የዓለም ዋንጫ እ.አ.አ ከ1966 ዓ.ም ጀምሬ እስካሁን እከታተላለሁ እ.አ.አ. በ 1982 ዓ.ም አውስትራሊያ የሄድኩት ለአለም የወጣቶች የእግር ኳስ ሻምፒዮን ነበር። ለማንኛውም ከሃገር ቤት ርቆ መኖር መቆጨት አይቀርም። የመፃፍ የመናገር ባጠቃላይ የነጻነትን ኑሮ የለመደ ምርጫ የለውም።




ኒዎርክ የኦሎምፒክ ትሩስ ፋውንዴሽን ስብሰባ ከግራ ወደ ቀኝ ፍቅሩ ኪዳኔ የፋውንዴሽኑ ጸሃፊ፤ አቶኒዮ ሳማራንች የኢንተርናሽናል ኦሎምፒክ ኮሚቴ ፕሬዘዳንት ፤ ኮፊ አናን የተ.መ.ዋና ጸሃፊ ጆርጅ ፓፓንድሪው የግሪክ ውጭ ጉዳይ ሚ.ር እ.አ 2001

**ጥያቄ፤-** በመጨረሻም በአውስትራሊያ ላሉ ኢትዮጵያዊያን የስፖርት አፍቃሪዎች የሚያስተላልፉት መልዕክት ካሎት?

**መልስ፡-**አውስትራሊያ እሩቅ ነው የሃገሬ ሰው እንዲህ ተበታትኖ ማየቱ ሁሌም ያሳዝነኛል። በአንድ በኩል ራሳቸውን ችለው ባህላቸውን ጠብቀው መሃበር አቋቁመው መኖራቸው ደግሞ ያኮራኛል። ስፖርትን የመሰለ ሁሉን የሚያቀራርብ የለም አውስትራሊያም ልክ እንደሰሜን አሜሪካና አውሮፓ የእግር ኳስ ውድድር ማዘጋጀትዋ አስደሳች ነው። ከዚያም ያሉ ወጣቶች መዝናኛቸው ስፖርት መሆኑ ንቃታቸውን ያሳያል።

በአውስትራሊያ ለሚኖሩት የሃገሬ ተወላጆች የከበረ ሰላምታዬን አቀርባለሁ ። በሜልበርን ከተማ የሚኖረው አብሮ አደጌ የፒያሳ ልጅ ሐንስ ሔስ እና የመቻል ተጫዋች የነበረውን ወንድሙ በቀለንም አልረሳኋቸውም ።በወጣቶች የዓለም ዋንጫ ውድድር ግዜ በአድላይድ ከተማ የፊፋ ተጠሪ ሆኜ ባገለገልኩበት ወቅት ያስተናገዱኝ ያገሬ ሰዎች አስታውሳለሁ። ..............///................

**ሜልበርን ነዋሪ ከሆኑ በኢትዮጵያ ስፖርት ታሪክ ጉልህ አሻራ ካሳረፉ ስፖርተኞቻችን መካከል ሳህሉ መኩሪያ አንዱ ነው። ሳህሉ መኩሪያ በቦክስ ስፖርት ከተወዳዳሪነት እስከ ብሄራዊ ቡድን አሰልጣኝነት የተጓዘ፤ እንደ ተወዳዳሪ ከፍተኛ ውጤት የነበረው እንደ አሰልጣኝም ብዙዎችን ለውጤት ያበቃ ባለውለታ ስፖርተኛ ነው። ኢትዮ ቶርናመንት ከሳህሉ ጋር ጥቂት ቆይታ አድርጋለች፤ እንሆ:-**

**ኢ.ቶ** ጤና ይስጥልኝ ሳህሉ፤ በቅድሚያ ስለግዜህ በጣም አመሰግናለሁ፡ ቦክስ መቼ ጀመርክ? በውስጡስ የነበርህን ቆይታ? ለአንባቢያን ዘርዘር አድርገህ ብትገልጽልን።

**ሳህሉ፡-**እኔም ስለተሰጠኝ እድል በጣም አመሰግናለሁ፡፤ቦክስ የጀመርኩት እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1972 ነው።በመጀመሪያ ፖሊስ ክለብ በኋላም ከ1975 ጀምሮ ህንጻ ኮንስትራክሽን ነበር የምጫወተው፡፤ የምጫወትበትም ኪሎ መጀመሪያ 63 ኪሎ ብኋላም 67 ነበር፤፡ በሃገር ውስጥ ባደረኳቸው ውድድሮች ለ9 አመታት በተከታታይ የኢትዮጵያ ሻፒዮን ሆኛለሁ።በጀመሪነት ግዜ ከተሸነፋኩበት አንድ ውድድር በስተቀር በሃገር ውስጥ ተሸንፌ አላውቅም።

ኢትዮጵያ ውስጥ በተደረጉ ኢንተርናሽናል ውድድሮች 2 ግዜ የወርቅ ሜዳል አግኝቻለሁ፡፡ በአራተኛው የምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ ውድድር ኬንያ ላይ የብር ሜዳል፤ ጀርመን አገር ሰባት ግዜ ሄጃለሁ በሁለት ከፍተኛ ውድድሮች የነሃስ ሜዳል አግኝቻለሁ። ኡጋንዳ ላይ



ሳህሉ መኩሪያ አስልጥኖ ለድል ካበቃው ኒክ ቲምላተስ ጋር

እንዲሁ የነሃስ ሜዳል አግኝቻለሁ፡፤ባጠቃላይ በሃገርም በውጭም ከመቶ በላይ ውድድሮች አድርጌያለሁ። በጥቂቶቹ ብቻ ነው መሸነፍን ያየሁት።ለ10 አመታት ያህል በተወዳዳሪነት ቆይቼ በ1982 ነው ያቆምኩት።

**ኢ.ቶ** ተወዳዳሪነቱ ካቆም በኋላስ ህይወት እንዴት ቀጠለ?

**ሳህሉ፡-**ይገርምሃል በዛው አመት ለአሰልጣኝነት ኮርስ ወደ ጀርመን አገር የመሄድ እድል አግኝቼ ሄድኩ።ኮርሱን ጨርሼ ከመጣሁ በኋላ 18 አዳራሽ በግል ማሰልጠን ጀመርኩ። ኒያላ ስፖርት ክለብም አሰለጥን ነበር። አዲስ ከተማ ወወክማም እንዲሁ አሰለጥን ነበር፡፤ የተለያዩ ቦታዎች እያሰለጠንኩ ብሄራዊ ቡድንም እየተጠራሁ አሰለጥን ነበር።በመጨረሻም ለሲዲኒ ኦሎምፒክ ብሄራዊ ቡድኑን ይዤ መጥቼ አልተመለስኩም።

**ኢ.ቶ** የአሰልጣኝነት ዘመንህ እንደተወዳዳሪነትህ የተሳካና ድንቅ ነበር?

**ሳህሉ፡-**መቼም አንድ አሰልጣኝ የሚመዘነው ያሰለጠናቸው ልጆች በሚያስመዘግቡት ውጤት ነው። በዚህ ረገድ እነ ሲሳይ፤ ደረጀ ደሱ፤ ቴዎድሮስ ምትኩና ሌሎችም በርካታ የብሄራዊ ቡድን ተሰላፊዎችን አፍርቻለሁ።

**ኢ.ቶ** አውስትራሊያ ባለህስ ቆይታ ?

**ሳህሉ፡-**እዚህም ማሰልጠኔን አላቆምኩም ፤ ሲድኒ እያለሁ ጀምሬ አሁንም ኒክ ቲምላተስ የተባለ እኔ ያሰለጠንኩት ተወዳዳሪ በቅርቡ ሻምፒዮን ሆኗል።

**ኢ.ቶ**በአውስትራሊያ ቤልት አገኘ ሲባል እሰማለሁ ኢትዮጵያ ደግሞ በዚህ ኪሎ ካታጎሪ ወርቅ አገኘ ወይም ሻምፒዮን ሆነ ይባላል ልዩነቱ ምንድነው?

**ሳህሉ፡-**በዚህ አገር ቤልት የሚሸለመው የፕሮፌሽናል ቦክሰኞች ውድድር ነው። የሚወዳደሩትም ለገንዘብ ነው፡፤ አንድ ነጋዴ ምርጥ ምርጥ ቦክሰኞችን ጠርቶ ውድድር ሊያዘጋጅ ይችላል። አሸናፊው ገንዘብ ይሸለማል፡፤ በፎክስቴል ራቁታቸውን ሲወዳደሩ የምታያቸው፡፤ ፕሮፌሽናሎች ናቸው፡፤ የቡድናቸውን ማልያ ወይም የሃገራቸውን ባንዲራ አድርገው የሚወዳደሩት ደግሞ አማተሮች ናቸው፡፤ በተወሰነ ኪሎ ካታጎሪ ይወዳደሩና ወርቅ፤ ብር፤ ነሃስ ይሸለማሉ። የኛም አገር እንደሱ ነው።አማተሮች ነበርን እኛም።

**ኢ.ቶ** እስኪ መቼም ሪንግ ላይ አስቂኝ አጋጣሚ አይጠፋምና ከመለያየታችን በፊት አንድ ሁለት ጀባ ብትለን፡፤

**ሳህሉ፡-**ልክ ነህ ብዙ አስቂኝ ነገር አለ። በራሴ ላይ የደረሰውን ላስቀድም፡፤ገና ቦክስ ጀምረን ብዙም ሳልጫወት ብሄራዊ ቡድን ተመረጥኩ።እናም ለሎሳንጀለስ ኦሎምፒክ ልምድ ያግኙ ተባልንና ጀርመን ሄድን። ጀርመን ለኔ የደረሰኝ በጣም ታዋቂ የሆነ የሜክሲኮ ቦክሰኛ ነው፡፤ ከመቶ በላይ ውድድር ያደረገ ነው። እኔ ደግሞ ያደረኩት ውድድር 5 ነው። ታዲያ አሰልጣኜ ይሄ ነገር እንዴት ይሻላል? ያንተንም ወደ 70 እናድርገው አለ። አዎ 70 ይባል። 5 ውድድር ማለት ትንሽ ሞራል ስለሚነካ 70 ውድድር አድርጓል ተብሎ እንዲተዋወቅ ተስማምተን በ70 ተዋወቀልኝ። ያም ሆነ ይህ ግን ሰውየው በጣም አደገኛ በመሆኑ በፍራቴ አልቀረም፡፤ አይደርሱ የለም ሰአቱ ደረሰ ፡፡ ሪንግ ላይ ወጣን። አንድ ዙር እንደምንም ጨረስኩ። ሁለተኛው ዙር ላይ ገላገለኝና ወጣው እልሃለሁ። 70 ውድድር ያደረገው ቦክሰኛ በሁለተኛው ዙር ...ቅቅ።

ሌላው ደግሞ እኔም በተራዬ  በጣም ልምድ አግኝቼ አገር ውስጥ በተከታታይ አመት ሻምፒዎን በመሆኔ ከኔ ጋር የሚደርሳቸው ተወዳዳሪዎች እንደሚጨነቁ እሰማ ነበር። አንዴ አንድ የፖሊስ ተወዳዳሪ ከኔ ጋ ይደርሰዋል። ግን እሱ አልሰማም። የሰማው፡ አሰልጣኙ ነበርና ውድድሩ እስኪደርስ በጭንቀት እንዳይጎዳ አትንገሩት ይላል። ነገር ግን ቦክሰኞች ስለሚገናኙና ስለሚያወሩ ሙሉ ለሙሉ መደበቅ አይችልም። ካንዱ ሰማው;፡፤ በኋላ ከአስልጣኑ ጋ ምሳ እየበሉ ልጁ ድንግጦ ምግብ መብላት አቅቶት ያያል ። አሰልጣኙ ምን ሆነሃል ለምን አትበላም ይለዋል፡፤? እኔ ከሳህሉ ጋ ነው እንዴ የደረሰኝ ? ይለዋል። አሰልጣኙም ማን ነገርህ፡? ይልና ከሰማ አይቀር ብሎ፡ አዎ እውነት ነው ታዲያ ሳህሉ የሆነ እንደሆነስ? ብሎ ሊያበረታታው ይሞክራል;። ቀኑ ደረሰ ሪንግ ላይም ወጣን ፡፡ ገና እንደጀመርን በቀኝ እጄ ሙሉ ለሙሉ ፊቱ ላይ አገኘሁት ፡፤ ቀጥሎም በግራ እጄ በሃይል ሰነዘርኩ፤ ግን አለመታሁትም ሳትኩት፡፤ አጅሬ ግን ተስቶም ወደቀ ። ዳኛው አንድ ሁለት እያለ መቁጠር ጀመረ እሱ ግን ከፈለክ መቶ ቁጥር  ብሎ ለጥ አለ፡፤ ልክ ዳኛው 10 ሲል ፍንጥር ብሎ ተነስቶ ተቃቅፈን ስንሰነባበት በጆሮዬ ምን እንዳለኝ ታውቃለህ? **"ማን ፉል አለ የሚቀጠቀጥ"** ....ሳቄን መቆጣጠር አልቻሉም .....!

**ኢ.ቶ** በጣም በጣም የሚገርም ቦክሰኛ ነው፡፤ እንዲህ ከፈራ ለምን ፎርፌ አይሰጥም ?

**ሳህሉ፡** እንዴ ክለቡ የሚቀልበው ደሞዝ የሚሰጠው እንዲወዳደር እንጂ ፎርፌ እንዲል አይደል ማን እሺ ይለዋል?

በጣም አመስግናለሁ ሳህሉ! ...../////......

## ቆይታ ከተካበ ...........

[ከገጽ-10 የዞረ]

**ጥያቄ፡-**የኳስ ነገር አይታወቅም እያልክ ነው ወይስ ...?

**መልስ፡-**አይ ቡድኑ ያለውን ጠንካራ ጎን ይዞ ሌሎችም በውጭ ያሉ ተጫዋቾችን ማሰባሰብ ከቻለ ጥሩ ቡድን ይወጣዋል። ለምሳሌ እዚህ እኛ ጋ አንድ በጣም ጎበዝ የሆነ ልጅ አለ፡፤ ሲጫወት ቪዲዮ ክሊፑን ለአሰልጣኙ ልከንለት አይቶት ይምጣ ብሏል፡፤ ሊሄድ እየተዘጋጀ ነው፡፤ እሱ ከሄደ ትልቅ ተስፋ ነው። በጣም ፈጣንና ጎል አግቢ ልጅ ነው፡፤ ከሌላም አገር እንዲሁ ከሰበሰቡ ምናልባት ደቡብ አፍሪካ ጥሩ ተፎካካሪ ሊሆኑ ይችላሉ።

ይልቅ እኔን በጣም ያናደደኝ ነገር ለምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ ዋንጫ ዋናውን ቡድን አስቀምጠው ሁለተኛውን ቡድን መላካቸው ነው፡፤ ይህን የመሰለ እድል አይገኝም። ቡድኑ ሄዶ መጫወት ነበረበት፡፤ ልጆቹ ብዙ ኢንተርናሽናል ልምድ ስለሌላቸው በጣም ይጠቅማቸው ነበር።

**ጥያቄ፡-** ምንአልባት ተጫዋቾች እንዳይጎዱ ወይም የማይሆን አይነት መሸነፍ ተሸንፈው የአካልም የሞራልም ስብራት እንዳያጋጥ ማቸው ሰግተው ይሆን?

**መልስ፡-** ሰግተው ሊሆን ይችላል፡፤ ነገር ግን ስጋታቸው ትክክል አይደለም ነው የምለው በራሴ አመለካከት። ሄደው ቢጫወቱ ምንም አይሆኑም፡፤ አንድ ሳምንት እስኪቀረው ድረስ መጫወት ይችላሉ፡፤ እያንዳንዱ ጌም ትምህርት የምታገኝበት፤ ደካማ ጎንህን የምታይበት በመሆኑ ትልቅ እድል ነው ያመለጣቸው።በኛ ግዜ በሳምንት እስከ 5 ጌም የተጫወትበት ግዜ አለ የወዳጅነት ብቻ። ብዙ ልምድ ነው የምትቀስመው። አሁን ገና ተሰባስበው ልምምድ አለመጀመራቸውን ሰምቻለሁ። ያ ደግሞ ልክ አይደለም። ከውድድሩ በፊት ምንም የወዳጅነት ግጥሚያ ሳያደርጉ መግባ ታቸው ትልቅ ጉዳት ይኖረዋል ።

ለማንኛውም ግን ፖዝቲቭ እያሰብን መጠበቅ ነው ያለብን።ከ31 ዓመት በኋላ ለዚህ መብቃታቸው ራሱ ትልቅ ነገር ነው፡፤ በዚህ ሞራል ኳሳችንም ሊያድግ ይችላል፡፤ አንድ ቡድን ለአፍሪካ ዋንጫ መሳተፉ ራሱ አገር ውስጥ ያለውን የኳስ እንቅስቃሴ ይለው ጠዋል።

በኛ ግዜ ብዙ ተስፋ አስቆራጭ ነገሮች ነበሩ ብዙ ሞራል የሚጎዱ ነገሮች ነበሩ፤ ለምሳሌ አንዴ ታንዛኒያን 4-2 አሸንፈን ቀጣዩን ጌም በጉጉት ስንጠብቅ ወጣት ቡድኑ ሊጫወት ሄዶ በመጥፋቱ የኛ ውድድር ተሰርዞ ለታንዛኒያ ፎርፌ ተሰጥቷል።

**ጥያቄ፡-** መልካም እድል ለብሄራዊ ቡድናችን እየተመኘሁ ወደ ቀጣዩ ጥያቄ ላምራ፡ በምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ ዋንጫ የፍጻሜ ቅጣት ምት ወቅት የአንተንና የዳኛቸውን ስም በመጥራት በኢትዮጵያ እግር ኳስ አፍቃሪ ዘንድ ትልቅ ትዝታን የጣለው ጋዜጠኛ ደምሴ ዳምጤ ቡድናችን ለአፍሪካ ዋንጫ ማለፉን እንኳ ሳያይ በቅርቡ ከዚህ አለም በሞት ተለይቷል፡፤ ዜና እረፍቱን ስትሰማ ምን ተሰማህ? እስኪ ከደምሴ ጋር ያለህን ትውውቅና ስብ እናውን ግለጽልን፡፤

**መልስ፡-** የደምሴን ሞት ስሰማ በጣም በጣም ነው ያዘንኩት፡፤ በርግጥ መታመሙን ሰምቼ ነበር። ነገር ግን ሞት ሁሌም ቢሆን አስደንጋጭ በመሆኑ በጣም አስደንግጦኛል። ደምሴን የማውቀው ልጅ ሆኜ በድሬደዋ ስታዲየም የነጻ ጋዜጠኝነት ግልጋሎት ሲሰጥ ነው፡፤ በግዜው በጣም የሚያምር ነጭና ጥቁር አዲዳስ አድርጎ ሲዘግብ አስታውሳለሁ። ታላቅ ወንድሜ ስለሽ ይባላል የሱ ክላስ ሜት ነበር፡፤ በኋላም አዲስ አበባ ስራ ይዞ ሄዶ በስፖርት ጋዜጠኝነት ያደረገውን አስተዋጾ ሁሉም የሚያወቀው ነው።

ደምሴ በጣም ኮሚክ፤ ሰውን በሳቅ የሚገል ባጠቃላይ ጨዋታው የማይጠገብ አይነት ሰው ነው። ቅን ነው፡፤ ሰው ማስከፋት አይፈልግም፡፤ በተለይ የማደንቀው ደግሞ በስፖርት ፕሮግራሙ በሚያቀርበው ትችት በትክክል የቡድኖችን ጥንካሬና ደካማ ጎን የማየት ብቃቱን ነው፡፤ ተጫዋቾችን ሲተች በጣም ተጠንቅቆ ሞራሉን ሳይነካ ነው የሚመክረው፡፤ ሌሎቹ ጋዜጠኞች እኮ ሲተቹ እንኳን ለሞራል ሊጨነቁ እንድትታሰር ሁሉ የሚፈልጉ ነው የሚመስሉት። ደምሴ ግን ልዩ ችሎታና ቀናነት ነበረው፡፤

**ጥያቄ፡-** ተካበ ሁለተኛውንም አዳኔ ጉድ ነው! ጉድ ነው ! የሚለው ድምጹ አሁንም ጆሮዬ ላይ ያስተጋባል... ለመሆኑ ከድል በኋላ አግኝተህው ነበር?

**መልስ፡-** የእለቱ ለት አላገኘሁትም ሌላ ግዜ ግን ተገናኝተናል። ብዙ ሰዎችም የሚያስታውሱት አሁን አንተ እንዳልከው ነው። ደምሴ እውነተኛ የኳስ ፍቅር ያለው ጋዜጠኛ ነው። ከዚያ ውጭ አትላንታ ጋብዘነው መጥቶ አግኝቼዋለሁ፡፤ ኢትዮጵያ የሄድኩ ግዜ ግን ላገኘው አልቻልኩም። ባጠቃላይ ኢትዮጵያ ታላቅ የስፖርት ሰው ነው ያጣቺው፡፤በዚህ አጋጣሚ ለደምሴ ቤተሰቦችና ወዳጅ ዘመዶች መጽናናትን ይሰጣቸው ዘንድ መልካም ምኞቴን ልገልጽ እወዳለሁ።

**ጥያቄ፡-** ጥያቄዬን እየጨረስኩ ነው፤ ከመሰነባበታችን በፊት ግን እዚህ በክብር እንግድነት እንድትገኝ ተጋብዘህ እንዳልተመችህና መምጣት እንዳልቻልክ ጭምጭምታ ሰምቻለሁ፤ ልክ ነኝ?

**መልስ፡-** አዎ ተጋብዤ ነበር ። ነገር ግን በስራ ምክንያት ግብዣውን ተቀብዬ መምጣት ባለመቻሌ በጣም አዝኛለሁ። መካከላችሁ ሆኜ አብሬ ባሳልፍ ደስ ይለኝ ነበር። ግን ከአቅም በላይ ሆነ። ስለ ተደረገልኝ ግብዣ ግን ከልብ ላመሰግን እወዳለሁ።

**ጥያቄ፡-** እኔ ደግሞ ተካበ ከመጣ ከአማረ ጋር ባለፈው እንደ ተፎካከሩ ተቃራኒ ቡድን አሰልፈናቸው ጉድ እናያለን ብዬ አስቤ ነበር። ማነው ከጉድ የተረፈው አንተ ወይስ እሱ?

**መልስ፡-** ከጉድ የወጣው እሱ ነው፡ እኔ በበረኝነት ብቻ ሳይሆን በተጫዋችነትም ጉድ እንደምሰራው ራሱም ያውቃል...!

**ጥያቄ፡-** እሱማ ፈርቶኝ ነው የቀረው እያለ መሰለኝ

**መልስ፡-** እኔ እንደማልፈራው ያውቃል ይልቅ እሱ የሚፈራው የኔን ቡድንና ጢማም ፍየል ነበር፡

**ጥያቄ ፡-** ሳቅ...... እኔ መልዕክት አድራሽ ነኝ ይህንንም አደርሳለሁ። በተረፈ ተካበ ስለ ሰጠህን ሰፊ ማብራሪያ በአንባቢያን ስም በድጋሚ አመሰግናለሁ።

**መልስ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

KAAH
KAAH MONEY TRANSFER
LEADER IN MODERN REMITTANCE
ካህ የሐዋላ አገልግሎት
ካህ በሐዋላ አገልግሎት ተወዳዳሪ የሌለው።
96898788 / 0421165928

ሌማት እንጀራ ቤት
LEMAT INJERA BAKERY AND GROCERY



Serving You Only The Best ...

ሌማት እንጀራ ቤት
LEMAT INJERA BAKERY AND GROCERY
TRADITIONAL ETHIOPIAN BREAD AND GROCERIES
CALL US NOW TO PLACE YOUR ORDER
9689 0006
A:157 Nicholson St.
Footscray VIC 3011
F: 03 9396 1444
M: 0413 572 462
E: lematinjera@yahoo.com

እናት ጓዳ
Ria
Commonwealth Bank
Account Name: Daniel and Biely
BSB: 063 240
Account No: 10307752
Fast, Secure, Economical
በሐዋላ አገልግሎት ተወዳዳሪ የሌለው።

እናት ጓዳ
Ria
Daniel Tsegaye
General Manager
Tel: (03) 9041 0498
Mobile: 0423 323 808
or 0413 166 557
እንጀራ፤
በርበሬ
ሽሮ
ሚጥ ሚጣ
በሶ
ቡላ
ኮረሪማ
ቆሎ
ቋንጣ
ስልፍ ራይዝ ዱቄት
ጥራጥሬ እህሎች
ቅመማ ቅመሞች
እንጀራ፤ ለሰርግ፣ለልደት፣ለማንኛውም ዝግጅት በታላቅ ቅናሽ እናቀርባልን ።
አድራሻ፡ 187 ባርክሊ ስትሪት ፉት ስክረይ
Address: 187 Barkly Street, Footscray

# መልካም ልደት



ቤተል ሳምሶን 10ኛ ዓመቷን
ህዳር 2005 አከበረች






ሔርሜላ ሙሉጌታ 10ኛ ዓመቷን
ታህሣሥ 2005 አከበረች



በዕምነት ገዛህኝ
መስከረም 2005 ተወለደ






ባርናባስ ጌታሁን መስከረም 2005
5ኛ ዓመት ልደቱን አከበረ



ኤልታን አበበ በህዳር
2005 ዓ.ም ተወለደ






ኤልሻዳይ አበበ በጥር 2005
2ኛ ዓመቱን ያከብራል




HAPPY BIRTHDAY




Ras Dashen
Ethiopian Cafe and Restaurant
ራስ ዳሸን ምግብ ቤት
Delicious & Healthy
Ethiopian Cuisine
121 Nicholson St.
Footscray, VIC. 3011
(03) 9687 3293
Mob: 0403 978 248
Breakfast, Lunch, Dinner
Vegetarian Options
Traditional Coffee & Tea
Catering Service
Function Hire
Great, friendly service
121 Nicholson St.
Footscray, VIC. 3011
(03) 9687 3293
Mob: 0403 978 248


Preparation of Business Plan, Cash flow
Advice on Tax planning
Audit of Non for profit
Citizenship
Kids Vision Family Day Care Pty Ltd
Dedicated to quality care and achieving dream

# ለፈገግታ-ከኳስ ሜዳ

## ተንኮለኛው ..... ከበደ!


ሙሉጌታ ከበደ

የጊዮርጊሱ ተጫዋች ሙሉጌታ ከበደ ከጊዮርጊስ በፊት ለወሎ ምርጥ እና ለወሎ ፔፕሲ ክለብ ነበር የሚጫወተው፡፡ በጉብዝናው ወደ ጊዮርጊስ ተዛውሮ መጫወት እንደ ጀመረ በጨዋታ መሀል የተቃራኒ ቡድን ተጫዋቾች ሲጎትተው እየተመናጨቀ **«ሸማዬን ልቀቅ»** ነበር የሚለው፡፡ በዚህ የተነሳ ለብዙ ጊዜ «ሙሉጌታ ሸማ» እያሉ ያበሽቁት ነበር፡፡

ሙሉጌታ በተጫዋችነት ዘመኑ እንደጉብዝናው ሁሉ በተንኮለኛነቱም ይታወቅ ነበር፡፡ በአንድ ወቅት ጊዮርጊስ እና የሊቢያው አልኢትሃድ ሲጫወቱ ጨዋታው ሊጠናቀቅ 7 ደቂቃዎች እስከቀሩት ሰዓት ድረስ 1ለ1 ነበሩ፡፡ ነገር ግን ሙሉጌታ ማንም ሳይነካው ፔናሊቲ ክልል ውስጥ ኮርና ሲመታ ወድቆ በመንደባለሉ ፍፁም ቅጣት ምት ለጊዮርጊስ ተሰጠና ጊዮርጊስ ጨዋታውን 2ለ1 በሆነ ውጤት አጠናቀቀ፡፡ የአልኢትሃዱ የቡድን አምበል ከጨዋታው በኋላ ጋዜጠኞች ሲጠይቁት እንዲህ ነበር ያለው፡፡

**«ያሸነፈን ጊዮርጊስ ሳይሆን ያ ከይሲ አጭር ልጅ ነው፡፡»**

ሌላ ግዜ ደግሞ ብሄራዊ ቡድናችን ከቤኒን ጋር ሲጫወት ሙሉጌታ ከበደ የቤኒንን ተከላካዮች አታሎ አልፎ በቅርብ ርቀት ወደ ግብ የሰደዳት ኳስ የጎሉን ቋሚ ታካ ለጥቂት ወደ ውጭ ትወጣና በውጭው መረብ ሥር ትወተፋለች። ሰዓት እያለቀ ነበርና አጅሬ መላ መፈለግ ነበረበት፤ ወዲያውኑ ፈጥኖ ወደ ኳሳ በመሮጥ ኳሷን በእጁ አንስቶ ወደ መሃል ሜዳ ይገሰግሳል። ዳኛው ግራ ተጋቡ። ወዲያም እጃቸውን ወደ መሃል ሜዳ እያመለከቱ ፊሽካ ነፉ። ጎል መስሏቸው አጸደቁት። ቤኒኖች አልገባም ብለው ጮሁ! ቆይቶ ተንኮሉ ቢታወቅም፤ ጎሉ ግን ተቆጥሮ ኢትዮጵያ 2 ለ1 አሸንፋለች። ሌላውንም ጎል ያገባው እሱው ነበር፡፡ አንዱን በአብዶ አንዱን አወናብዶ!

## ቡናና ጅን !



የቡና ተጫዋቾች (ብዙዎቹ) በካሳዬ አራጌ መሪነት ግሮሰሪ ገብተው ጠጥተው ወደሜዳ በመግባትና ከጨዋታ በኋላም ተመልሰው በመሄድ ይታወቁ ነበር፡፡ በአንድ ወቅት እንደልማዳቸው ጅናቸውን ተግተው ወደ ሜዳ በመግባት የባንክ ቡድንን 3ለ1 አሸንፈው ወደግሮሰሪያቸው ይመለሳሉ፡፡ ከእስታዲየም ወጥቶ ደስታውን በቢራ ሊያወራርድ እግር የጣለው አንድ ደጋፊያቸው ድንገት እዚያ ግሮሰሪ እነካሳዬ አራጌን ሲያገኛቸው ሁሉም ስፐራይት አዘው እየጠጡ ነው፡፡ ሰውየው በዕለቱ ውጤትና እነርሱን በአካል በማግኘቱ ተደስቶ አስተናጋጁን በመጥራት «የሁሉም ሂሳብ እኔ ጋር ነው ደምረህ ንገረኝ» ይለዋል፡፡ አስተናጋጁም እንደታዘዘው ሂሳቡን በወረቀት ሰርቶ ለሰውየው ይሰጠዋል፡፡ ሰውየው በአንድ ጊዜ ላብ አጠመቀው፡፡ የተጠየቀው ሂሳብ በጣም ብዙ እና ያልጠበቀው ነው፡፡ ለካስ እነ አጅሬ በስፐራይት ጠርሙስ ሞልተው የሚጠጡት ጅንኑን ኖሯል!!

## አንዳንዶቻችሁ እንዲህ ነው የምትመቱት!

የኢትዮጵያ ችርቻሮ ንግድ ኮርፖሬሽን (ኢችንኮ) ቡድን አሰልጣኝ ተጫዋቾቹ የቅጣት ምት ልዩ ተሰጥኦ እንዲኖራቸው ለማድረግ ብዙ ይጥርና ይደክም እንደነበር ይነገራል፡፡ በዚሁ መሠረት ብዙ ካለማመዳቸው በኋላ የመጨረሻው ዕለት ክህሎታቸው ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ ሁሉም እንዲመቱ ያደርጋል፡፡ ነገር ግን ሁሉም የሚመቱት ታርጌት አልመታ እያለ ወደውጭ ሲወጣ አሰልጣኙ በጣም ይናደድና «ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ እኔ መትቼ አሳያችኋለሁ፡፡ ከዚህ በኋላ ግን በፍፁም አላሳያችሁም፡፡ ለመጨረሻ ጊዜ የማደርገውን አስተውሉ» ይላቸውና ኳሷን አስቀምጦ ተንደርድሮ ይጠልዛታል፡፡ ኳሷ እንኳን ልትገባ በግቡ ክልል እንኳን ማለፍ ተስኗን ወደውጪ ትወጣለች፡፡ በዚህ ጊዜ አሰልጣኙ ፈርጠም ብሎ «አያችሁ አይደል?» ... አንዳንዶቻችሁ እንዲህ ነው የምትመቱት» አላቸው፡፡

ወደ ገጽ 25

# ለፈገግታ .....

[ከገጽ 24 የዞረ]

## ★ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ 32ኛ ልጅ ★


አለማየሁ ኃይለሥላሴ (ፊኛ)

እንደ ሙሉጌታ ከበደ ሁሉ ሜዳ ውስጥ በሚሰራው ተንኮልና በቀልዱ የሚታወቀው ሌላው የቀድሞ የጊዮርጊስ ቡድንና የብሄራዊ ቡድናችን 2 ቁጥር ቦታ ተጫዋች አለማየሁ ኃይለሥላሴ በቅጽል ስሙ አለማየሁ ፊኛ ነው። አለማየሁ ኃይለ ሥላሴ (ፊኛ) በእግር ኳስ ዘመኑ እጅግ የማይረሳ ገጠመኝ አለው:: ለአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ከዛምቢያ ጋር ጨዋታቸውን አ/አበባ ላይ በሚያደርጉ ጊዜ ሳይነኩት እንደተመታ እየወደቀ ሁለቱን ኮኮብ የዛምቢያ ተጫዋቾች በቀይ ካርድ እንዲወጡ ያስደርጋል።ወደ ዛምቢያ ለመልስ ጨዋታ ሲሄዱ አለማየሁ የሚባል ሁለት ተጫዋቾች ከሜዳ አስወጥቶብናል የቱ ነው ብለው የዛምቢያ ቲፎዞዎች ኤርፖርት ድረስ ይሄዳሉ። በጋጣሚ ራሱን ያገኙትና የቱ ነው አለማየሁ ብለው ይጠይቁታል። አጅሬም አለማየሁ ቀርቷል አለመጣም ብሎ መልሶ ቡድኑ በሰላም ወደ ሆቴሉ ይሄዳል። ይህ በሆነ በ3ኛው ቀኝ ጋዜጦች የአለማየሁን ፎቶ አውጥተው አለመቅረቱን ይጽፋሉ። ወዲያውኑ ይህን የሰሙ ሌሎች ጋዜጠኞች ሆቴሉ ድረስ በመሄድ ቃለ መጠይቅ እንዲያደርግ ይጠይቁታል። እሱም ፈቃደኛ ሆኖ ለቃለ መጠይቅ ይቀርባል። **ስምህ ማን ይባላል?** የመጀመሪያው ጥያቄ ነበር። አሌክስም አለማየሁ ኃይለስላሴ እባላለሁ ብሎ ራሱን ያስተዋውቃል። ጋዜጠኛው መለስ አድርጎ **የንጉሱ ልጅ ነህ እንዴ?** ብሎ ይጠይቃል። አሌክስ ምኑ ሞኙ? **አዎ!** ብሎ ይመልሳል።ቀጠለ ጥያቄው፤- **ስንተኛ ልጃቸው ነህ?** አሌክስ ግራ ገባው.. ባወጣ ያውጣው ብሎ **32ኛ ልጃቸው ነኝ**።ይላል፡፤ ወዲያው ጋዜጦች የንጉሱ 32ኛ ልጅ ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ይጫወታል ብለው አራግበውት ኖሮ በግዜው የዛምቢያ ፕሬዘዳንት የነበሩት ኬኔስ ካውንዳ ሆቴል ድረስ በመምጣት ይተዋወቁታል። የንጉሱ ልጅ ስላለ በጥም ጥሩ ሆቴል ይስተናገዱ ተብሎ ሆቴል ይቀየርላቸዋል፡፤ ወደ ሜዳ ለጨዋታም ሲሄዱ በስረገላ ተቀምጠው እንዲሄዱ ተደርጎ በክብር ተስተናግደዋል።

## “ በጥግ በኩል ሹልክ ብለህ ግባ ”

ሩህሩሁ አሰልጣኝ

በ1981 ዓ.ም ጃንሜዳ ላይ ይካሄድ በነበረው የሁለተኛ ዲቪዚዮን ሊግ ውድድር የፔፕሲ ቡድን ጠንካራ ተፎካካሪ ነበር:: እናም ብዙ ወጣቶች በዚህ ቡድን ውስጥ ታቅፈው ይጫወቱ ነበር:: በአንድ ወቅት የተጫዋቾች ቁጥር ወደ 36 ደርሶ እንደነበርም ይነገራል:: እናም በተጠቀሰው ዓመት የመጨረሻው የሊጉ ውድድር ሲካሄድ አመቱን ሙሉ አንድም ቀን ሳይጫወት ያለፈ ተጫዋች አሰልጣኙን ይጨቀጭቀዋል:: «ኧረ ዛሬ እንኳን ኳሷን ልንካ ያለዛሬ እኮ በቃ መቼም አልጫወት» እያለ ሲነዘንዘው አስቀድሞ 3 ተጫዋቾችን ቀይሮ የነበረው አሰልጣኝ የሚያደርገው ግራ ይገባዋል:: በመጨረሻ ምንም ማድረግ እንደማይችል ሲያውቅ ሩህሩሁ አስሰልጣኝ ልጁን ቀስ ብሎ በጆሮው «ቀስ ብለህ መስመር ዳኛው ሳያይ በጥግ በኩል ሹልክ ብለህ ግባ» ይለዋል:: ተጫዋቹ እንደተ ባለው አድርጎ ጨዋታው ሊጠናቀቅ 2 ደቂቃ ሲቀረው የተቀናቃኝ ቡድን አሰልጣኝ ዘሎ ወደ ሜዳ ይገባና ዳኛው ጨዋታውን እንዲያስቆም ያደርገዋል:: እናም ተጫዋቾቹ ሲቆጠሩ የፔፕስ 12 ይሆናሉ:: በዚህም ለዚያኛው ቡድን ፎርፌ ይሰጣል:: የሚገርመው ግን እስከዚያ ደቂቃ ድረስ በመስመር ዳኛው በኩል ተጫዋቹ ሾልኮ መግባቱ አለመታወቁ ነው::

## ★ መንግስቱና ሸዋንግዛው ★

"ጊዮርጊስን ከለብ ዝነኛ ካደረጉት ውስጥ መንግሥቱ ወርቁና ሸዋንግዛው ይጠቀሳሉ፣ ሁለቱም አንድ ቤተሰብ ነው ያገቡት ሁለቱም የብሔራዊው ቡድንም የጊዮርጊስም አምበል ነበሩ፣ ሁለቱም የብሔራዊ ቡድን አሰልጣኝ ነበሩ፣ ሁሉቱም የሼል ድርጅት ነበራቸው፣ ሁለቱም ቤተመንግሥት ነበር ያደጉት፣ ★ ★ ★

ሁሉም ሰው የሚያውቀው መንግሥቱ ወርቁ በሚለው ስም ነው:: ቤተሰቦቹ ያወጡለት እና የመዝገብ ስሙ አሻግራቸው ነው:: አባቱ አርበኛ ስለነበሩ ለጣሊያኖች ስላስቸገሩ አባቱን ለማስመጣት አሻግራቸው ወርቁ ከእናቱ ጋር ታሠረ:: በልጅነቱ በእሥር ላይ የነበረው አሻግራቸው ጣሊያኖች ሁኔታውን ዐይተው አንተ መንግሥት ለመሆን ነው የምትፈ ልገው በሚልመንግሥቱ ብለው ጠሩት:: አሻግራቸው የሚለው ስሙ እየተረሳ ሄደና በመንግሥቱ ስያሜ እየታወቀ ሄደ:: በእግር ኳሱም ነገሡ:: [ወደ ገጽ 33 ዞሯል]

# ከ31 ዓመት በኋላ የተገኘው ድል እና ደጅ ያደረው ኢትዮጵያዊ
## ተጫዋቾቹ፣ ተመልካቹ፣ ፖለቲካው እና መጪው ጊዜ (ልዩ ዘገባ ከአ.አ)

ዓለም አቀፋዊ ዝና ያላቸውም ሆኑ ነገሩን በስሜት ሲገልፁ የነበሩት የሀገራችን መገናኛ ብዙሃን ስለ ድሉ ያስተላለፉትን ዘገባ የጀመሩት ተመሳሳይ በሆነ አንድ ቃል ነበር፡፡«ከ31 ዓመት በኋላ የተገኘ ድል» በሚል፡፡እኔም ይህንኑ ቃል ከመድገም ውጪ ሌላ ጀምርበት ቃል የለኝምና እንዲህ ልበል «ኢትዮጵያ ከ31 ዓመት በኋላ ወደ አፍሪካ ዋንጫ ተመልሳለች፡፡ ዋልያዎቹ ቅዥት የመሰለውን ህልም በመፍታት የትውልዱን ታላቅ ምኞት አሳክተዋል፡፡»ሀገራችን በእግር ኳስ ወዳድ ህዝቦች የተሞላች ናት፡፡ እንዳለመታደል ሆኖ ግን ኳሳችን ለአደባባይ መብቃትን አልታደለም፡፡ ምክንያቱን ለማወቅ ጥልቅ ጥናትን ማድረግ ደግሞ ትርፉ ድካም ነው፡፡ ለምን ቢሉ ምላሹ ግልጽ እና አንድ ነው፡፡ ኳሳችን ከፖለቲካ ተፅእኖ
ነጻ አይደለም፡፡ኳስና ፖለቲካውን ምን አገናኘው ለምትሉ ወደኋላ ምላሽ አለኝ፡፡ አሁን ግን ወደድሉ እንመለስ፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ኢትዮጵያ ከ 31 ዓመት በኋላ የአፍሪካ ዋንጫ ተሳታፊነት ምኞቷን በድል አሳክታለች፡፡ ላለፉት ረጅም ዓመታት የኢትዮጵያዊያን ሁሉ ጥያቄ ሆኖ የቆየው የአፍሪካ ዋንጫ ተሳትፎ እውን ሆኗል፡፡ የሱዳን አቻቸውን ሁለት ለባዶ በማሸነፍ ማለፋቸውን ያረጋገጡት ዋልያዎቹ በአጠቃላይ ውጤት አምስት እኩል ቢሆኑም ከሜዳው ውጪ ግብ ባስቆጠረ በሚለው የፊፋ ህግ መሰረት ከፊታችን ጥር 11 ቀን 2005ዓ.ም እስከ የካቲት 3 ቀን 2005ዓ.ም ድረስ በደቡብ አፍሪካ አስተናጋጅነት ለሚካሄደው 29ኛው የአፍሪካ ዋንጫ አልፈዋል፡፡

በመጀመሪያው ጨዋታ ምዱርማን ውስጥ በአልሂላል ስታዲየም በሱዳን አቻቸው አምስት ለሶስት ተሸንፈው የመጡት ዋልያዎች የአዲስ አበባውን ጨዋታ ለማሸነፍም ከፍተኛ ፍላጎትና እልህ ነበራቸው፤ እናም የነበራቸውን የሁለት ግቦች ብልጫ በመቀልበስ ድሉ የኢትዮጵያ እንዲሆን አድርገዋል፡፡

መለስ ብለን የጨዋታውን ሁኔታ ስናስብ ብዙ አስገራሚ እና ህልም የሚመስሉብት ትእይንቶች እናስታውሳለን፡፡ የጨዋታው የመጀመሪያ አጋማሽ በሱዳኖች ሰዓት የማባከንና በዋልያዎቹ አለመረጋጋት ታጅቦ ነበር የተጠናቀቀው፡፡ ዋልያዎቹ ይጠበቅባቸው የነበሩትን ሁለት ግቦች ለማስቆጠር በማጥቃት ላይ የተመሰረተ አጨዋወት ይዘው እንደሚገቡ ቢታሰብም አሰልጣኙ የተከተሉት የአራት ሶስት ሦስት አሰላለፍ ውጤታማ የነበረ አይመስልም፡፡ ሱዳኖች ውጤታቸውን አስጠብቀው ለመውጣት በሶስት አምስት ሁለት አሰላለፍ ወደሜዳ መግባታቸው ዋልያዎቹ በመሀል ሜዳ እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል መልኩ ባይበለጡም እንደልባቸው ኳስን ይዘው ለመንቀሳቀስ አላስቻላቸውም፡፡ በዚህ ምክንያት በረጅም ወደ ግብ የሚልኳቸው ኳሶች ከሱዳን ተከላካዮችና ከግብ ጠባቂው ማለፍ አልቻሉም ነበር፡፡ወደ እረፍት ከመውጣታቸው በፊትም በዋልያዎቹ አልፎ አልፎ ከሚደረጉ የግብ ክልል እንቅስቃሴዎች በስተቀር እምብዛም ማራኪ የሚባል ጨዋታ አልታየም፡፡ ሱዳኞች ኳስ መሬት ላይ በማንከባለል ሰዓት ለማባከን ባደረጉት ጥረት ጨዋታው የተፈለገውን ያህል ታዳሚውን አላዝናናም፡፡ ይህም በተመልካቹ ስሜት ላይ መጥፎ መረበሽን ፈጥሮ ነበር፡፡ በዚህ መልኩ የመጀመሪያው አጋማሽ መጠናቀቁ ደግሞ ተመልካቹ የተመኘውን ድል በሩቁ እያለመ በሀሳብ እንዲቆዝም አድርጎታል፡፡ ሌሊቱን እዚያው አድሮ የስታዲየም መግቢያ ትኬቱን የቆረጠው ህዝብ ጨዋታው እስኪጀመር ድረስ ቀኑን ሙሉ ሲጨፍር እንዳልነበር በጨዋታው እረፍት ሰዓት ሁሉም በትካዜ ተውጦ ስታድየሙ በዝምታ መሞላቱ የእውነትም ውጤቱ እየራቀ መሄዱን ሚያረጋግጥ መስሎ ነበር፡፡ ከእረፍት መልስ ተጫዋቾች ይቀይራሉ ተብለው የተጠበቁት አሰልጣኝ ሰውነት ምንም ለውጥ ሳያደርጉ ወደ ሜዳ ገብተዋል፡፡ በ49ኛው ደቂቃ ባልተለመደ ሁኔታ ወደ ቀኝ መስመር ወጥቶ ሲጫወት የነበረው አዳነ ግርማ የሞከራት ኳስ አግዳሚውን መትታ ወደውጪ መውጣቷ ግን ሁሉንም ተመልካች ከትካዜ ያባነነች፣ ወደ ድጋፍና የሞራል ጩኸቱ የመለሰች ነበረች፡፡ እንግዲህ ያኔ ነው ሁሉም በአንድ ድምፅ «ድሌ ማታ ነው ድሌ» ወደሚለው ህብረ ዝማሬ የተሻገረው፤ አዳነ የመታት ኳስ የግቡን አግዳሚ ለትማ መውጣቷን እንዳየ ወደ ጥላ ፎቅ ተመልካቾች ፊቱን አዞሮ በእጁ «ተነሱ!» አለ «ተነሱ የድሉን ዝማሬ አስተጋቡ!»... ይሄኔ ስታድየሙ በጩኸት አበደ፡፡ እናም እንዲሁ ጭፈራው እንደ ደራ ተዓምረኛዋ 59ኛ ደቂቃ መጣች፡፡ ጥሩ ሲንቀሳቀስ የነበረው ነገር ግን ድካም የታየበት ምንያህል ተሾመ ወጥቶ የመስመር ተጫዋቹ በሀይሉ አሰፋ (ቱሳ) ወደ ሜዳ ሲገባ ጨዋታው ጋለ፤ ይህን ተከትሎ በ62ኛው ደቂቃ ተቀይሮ የገባው ቱሳ ከቀኝ መስመር በግሩም ያሻገራትን ኳስ አዳነ ግርማ በጭንቅላቱ በማስቆጠር ኢትዮጵያን የህልሟ ግማሽ ላይ አደረሰ፡፡ ኳሷ ከመረቡ ስትገናኝ እድሜ ጠገቡ ስታዲየማችን የሚናድ እስኪ መስል እንደሸቦ አልጋ ይረግብ ጀመር፡፡ ከዚያች ግብ መቆጠር አራት ደቂቃዎች በኋላም በተመሳሳይ ከቀኝ መስመር የመጣችውን ኳስ አጥቂው ሳላህዲን ሰኢድ ሲያስቆጥር ህዝባችን ጮቤ ረገጠ፡፡ «ተረኛ ነኝና እንዳትሸበሪ ስለይሽ አድራለሁ ሱዳን ደህና እደሪ» የሚለው ዜማ በስታድየሙ አስተጋባ፡፡ ከፊሉም እንባውን በደስታ ያረገፈው ነበር፡፡

### የማይረሱ ትዝታዎች

አንድ መቶ አንድ ደቂቃዎችን ባስቆጠረው ጨዋታ የታዩት ድራማዊ ክስተቶች ብዙ ናቸው፡፡ ከነዚህ ክስተቶች መካከል ቀዳሚው ኳስ ወዳዱ ኢትዮጵያዊ የዘጠና ደቂቃውን ጨዋታ ለማየት ከቅዳሜ ሌሊት ጀምሮ በስታድየሙ ዙሪያ መገኘቱ ነው፡፡ቅዳሜ ምሽቱን ከ4 ሰዓት ጀምሮ በየስታድየሞቹ በሮች ወረፋ መጠበቅ የጀመረው ህዝብሌሊቱን እሳት እያነደደ በጭፈራ እና ሆታ ነው ያነጋው፡፡ በስታዲየም ዙሪያ ያሉት እነ«ጌታ ዘሩ» ድራፍት ቤቶችም ገበያቸው ደርቶ፣ መቀመጫዎቻቸው ሁሉ በሰው እንደተሞሉ ነው የነጋው፡፡ ለወትሮው ከምሽቱ 4 ሰዓት ላይ አገልግሎታቸውን በመጨረስ ይዘጉ የነበሩት የስታዲየም ዙሪያ ድራፍት ቤቶች አስተናጋጆቻቸውን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድንን ማሊያ በማልበስ ሌሊቱን ሲያገለግሉ እንዲያነጉ ማድረጋቸው የበዓሉን ዋዜማ ምሽት የማይረሳ ትዝታ እንዲኖረው አድርጓል፡፡ ወረፋ ለመሸጥ ብለው ሌሊቱን በስታዲየሙ በሮች ስር በጎረምሶች እየተጠበቁ ያነጉት እናቶች ጉዳይም ከማይረሱ ትዝታዎች አንዱ ነበር፡፡ ምሽቱ አልፎ ቀኑ ሲመጣ ተመልካቹ አልደከመም፡፡ ሌሊቱ ሲጨፈር እንደነጋው ቀኑም በጭፈራ የታጀበ ነበር፡፡ ሁሉም ስርዓት (ሰልፍ) እንደያዘ የስታዲየሙ መከፈቻ ሰዓት (6ሰዓት) ሲደርስ ሁሉም እንደ አመጣጡ ትኬቱን ቆርጦ ገብቷል፡፡ ይሁንና የስታዲየሙ መቀመጫዎች ሞልተው ትኬት አልቋል ሲባል ውጪ የነበረው ህዝብ ቁጥር የገባውን ሁለት እጥፍ ይሆናል፡፡ ፖሊስ «ትኬት አልቋል ተመለሱ» ማለት ሲጀምር ግን ነገሩ አዝማሚያውን የቀየረ እስኪመስል ግርግር ተፈጥሯል፡፡ በተለይም በሚስማር ተራ በኩል በፖሊስና ትኬት አልቋል በተባሉ ተመልካቾች መካከል በተነሳ አምባጓሮ የተወሰኑ የፖሊስ አባላት ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡

ከሰላሳ ሺህ በላይ ደጋፊ የተገኘበት የአዲስ አበባ ስታድየም መሙላቱን አምኖ ወደኋላ የተመለሰው ተመልካች ሁለተኛ አማራጩን ከመጠቀም አልቦዘነም፡፡ ይልቁንም በጥቂት ሜትሮች ርቀት ላይ ወደሚገኘው መስቀል አደባባይ በማምራት በትልቁ የሶኒክ ስክሪን የሚተላለፈውን ጨዋታ ተከታትሏል፡፡ በዚያ ቦታ የነበረው ህዝብ ስታዲየም ከገባው የሚበልጥ ሲሆን ጎዳናው በህዝብ ተሞልቶ ሲታይ ትእይንቱ በ1997 ኢህአዴግ እና ቅንጅት የጠሩትን የድጋፍ ሰልፍ ያስታውሳል፡፡ሌላኛው የዚህ ጨዋታ ክስተት ሁለቱ ጎሎች በጥቂት ደቂቃዎች ልዩነት ከተቆጠሩ በኋላ

በመጠኑ የቀነሰው የደጋፊዎች ጭንቀት የጨዋታው ሌላኛው አስገራሚ ገፅታ ከነበረው ከግብ ጠባቂው ጀማል ጣሰው ጉዳት በኋላ ተባብሶ የመቀጠል እድል ገጥሞታል፡፡አስቀድሞ የሶስት ተጫዋቾች ቅያሪ አድርጎ ኮታውን የጨረሰው ብሔራዊ ቡድናችን የጀማልን ጉዳት ተከትሎ በአስር ልጆች መጫወቱም የዚህ ወሳኝ ጨዋታ ሌላኛው ክስተት ነበር፡፡ በመጨረሻም ከአስር በላይ ለሆኑ ደቂቃዎች ከአማካይነት ወደ ግብ ጠባቂነት ተቀይሮ የተጫወተው አዲስ ህንጻ በ101ኛው ደቂቃ ኳሷ አምልጣው ከመረብ የተገናኘች ቢሆንም ከጥቂት ሽርፍራፊ ሰኮንዶች በፊት ዳኛው የጨዋታውን መጠናቀቅ የምታበስረውን ፊሽካ በመንፋታቸው ሳትቆጠር ቀረች እንጂ ጉድ ሆነን ነበር፡፡በመጨረሻም አንድ አስገራሚ ትውስታ እናንሳ፡፡ ጨዋታው ዜሮ ለዜሮ በነበረበት የመጀመሪያው አጋማሽ እና ሁለተኛው ግብ እስከ ተገኘችበት ደቂቃ ድረስ በጨዋታው ሜዳ ዙሪያ የነበሩ ኳስ አቀባዮች በፍጥነትና በንቃት ግዴታቸውን ሲወጡ ነበር፡፡

ሁለተኛዋ ግብ ከተቆጠረች በኋላ የሆነው ግን እንደ ኢትዮጵያ ሆነው ሲያስቡት የሚያስቅ እንደ ሱዳን ሆነው ሲያስቡት ግን አንጀት የሚያደብን አናዳጅ ትእይንት ነበር፡፡ሁሉም ኳሷን ደብቀው ዳኛው እና የሱዳን ተጫዋቾች «የኳስ ያለህ» እስኪሉ ድረስ ኳሷ ከሜዳ ትጠፋለች፡፡ ሰከንዶች ደቂቃ እስኪሞሉ ኳስ ጠፍቶ ሱዳኖች ዳኛውን «ሰዓት ያዝልን» ሲሉት ድንገት አንድ ኳስ ከሆነ አቅጣጫ ወደ ሜዳ ትገባለች፡፡ ጨዋታው ሊጀመር ሲል ደግሞ በሌላ አቅጣጫ ሌላ ኳስ ትገባለች፡፡ ጨዋታው እንደገና ይቋረጣል፡፡ በዚህ ተግባር ውስጥ የስታዲየሙን ፀጥታ ሲያስከብሩ የነበሩት ፌደራል ፖሊሶች ሳያቀሩ ተሳታፊ ነበሩ፡፡ ሰዓቱን በመግደል ድሉ እኛ ጋር እንዲቀር በማድረጉ በኩል ይህ ክስተት ተጫዋቾቹ ያደረጉትን ተጋድሎ ያህል ዋጋ ነበረው፤ ደግሞም እኛ ያደረግነው እነርሱ ካደረጉት አይበልጥም፡፡

## የመሰሉ መንግስቱ የጦርነት (አዋጅ?)

መሰለ መንግስቱ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ስሙ የገነነ ታዋቂ የስፖርት ጋዜጠኛ ነው፡፡በተለይም በኤፍ ኤም 98.1 በሚያስተላልፈው «እግር ኳስን በሬድዮ ተመልከቱ»በተሰኘ የቀጥታ ስርጭት ፕሮግራሙ እጅግ ተወዳጅ ለመሆን በቅቷል፡፡ መሰለ ኢትዮጵያና ሱዳን በአምዱርማን ያደረጉትን ጨዋታ በቦታው ተገኝቶ በቀጥታ የስልክ ስርጭት ወደ ኢትዮጵያ ያስተላልፍ ነበር፡፡ በወቅቱ ሲያስተላልፍ ያደመጠ ኢትዮጵያዊ ደግሞ ሳይወድ በግዱ በሱዳኖች ላይ «ቂም እንዲቋጥርና በጠላትነት እንዲያስባቸው» ይገደዳል፡፡ መሰለ በወቅቱ በቀጥታ ስርጭት የተናገረውን ቃል በቃል ማስታወስ ቢከብድም የመልእክቱ መንፈስ ግን እንዲህ የሚል ነበር «... ሱዳኖች በኢትዮጵያ ላይ ግፍ እየፈጸሙ ነው፡፡ ዳኞቹ ቀይ የሚያሰጥ ጥፋት ሲፈጸም እያዩ ዝም ብለዋል፡፡ የእኛ ቡድን ሶስት እኩል ከሆነ በኋላ ጨዋታው ሙሉ በሙሉ በወንጀሎች የተሞላ ሆኗል፡፡

ሱዳኖች ማንም ሳይነካቸው ሲወድቁ ፍፁም ቅጣት ምት ተሰጥቷቸዋል፡፡ እኛ ጋዜጠኞችና ቡድናችንን ለመደገፍ በቦታው የተገኙ ኢትዮጵያዊያን በፖሊስ ተከበን ነው ያለነው፡፡ ሱዳናውያን ከስታዲየሙ ላይ የባንዲራ ብረት ዘንግ ነቅለው ሊገድሉን ከበውናል፡፡ ፖሊስ እኛን ወደሆነ ክፍል አስገብቶን ነው ያለነው፡፡ ከዚህ በደህና መውጣታችንን በፍፁም እርግጠኛ አይደለንም፡፡ አድማጮች ከእንግዲህ ላንገናኝ እንችላለን፡፡ ሊገድሉን ይችላሉ፡፡»

እንዲህ አይነት ይዘት ያለው የመሰለ መንግስቱ ዘገባ ኢትዮጵያ ያለውን ተመልካች በቁጭት እና በእልህ ሲያንቆራጥጥ ነበር፡፡ ያም ሆኖ መሰለ እና የልኡካን ቡድኑ ከስነልቦና ጥቃት በስተቀር አካላዊ ጥቃት ሳይደርስበት ተመልሷል፡፡ ህዝቡ ግን «ይመጧታል!» እያለ በእልህና ዛቻ ነው የከረመው፡፡ ይህን ሁኔታ የተረዱ የስፖርት ፌዴሬሽን አመራሮች ህዝቡን ለማረጋጋት በተደጋጋሚ ስለ ስፖርታዊ ጨዋነት በየሚዲያው ይሰብኩ ነበር፡፡ የሚዲያውን አባላት በመሰብሰብም «ሚዲያው ህዝቡን በማረጋጋት እና በስታዲየም የበቀል ተግባር እንዳይኖር የመስበክ ስራ እንዲሰሩ አደራ»ብለዋል፡፡የጨዋታው እለትም የስታዲየሙ አስተዋዋቂ ደጋግሞ ሲናገር የነበረው «በስፖርታዊ ጨዋነት ጨዋታውን አሸንፈን ወደ አፍሪካ ዋንጫ እናልፋለን፡፡ ነገር ግን የእንግዳው ቡድን አንዳንድ ተጫዋቾችና ደጋፊዎች በተስፋ መቁረጥ ስሜት የጠብ ትንኮሳ በማድረግ አጋጣሚውን ያለ ጨዋታ ለማለፍ ሊጠቀሙበት ስለሚችሉ ኢትዮጵያዊያን እንዳንታለል አደራ» እያለ ነበር፡፡ ይሁንና ማንም ምንም ሳይሆን ነገሩ በሰላም ተጠናቋል፡፡

ከጨዋታው እና ከድሉ በኋላ ሲታሰብ ግን የመሰለ መንግሥቱ ዘገባ የጦርነት አዋጅ ያክል ነበር፡፡ ምክንያቱም ሱዳን ቢያሸንፈን ኖሮ አንድም የሱዳን ተጫዋች በሰላም ወደ ሀገሩ ይሸኝ ነበር ማለት ዘበት ነው፡፡ የመጀመሪያዋን ጎል ያስቆጠረው አዳነ ግርማ «ብንሸነፍ ኖሮ የሚደርሰውን ጉዳት ሳስብ ይዘገንነኛል» ያለውም ለዚህ ነው፡፡

## ታሪክን የኋሊት

ኢትዮጵያ ከሱዳንና ግብፅ ጋር መስርታው ከራቀችው የአፍሪካ ዋንጫ ለመጨረሻ ጊዜ የተለያየችው የዛሬ 31 ዓመት በሊቢያ በተካሄደው ሻምፒዮና ነበር፡፡ በወቅቱ ወደ ሊቢያ ያቀናንበትን የመጨረሻ ማጣሪያ ግብ አስቆጥሮ ያሳለፈን መሐመድ ኡስማን (ሚግ)ሲሆን የአዲስ አበባ ስታዲየም የአሁኑን ያክል በጭፈራ ሲናጥ እንደነበር የነበሩ ያስታውሱታል፡፡ ኢትዮጵያ የዛሬ 51 ዓመት በ1954 ዓ.ም ሶስተኛው የአፍሪካ ዋንጫ በእነ መንግስቱ ወርቁ አማካኝነት ወስዳለች፡፡ በ1973 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቡድን ለ10ኛው አፍሪካ ዋንጫ ወደ ሊቢያ ያመራውም በመንግስቱ ወርቁ አሰልጣኝነት ነው፡፡ በወቅቱ የነበረው ቡድን ጠንካራ እና የኢትዮጵያ ወርቃማው የእግር ኳስ ዘመን ተደርጎ የሚወሰድ ቢሆንም ቡድኑ ማጣሪያውን በድል ማጠናቀቅ ባለመቻሉ ከሻምፒዮናው የተሸኘው ገና በጠዋቱ ነበር፡፡ በምድብ ድልድሉ ከነበሩት ናይጄሪያ ጋር 3ለ0 ተሸንፎ፣ ከዛምቢያ ጋር 1ለ0 ተሸንፎ፣ ከአልጀሪያ ደግሞ 0ለ0 በሆነ ውጤት ተለያይቶ ነው ሻምፒዮናውን የተሰናበተው፡፡ በ4 የግብ እዳ እና 1 ነጥብ ብቻ ይዞ ነው ሊቢያን ለቆ የወጣው፡፡ ይሁንና ቡድኑ አሁንም ድረስ ስለ ጥንካሬው ይነገርለታል፡፡ አምበሉ ንጉሴ ገብሬም ዛሬ ድረስ የወርቃማው ዘመን ልጅ እየተባለ በየሚዲያው ይወደሳል፡፡ ከዚህ ሁሉ በላይ ግን ግጥምጥሞሹ ቀልብ ይስባል፡፡ የዛሬ 31 ዓመት ከኢትዮጵያ ጋር በምድብ ድልድል የነበሩት እነማን እንደነበሩ አስተዋላችሁ? በአሁኑ የደቡብ አፍሪካ ሻምፒዮና ከእኛ ጋር የተደለደሉት ራሳቸው ናቸው፤ ከአልጀሪያ በስተቀር፡፡ በእሷ ፋንታ ኮትዲቫር ነች ያለችው፤ ግጥምጥሞሹ አይገርምም?

## እግር ኳሳችን ያስመካል?

አሁን ወሳኙ ጥያቄ ላይ ደርሰናል፡፡ የተገኘው ድል እንዳስደሰተን ወደ ሻምፒዮናው መመለሳችን እንዳኮራን ሁሉ የቡድናችን አቋምም ሊያሳስበን ይገባል፡፡ እንደ እኔ እንደ እኔ ከሆነ የቡድናችን ብቃትና ችሎታ ከየትኛውም የአፍሪካ ሀገር የተሻለ ነው ለማለት ይከብደኛል፡፡ ስለዚህም ድሉ የተገኘው በእድል ነው እስከማለት እደርሳለሁ፡፡ በየትኛውም የዓለም ሻምፒዮና የሚጫወት ቡድን ከችሎታው እኩል እድል መኖሩን ያምናል፡፡ የአለማችን ሀያሉ ቡድን የማንችስተር ዩናይትድ አሰልጣኝ የሆኑት አሌክስ ፈርጉሰን ሳይቀሩ ከቡድን ጥንካሬ እኩል እድል ወሳኝ መሆኑን ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡ ስለዚህም የብሄራዊ ቡድናችንን ውጤት እድል አድርጎ ማሰብ ጨለምተኛ አያስብልም፡፡ ከዚህ በታች የማነሳው ሀሳብ ደግሞ ምን እያልኩ እንደሆነ በግልጽ ያስረዳልኛል፡፡

የኢትዮጵያ ቡድን በዘንድሮው የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ እንዲሳተፍ ከካፍ ጥሪ የቀረበለት እንደወትሮው በየሁለት ዓመቱ የሚካሄደውን የተናፋቂውን ሻምፒዮና መርሀ ግብር ተከትሎ አይደለም፡፡ ዘንድሮ 29ኛው የአፍሪካ ዋንጫ በደቡብ አፍሪካ እንዲካሄድ የተፈለገው የውድድር መርሀ ግብሩ ወደ ጎደሎ ቁጥር እንዲሻገር ተፈልጎ

[ወደ ገጽ 31 ዞሯል ]

# የብሄራዊ ቡድናችን ታዋቂው ግብ ጠባቂ ለማ ክብረት ...

ከገጽ 31 የዞረ


አስታውሳለሁ ከምድባችን በመጨረሻ የተጫወትነው ከአየር ኃይል ጋር ነበር። እነሱ ሁለት እድል ይዘው ነው የገቡት። ማሸነፍና ወይ እኩል መሆን ወደ አንደኛ ዲቪዚዮን ያስገባቸው ነበር። እኛ ደግሞ ማሸነፍ ብቻ ነበር እድላችን። ባጋጣሚ እኛ ጨዋታው ሊያልቅ ሲል አንድ አገባንና ስንፈነጥዝ ከጥቂት ደቂቃ በኋላ እነሱ ሪጎሬ አገኙ ፤ ተጫዋቾቻችን ሁሉ አዝነውና ተስፋ ቆርጠው ሳለ ሪጎሬውን አድኜ ተስፋችንን አለመለምኩት። ወደ አንደኛ ዲቪዚዮን ገባን፡፤ ይህ መቼም ከህሊናዬ የማይጠፋኝ ትዝታ ነው።

ከዚያም አንደኛ ዲቪዚዮን ገብተን 3 ወይም 4 ጨዋታ እንደ ተጫወትን ለብሄራዊ ቡድን ተመርጠን ወደ ሞርሽስ ሄድን። በዛው ጠፋን ማለት ነው።

**ኢ.ቶ** ሞርሽስ ላይ ከመጥፋታችሁ በፊት ባደረጋችሁት ጨዋታ እኩል ለኩል ሆናችሁ በፍጹም ቅጣት ምት እንድትለያዩ ሲደረግ ለማ ክብረት አንድ ታሪክ መስራቱን ዛሬም ድረስ አስታውሰዋለሁ፡፤ እስኪ ካንተው አንደበት እንስማው።

**ለማ** ልክ ነህ ሞርሽስ የሆነው ነገር ዛሬም ድረስ ይገርመኛል። ወደ ሞርሽስ የመጣነው ለመልስ ግጥሚያ ነበር። ከ15 ቀን በፊት አ/አ ላይ ተጫውተን እኛ 1 ለ ዜሮ አሸነፍናቸው። ሞርሽስ ላይ ደግሞ እነሱ 1 ለ ዜሮ አሸነፉን። እኩል ስለሆንን ሰአት ተጨመረ። አሁንም አልተሸናነፍንም፡፤ 5 አምስት ቅጣት ምት ተሰጠ፡፤ የቡድኑ አምበል የነበረው በዛ ጨዋታ ስላልተሰለፈ እኔ ደግሞ ምክትል ስለነበርኩ መጀመሪያ ለመምታት ዕጣ የተጣጣልኩት እኔ ነበርኩ; ። ዕጣው ለኛ ወጣ። አሰልጣኞችን መንግስቱ ወርቁ ነበር ፡፤ እኛ መጀመሪያ እንምታ ወይስ እነሱ ይምቱ ? ብዬ ጠየቅኩት ፡፤ እነሱ ይምቱ አለኛና እኔ ወደ ጎል ሄድኩ። መቱ አዳንኩት። ቀጥሎ ተስፋ ሚካኤል ዳኘው የኛን መታ እሱም ሳተ። ተስፋ ሚካኤል ሪጎሬ ሲመታ በጣም ጎበዝ ነበር ያን ቀን ግን ሳተ፡፤ ሄጄ አጠገቡ አጀሃ አጀሃ አይዞህ ብዬ ጀርባውን መታ አድርጌ አበረታትቼው ወደ ጎሎ ሄድኩ። እነሱ 2ተኛውን መቱ አሁንም አዳንኩት፡፤ ጎል ውስጥ ስቆም በጣም እንቆራጠጥና እዘል ስለነበር ይመስለኛል መቺዎቹ ይደናገጡ ነበር። አሁን የኛ 2ተኛው ተመታ አገባን። እነሱ 3ኛ መቱ አገቡ። አሁን 2 ለአንድ ሆንን፡፤ የኛ 3ኛ ተመታ ሳትን። አሁንም ሁለት ለአንድ ነን እኛ አንድ አድቫንቴጅ አለን። አራተኛው የነሱ ተመታ አሁንም አዳንኩ።

**ወደ ገጽ 34 ዞሯል።**



# ተወዳጁ የስፖርት ጋዜጠኛ ደምሴ ዳምጤ ...?

[ ከገጽ 14 የዞረ]

ደምሴ የጋዜጠኝነት ሙያን በመደበኛ ትምህርት አልተማረም። ኮሌጅ መግባት በሚችልበት ወቅት ነበር ቋሚ ሰራተኛ ሆኖ በጋዜጠኝነት የተቀጠረው። ይሁንና በግል ጥረቱ በተለያዩ መንገዶች ዕውቀቱን ለማሳደግ የሚጥር ሰው ነበር። ኢትዮጵያ ሬድዮ ሲቀጠር መጀመሪያ ሪፖርተር ነበር የሆነው። በሂደት ግን እስከ አዘጋጅነትና የፕሮግራም ሃላፊነት ድረስ መዝለቅ ቻለ።

ከ33 አመታት በላይ በቋሚነት ሲያገለግል በየክፍላተ ሃገሩና በመላው አለም በስራው የመንቀሳቀስ እድል ነበረው። አትላንታ፤ አቴንስና ቤጂንግን ጨምሮ የተለያዩ ኦሎምፒኮችን፤ የሻምፕዮና ሺፕ እና አገር አቋራጭ ውድድሮችን በቀጥታ ስርጭቶች አስተላልፏል። በድምሩ ከ30 በላይ አገራትን በስራው ምክንያት አዳርሷል።

በተለይም የቀጥታ ስርጭቶቹን ሲያስተላልፍ በከፍተኛ ሰሜት ተሞልቶ- እንደወረደ ስለሚያቀርብ ባድማጮቹ ልብ ውስጥ አገዝፎታል። የብሄራዊ አግር ኳስ ቡድናችን ወሳኝ ግጥሚያ ካለው ለደምሴ ከባድ ፈተና ነው። የምንሸነፍ ከመሰለ ደምጹ ሲሰል ፣ሃዘኑ አድማጮቹም ላይ ይጋባል። ወሳኝ ወጤት ማስመዝገብ ስንችልም እንዲሁ ደምሴ ሰሜቱን ያለገደብ ይለቀዋል።. . .ትንፋሹ ቁርጥ እስኪል። ህዝቡ ደግሞ ይወደዋል። ጭንቁ፣ ደስታው የምር ነውና።

ብዙዎቹ ስለደምሴ የኳስ ፍቅርና ስሜት ሲያስቡ በተለይ የሚታሰባቸው ታህሳስ 17 ቀን 1880 ዓ.ም ነው። በወቅቱ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ከዝምቧቤ አቻው ጋር ለፍጻሜ ዋንጫ ይጫወቱ ነበር። ያ ግጥሚያ ከምንግዜውም የተለየ ድባብ ነበረው።

. . .ጨዋታው ሊያልቅ አንድ ደቂቃ እንኳ የሚሆን ጊዜ አልቀረውም። የዝምቧቤ ብሄራዊ ቡድን 1ለ0 እየመራ ድሉን ሊያረጋግጥ አሰፍስፏል። ደምሴ ሲያቃስት፤ ሲያምጥ ቆይቷል። በርካታ ተመልካቾችም እንዲሁ ተሰፋ ቆርጠው ስቴድዮሙን ለቀው በመውጣት ላይ ናቸው። . . . ተአምረኛ አፍታ።

" አማኑኤል የእጅ ውርወራውን ወረወረ! ...." ንጉሴ ማስተላለፉን ቀጥሏል። «ሙሉኣለም ያሻገራትን ......ገብሬ ..ገብሬ ....ገብሬ በቴስታ.... 2 ቁጥሩ በራሱ ጎል .....» የደምሴ ጉሮሮ የሚሰነጠቅ መሰለ። ትንፋሹ ቁርጥ! ቁርጥ! . . . ስታዲዮሙ ተደበላለቀ። ከተማው፣ ገጠሩ ጩሀት በጩሀት ሆነ። ፌሽታ!!

. . .የፍጹም ቅጣት ምቱ ደግሞ የባሰውን ምጥ ነበር። ስንስት ጭንቀቱ ፤ ሲስቱ ተስፋው ።

የመጨረሻው የዚምቧቤ መቺ ገና ወደ ኳስ ሲያመራ በጭንቀት የተዋጠው ደምሴ "ውጪ! ውጪ! ውጪ! . . ." ሲል ተሰማ። መጸለዩ ነው። . . .እግዜሩም ሰማውና ኳሷ ጎል ሳትገባ ወጣች።

የፍጻሜው መቺ ዳኛቸው ደምሴ ጎል አስቆጥሮ ቡድናችን ዋንጫ መብላቱን ሲያረጋገጥ የነበረው የደምሴ ሁኔታ በአድማጮቹ እይምሮ ዛሬም ድረስ የሚያስተጋባ ይሆናል። " ዳኙ! ...ዳኙ ...ገላገለን! . . ." ያለው

አንዳንድ አድናቂዎቹ ለጤንነቱ በእጅጉ ይሰጉ ነበር። እንዲያው በስሜት ፣ በጭንቀትና በደስታ ልቡ ቀጥ እንዳትል ይፈራሉ። ግን ደግሞ እሱው ካላስተላለፈላቸው በቀር የሚረኩ አይመስሉም።

ደምሴ የሚወደደው በቀጥታ ስርጭቶቹ ብቻ አይደለም። ሰኞ ሰኞ ማታ የቅዳሜና የእሁዱን የከፍተኛ ዲቪዚዮን ጫዋታዎች በሚዳሳስበት ዘገባውም ይናፈቃል። በተለይ ደግሞ በልምድ በዳበረ እይታው የሚያቀርባቸው ግምገማዎች ፋይዳቸው የጎላ ነበር። ተጫዋቾችንና አሰልጣኞችን ጥንካሬአቸውን እያወደሰ ድክመታቸውን ደግሞ እንዲያርሙ ያመላክታል።ክለቦችና የስፖርት ፌዴሬሽኖችንንም እንዲሁ ተገቢ ትችት እየመገበ የሚጠነክሩበትን ጎን ሲመክር ኖሯል።

የኋላ ኋላ ግን የደምሴ ጤና እያስቸገረ መጣ። ሙሉ ግዜውን ለስራው ሰጥቶ የስኳር ህመሙን በተገቢው መከታተል ያለመቻሉ መዘዙ በዛ። እረፍት እንዲወስድ፣ በሽታውን እንዲያስታምም ቢመክሩትም " ስራዬን" እያለ በጅ እንዳላላቸው የ3 ልጆቹ እናት ባለቤቱ ወ/ሮ ጸሃይ መንግስቴ ተናግረዋል።

እራሱ ደምሴ እንደገለጸው ከሆነ የጤና ችግሩ እየተባባሰ የመጣው ከቤጅንጉ(28ኛው አኦሎምፒክ) መልስ ነበር። በተለይ የአይኑ ችግሩ ከፋ። ቀስ በቀስ የአንድ አይኑን ብርሃን ሙሉ በሙሉ፤- የሌላውን ደግሞ 80% አጣ። ሃኪሞቹም ከአቅማቸው በላይ መሆኑን ነገሩትና በአስቸኳይ ወደውጪ አገር ሄዶ ካልታከመ በቀር የቀረችው የአንድ አይኑ 20% የማየት አቅምም እንደምትጠፋ አስጠነቀቁት።

ይህ ለደምሴ ትልቅ ጭንቅት ነበር። እድሜውን በሙሉ የወር ደመወዝተኛ ሆኖ በጋለ ስሜትና ፍቅር ወገኑን ከማገልገሉ ውጪ የቋጠረው ቅርስ የሌለው ምስኪን ነው። በቀበሌ ቤት እየኖረ በታክሲ የሚጠቀም ባተሌ። ውጪ ሃገር ሄዶ ለመታከም አቅሙ እንደሌለው አምኖ ተኝቶ የሚመጣውን ከመጠበቅ በቀር የታየው አማራጭ አልነበረም።

በሚችለው ሁሉ ያገለገለው ህዝብ ሊደርስለት እንደሚችል ቢያውቅም ደምሴ ግን እርዳታ ጥየቃ አልወጣም። ይሉኝታ ክፉኛ የሚያጠቃው ነበርና አርፎ ተኛ። በኋላ ላይ ሁኔታው በጣም ያሳሰባቸው የሙያ ባልደርቦቹ አለምነህ ዋሴና ታምራት ሃይሉ (ቁምነገር መጽሄት) ነበሩ “ተኝተህማ አትሞትም” በሚል በራሳቸው ተነሳሽነት ችግሩን ለህዝብ ይፋ ያደረጉት።

. . . የኢትዮጵያ ህዝብም በሚያስደስት ወገንተኝነት የ40 አመት ውለታውን ከፈለ። የሚችለው በገንዝቡ፣ የማይችለው በጸሎቱ አለንልህ አለው። ደምሴ የህዝቡን ፈጣን ምላሽና ያሳየውን ፍቅር በኩራት ነበር የሚወሳው። “መንፈሴን ህዝቡ አጸናልኝ” እያለ።

ተክለ ብርሃን አምባዬ የተባለ የኮንስትራክሽን ድርጅት ባለቤትና ሼህ መሃመድ አላሙዲም በውጪ ሃገራት እንዲታከም ከፍትኛውን እገዛ ካደረጉ ስዎች መሃል የሚጠቀሱ ናቸው።

. . .ብርቱው ጋዜጠኛ በታይላንድ ያደረገው ህክምና ተስፋ ሰጪ ነበር። የቀረችው የአንድ አይኑ 20% የማየት አቅም እንዳትዳከምና ጭራሽኑ እንዳትጠፋ አስቆሙለት። በጊዜ ሂደት ትሻሽሎ 50% ያህል ሊመለስለት እንደሚችልም ነግረውት ነበር።

ግን የሕይወት ቀጠሮ ሆነና ከ13 አመት ለጋ እድሜው ጀምሮ በስፖርት ጋዜጠኝነት ወገኑን ሲያገለግል የኖረው ተወዳጁ ጋዜጠኛ ደምሴ ዳምጤ በተወለደ በ60 አመቱ ጥቅምት 26 ቀን 2005 ኢ.ም ከዚህ አለም ተለየን።

“ጤናዬ ከተመለሰ ወጣት ጋዜጠኞችን ከተሞክሮዬ እያካፈልኩ አቅጣጫ የማስያዝ ምኞት አለኝ” ያለን ውድ ሙያተኛ ላይመለስ ነጉዶ ድፍን አበሻን ሓዘን አለበሰው። ስራው ግን የማይሞት ሃውልቱ ነውና ሁሌም ሲታወስ ይኖራል። ደምሴ ዳምጤ ባለትዳርና የ3 ሴቶች አባት ነበር። መጽናናቱን ይስጣቸው።

——————-//——————

## ከ31 ዓመታት በኋላ ............[ከገጽ 31 የዞር .....]

### ኳስ እና ፖለቲካ

ኢትዮጵያ ከአለም አቀፍ ስፖርት መድረክ እየራቀች በደማቅ የተጻፈው ስሟም እየደበዘዘ የመጣው አመራሩ ስፖርት እና ፖለቲካን ለይተው በማያውቁ ሰዎች ስለተያዘ ነው፡፡ የብሔር ተዋፅኦ ለፓርላማ አባልነት እንጂ ለስፖርት ምንም የሚያበረክተው ፋይዳ የለም፡፡ ስፖርት የችሎታ ጉዳይ ነው፡፡ በተለይም እግር ኳስ፡፡ እኛ ሀገር ግን የክልል እና የብሔር ተዋፅኦ ይሉናል፡፡ በዚያ ላይ «እርስ በርሳቸው ውስጥ ውስጡን ተቀጣቅጠው ሲያበቁ» የፌዴሬሽን ምርጫ፣ የአሰልጣኝ ለውጥ እያሉ ስፖርቱን ይገድሉታል፡፡ ይህ ሁሉ አልበቃ ሲላቸው ደግሞ አንዲት ቀን እንኳን ስታዲየም ገብቶ ለማያውቅ የስታዲየሙን ሜዳ በከፉም በደጉም ለማያውቀው ሰው የድሉን መታሰቢያ በስሙ ይሰይሙለታል፡፡ ይሰይሙለትና በዚያን የሚያክል ሞቃት ሀገራዊ ደስታ ላይ ቀዝቃዛ ውሃ ይቸልሱበታል፡፡ «በእግር ኳሳችን የተገኘው ስኬት ለቀጣይ የህዳሴ ጉዟችን የሞራል ስንቅ ነው» እያሉ ደግሞ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻቸው መጠቀሚያ ያደርጉታል፡፡

አልፈውም «ድሉ የመልካም አስተዳደር ውጤት» መሆኑን ሲነግሩን ይቃጣቸዋል፡፡እነዚህ ናቸው እንግዲህ ኳሳችንን የሚመሩት፤ በእነርሱ እየተመራም ነው ደቡብ አፍሪካ ላይ ለውጤት እንዲበቃ የሚጠበቀው፡፡ እነ ይድነቃቸው ተሰማ፣ እነ መንግስቱ ወርቁ ህይወታቸውን የከፈሉለት ኳስ እንዲህ መሆኑን ቢያውቁ ምን ይሉ ይሆን?

### ማጠቃለያ

ከ31 ዓመት በኋላ ዋልያዎቹ ወደመሰረቱት ሻምፒዮና ተመልሰዋል፡፡ በእድልም ያግኙት በችሎታ ለዘመናት በቁጭት ተውጦ የነበረው ምኞት እውን ሆኗል፡፡ በዚህም መላው የኢትዮጵያ ህዝብ እስካሁን ደስታውን በመግለጽ ላይ ይገኛል፡፡ የቻለ ተጫዋቾቹን እየሸለመ ይገኛል፡፡ ከደቡብ አፍሪካ በድል ከተመለሱ ለእያንዳንዱ ተጨዋች ባለሁለት መኝታ ኮንደሚኒየም ቤት እና በጋራ የሚከፋፈሉት 11 ሚሊየን ብር ስጦታ ከየቦታው እንደሚሰጥ ቃል ተገብቷል፡፡ ቁጥር አንዱ ባለሀብትም 5 ሚሊየን ብር ሰጥተዋል፡፡ሊፋን ሞተርስ ጎል ላገቡት 2 ተጫዋቾች 10 ሺህ ብር ለእያንዳንዳቸው አበርክቷል፡፡

ኢንጅነር ተክለብርሃን አምባዬ በበኩላቸው ለሁሉም ተጫዋቾች 25 ሺህ ብር በነፍስ ወከፍ አበርክተዋል፡፡ሌሎችም እንደ የአቅማቸው እየሸለሙ ነው፡፡ ይህ ሁሉ እንግዲህ በተገኘው ድል ኮርተናል፤ በቀጣይም ለውጤት እንድትበቁ አደራ የሚል መልእክት ያለው ነው፡፡ አሰልጣኙ ሰውነት ቢሻው ከድሉ እና ሽልማቶቹ በኋላ «ሁሉም ኳሳችንን በመደገፍ የተሻልን እና ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረስን ለማድረግ በተነቃቃ ስሜት ሊያግዘን ይገባል፡፡ ከደስታው በኋላ በቀጥታ ወደ ስራ ገብተናል፣ ከፊታችን ትልቅ ውድድር አለብን ለዚያ ጠንካራ ዝግጅት ጀምረናል፡፡ እስካሁን ባለው ሁኔታም ከጊኒ ብሔራዊ ቡድን ጋር የአቋም መለኪያ ጨዋታ ለማድረግ እየተነጋገርን» ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡ሁለተኛዋን ግብ ያስቆጠረው ሳላህዲን ሰኢድ በበኩሉ «በአፍሪካ ዋንጫ ህዝባችንን የምናስደስትበት ሌላ ትልቅ ውጤት ለማምጣት ጠንክረን እየሰራን ነው» ሲል የመጀመሪያዋን ጎል ያገባው አዳነ ግርማ «የሁሉም ኢትዮጵያዊ ድጋፍ ካልተለየን እየሰራን ያለነው ልምምድና ውስጣችን የተፈጠረው መነቃቃት በርግጥ ለውጤት የሚያበቃን ነው» ብሏል፡፡ በአዲስ አበባው ጨዋታ ኳሷን ለማዳን ሲወረወር በአንገቱ ላይ ጉዳት የደረሰበት ግብ ጠባቂው ጀማል ጣሰው ደግሞ «በጨዋታው ወቅት ሰዓት ለመፍጀት የተጎዳሁ መስዬ ሁለት ደቂቃ እተኛለሁ ብዬ ነበር ወደ ሜዳ የገባሁት፤ ነገር ግን ለውሸት ያሰብኩት የእውነት ሆኖ በዚያው ተኝቼ ቀረሁ» ብሏል፡፡ በቀጣይ በሚኖረው ዋናው የአፍሪካ ሻምፒዮና ሙሉ ጤነኛ ሆኖ እንደሚደርስ እና እስከዚያው በደንብ እንደሚድን በሀኪሞቹ የተነገረው መሆኑንም ገልጧል፡፡

### ምኞት

ብሔራዊ የእግር ኳስ ቡድናችን በ29ኛው የአፍሪካ ዋንጫ ያልተጠበቀ ውጤት አስመዝግቦ በያለንበት እንዳለፈው ያስጨፍረን፣ ያስፈነጥዘንና፣ በደስታ ጮቤ ያስረግጠን ዘንድ ጥልቅ ምኞታችን ነው፡፡ ——///——

የኢትዮጵያን ኮሚኒቲ አማርኛ ሬድዮ ፕሮግራም

ዘወትር ዓርብ ምሽት እንደ ኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር ከምሽቱ 3 ሰዓት እስከ 4 ሰዓት ከ3CR ሬድዮ ጣቢያ በ855 ኤ ኤም ላይ በአማርኛ ቋንቋ ይተላለፋል።

3CR RADIO 855 AM

[ከገጽ 27 የዞር .....]

# ከ31 ዓመታት በኋላ ......

ነው፡፡ሻምፒዮናው በየዓመቱ የሚካሄደው የሙሉ ቁጥር ዓመቶችን እየተከተለ ማለትም በ2000፣2002፣2004፣2006... ወዘተ እያለ በመሆኑ አንደኛው አልፎ አንደኛው ሲመጣ ከአለም ዋንጫ ጋር ይጋጫል፡፡ ለምሳሌ ያህልም ባለፈው ዓመት አፍሪካ ዋንጫ እና አለም ዋንጫ በተቀራራቢ ጊዜ በአንድ ዓመት ውስጥ ተከናውነዋል፡፡ ይህ ደግሞ በተለይም በአውሮፓ በሚጫወቱ የአፍሪካ ልጆች ላይ ከፍተኛ ጫና እያሳደረ እና አንዳዴም ከፊፋ ደንብና መመሪያ ጋር እንዲጋጩ እያደረገ በመሆኑ ካፍ ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት አፍሪካ ዋንጫን በጎደሎ ቁጥር ዓመት እንዲከናወን ውሳኔ አሳልፏል፡፡ በመሆኑም ዘንድሮ (2013) ውድድሩ ሻምፒዮናው በተከናወነ በዓመቱ እንዲዘጋጅ ሲያደርግ ኢትዮጵያ ማጣሪያውን ከቤኒን እና ሱዳን ጋር እንድታድርግ ቀለል ያለ እድል ሰጥቷታል፡፡ እናም እዚህ ጋር እድል አንድ ይሏል፡፡ሌላው አስገራሚ እድል ኢትዮጵያ ካደረገቻቸው አራት የማጣሪያ ጨዋታዎች አንዱን ብቻ አሸንፋ ወደ ሻምፒዮናው ማለፏ ነው፡፡ ከቤኒን ጋር ቤኒን ላይ የነበረውን ጨዋታ 0ለ0 ነው የተለያየችው፡፡ ቤኒኖች እዚህ መጥተው 1ለ1 ነው ጨዋታው ያለቀው፤ ሱዳን ላይ ሱዳን 5 ኢትዮጵያ 3 ሆነው ተለያዩ፡፡ አዲስ አበባ ላይ 2 ለዜሮ እድል ተገኘ፡፡
የሁለቱ ቡድኖች ውጤት እኩል ሶስት ለሶስት ነው፡፡ ግባቸውም አምስት አምስት ነው፡፡ኢትዮጵያ ሰው አገር ግብ ባገባ በሚለው የፊፋ ህግ ተዳኝታ እንጂ ውጤቱ እኩል ነው፡፡እና ይሄስ እድል አይደለም? የእኛ ቡድን ከሱዳን አቻው ጋር የመጀመሪያውን ጨዋታ ያደረገው ሱዳን ላይ ነው። ማጣሪያውን ከሱዳን ጋር እንደምናደርግ በተነገረ ጊዜ የመጀመሪው ጨዋታ በኢትዮጵያ እንዳይሆን ፌዴሬሽናችን ሎቢ እስከማድረግ ደርሶ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው፡፡ የመጀመሪያው ጨዋታ አዲስ አበባ ላይ እንዳይሆን የተፈለገው ወቅቱ የክረምት ወቅት (ጳጉሜ) በመሆኑ በገዛ ዝናባችን ተጠልፈን እንዳንወድቅ ተፈርቶ እንደነበረም እናስታውሳለን፡፡ «እና ጳጉሜ ቢሆንስ?» የሚል ጠያቂ ካለ ደግሞ መልሱ ይሄ ነው። አንደኛ በዝናብ በሚከናወን ጨዋታ ተፈላጊውን ውጤት ለማግኘት አይቻልም፤ምክንያቱም ዝናቡ አያጫውትም በዚያ ላይ የእኛ ተጫዋቾች አቅመ ደካሞች በመሆናቸው ዝናብ ባዘለ ሜዳ ላይ ኳስ መግፋት አይችሉም፡፡ የአየሩን ግፊት የሚቋቋሙበት ፈርጣማ ጡንቻም የላቸውም፡፡ ባለፈው የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ የመጀመሪያ ግጥሚያ እለት አበበ ቢቂላ ስታዲየም ላይ በጊኒ 4ለ1 የተሸነፍነው ዶፍ ዝናብ በመውረዱ ነው፡፡ ስለዚህ ጨዋታው በሱዳን እንዲሆን መፈለጉ ተገቢ ነው፡፡ ይሁንና ይህም ቢሆን በእጣ የሚወሰን ሆነና እጣ እንዲወጣ ተደረገ፡፡ እጣው ደግሞ ጨዋታው ሱዳን ላይ እንዲከናወን ወሰነ፡፡ እናም በሱዳን የጠራ ሰማይ ስር 3 አገባን፡፡እዚህ አዲስ አበባ ክረምቱ አልፎ ነበርና በጠራ ሰማያችን ስር 2 ለማግባት ቻልን፡፡ በእኛው አየር፣ በእኛው ህዝብ መካከል እድላችንን ወሰንን፡፡ እና ይሄስ እንደ እድል አይቆጠር ይሆን? ለዚህ የእድል ሀሳብ ንኡስ ርእስ የሆነው ነጥብ **«በርግጥ እግር ኳሳችን ያስመካል ወይ?»** የሚለው ነው፡፡ እድል የፈጠረው አጋጣሚ ጥንካሬ እና ብቃትን ሊደርብ ይገባዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ የፌዴሬሽኑ አመራርና ሁሉም የስፖርት ቤተሰብ የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ ይገባዋል፡፡ [**ወደ ገጽ 30 ዞሯል**]

# ታዋቂው የብሄራዊ ቡድናችን ግብ ጠባቂ ለማ ክብረትና አስደናቂው የሞርሽስ ትዝታው


ለማ ክብረት

**ኢ.ቶ** ጤና ይስጥልኝ ለማ በቅድሚያ ስለ ግዜህ አመስግናለሁ። ዛሬ በትዝታ ላስጉዝህ ነው። ረዥም አመታት ወደ ኋላ ሄደህ ከኳስ ጋር የነበረህን ፍቅር እንድትገልጽልን ነው።

**ለማ ክብረት፡-** እኔም ስለ ተሰጠኝ እድል አመሰግናለሁ። አዎ ከኳስ ጋር የነበረኝ ፍቅር እንደማንኛው ኢትዮጵያዊ በጨርቅ ኳስ ነው የጀመርኩት።ሰፈር ውስጥና ት/ቤት እንጫወት ነበር። ከፍ ስል ማለትም 14 ና 15 ዓመት ሲሆነኝ በግዜው ኤሌትሪክ የሲ ቡድን ይመርጣል ሲሉኝ ወደዛ ሄጄ ሞከርኩ፡፤ በበረኛነት ነበር የሞከርኩት። ከኔ ጋ 4 በረኞች ነበርን እና እኔ ትንሽ ቁመቴ አጠር ስለሚል ነው መሰለኝ አንቺ ስታድጊ በሚቀጥለው አመት ነይ ተባልኩ። አስታውሳለሁ አቶ ወንድሙ በቀለ እንድገባ ሞክረውልኝ ነበር። ግን 3 በረኞች ስላሉ 4ኛ ማስገባት አልችልም አለ አሰልጣኙ። በበረኛ አልሆን ሲለኝ በተጭዋችም ሞክሬ እሱም አልሆን አለ። በብስጭት ወደ ቤቴ ሄድኩ ፡፤

ከዛ በኋላ ሰፈር ውስጥ መጫወቴን ቀጠልኩ። ባጋጣሚ አንድ እንግሊዝ ስኩል የሚማር የሰፈራችን ልጅ ነበር። ኤሌትሪክ ሲ ሞክሬ እንዳልተሳካልኝ ስነግረው ፡ ቆይ እስኪ ጋሽ ታደሰን እጠይቅልሃለሁ አለኝ። ጋሽ ታደሰ መኩሪያ በዛን ግዜ የበራሪን ሲ እያሰለጠነ የእንግሊዝ ስኩልም አስተማሪ ነበር። ልጁ እንዳለው ጠየቀልኝንና ና ተባልኩ። ሄድኩ። የእድል ነገር ሆነና ጋሽ ታዴ ለበራሪ ሲ እንድጫወት አደረገኝ በጣም ደስ አለኝ።

በራሪ ሲ መጫወት ጀመርኩ። የሚገርምህ ገና ነሽ እደጊ ተብዬ ከተመለስኩበት ከኤሌትሪክ ጋር ተጫወትንና 2 ለ አንድ አሸነፍናቸው። ሁለቴም 2 ለ 1 አሸነፍናቸው ፡፤ በዚህ ግዜ ሲራክ ገብረ መድህን የሚባል ተጫዋች የኤሌትሪክ አሰልጣኝ የነበረውን ጋሽ ታደሰን ፤ አየህ ጋሽ ታዴ ያኔ እንቢ ብለኸው እንዴት ጎበዝ እንደሆነ ብሎ አስታወሰው።የዛን ቀን ደግሞ በጣም ጥሩ ነበር የተጫወትኩት ።

ከዚያ ሁለት አመት ሲ ተጫውቼ ቢ ሳልጫወት በቀጥታ ኤ ቡድን ገብቼ መጫወት ጀመርኩ። ኤ እየተጫወትኩ ያኔ የኢህአፓ ግዜ ሁሉም ነገር ሲቆም በራሪም ፈረሰ። ተጫዋቾችም በየልዩ ልዩ ድርጅቶች ስራ እየገባን ለድርጅቶቹ መጫወት ጀመርን፡፤ እኔና ሉቾ ፊያት ነበር የተቀጠርነው፡፤ በኋላም አዲስ የቡድን አደረጃጀት ተብሎ የመኢሰማ ቡድን ሲመሰረት ፊያት ወደ እርምጃችን ነበርና ምድቡ እኛም እርምጃችን ገባን። እርምጃችን 3 አመት እንደተጫወትን ሌላ አዲስ የቡድኖች አደረጃጀት ተብሎ ወደ አንደኛ ዲቪዚዎን ለመግባት 52 ቡድኖች ሲወዳደሩ እርምጃችን የነበርነው ተጫዋቾች ተሰባስበን ባህር ትራንዚት ክለብን አቋቁመን ተወዳደረን። ከ52ቱ ቡድኖች 12 ብቻ አንደኛ ዲቪዚዎን ስለሚገቡ ውድድሩ በጣም ጠንካራ ነበር፡፤ አንደኛ ዲቪዚዮን ካልገባህ ደግሞ ለብሄራዊ ቡድን የመመረጥ እድል ስለማይኖርህ ለማለፍ መሟሟት አለብህ። **ወደ ገጽ 28 ዞሯል**

# ቅኝት በብሄራዊ የእግር ኳስ ቡድናችን ዙሪያ

ጥቅምት 4 ቀን 2005 ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ የሱዳን ተቀናቃኙን ሁለት ለቀለበት አሸንፎ ለአፍሪካ ዋንጫ ማለፉን ያረጋገጠው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ለደጋፊው ሕዝብ ያጎናጸፈው ደስታ በቀላሉ ሊገለጽ የማይችል እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡ ከሌሊቱ 10 ሰዓት በፊት ጀምሮ የካምቦሎጆን ዙሪያ ሲያጨናንቅ የነበረው ኳስ አፍቃሪ ኢትዮጵያዊ፤ስታዲዮሙ ከሚችለው ቁጥር በላይ "ቦታ አገኛለሁ ..." ብሎ በአካባቢው ፈስሶ እስከ ቀኑ 8፣9፣10፣11...ሰዓት ድረስ ቁር ፀሐይ ሲፈራረቅበት መቆየቱ፤የደቡብ አፍሪካውን ውጤት ጭምር በመናፈቅ....መሆኑ አሌ አይባልም፡፡ አለበለዚያማ እንደው "ለአፍሪካ ዋንጫ አልፈናል..." ማለቱ ብቻ ምን ፋይዳ ይኖረዋል?

እንግዲህ ያን የደቡብ አፍሪካ ተጋድሎ ለማየት ሌላ ጉጉት፣ሌላ ተስፋ...ተሰንቋል፡፡ ለዚህም ነው በግብጽ የሚገኘውን ሳለሃዲን ሰዒድን ጨምሮ 29 ዕጩ የብሔራዊ ቡድን ተጫዋቾች ተጠርተው ታህሣስ 1 ቀን 2005 ዓ.ም ስልጠና በአዲስ አበባ ስታዲዮም የተጀመረው፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን በደሌ ቢራ ፋብሪካን የሸመተው ዝና ብዙው ቢራ ጠማቂ ኩባንያ ሄኒከን፤ በታሪክ ለመጀመሪያ ግዜ ብሔራዊ ቡድናችንን በ24ሚሊዮን ብር ለሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ስፖንሰር ያደረገው፡፡ የሆላንዱ ኩባንያ ሄንከን ረቡዕ ታህሣስ 3 ቀን 2005 ዓ.ም በሂልተን ሆቴል ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጥ "በበደሌ ቢራ" ስም ዋሊያዎቹን ስፖንሰር ያደረገበትን ድርጊት "የሚያኮራኝ ተግባር ነው..." ብሎታል፡፡ በኢትዮጵያ የሄኒከን በደሌ ቢራ ፋብሪካ የቦርድ ሊቀመንበር ሚስተር ጀን ዶዬር " ዛሬ ጉሬዛና ዋልያ ለመረዳዳት ቃል የገቡበት ዕለት በመሆኑ ኩራት ተሰምቶኛል፡፡ እንደምታውቁት ጉሬዛ የበደሌ ቢራ መለያ ሲሆን፤ ዋልያም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን መለያ ነው፡፡ እኔ ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ ከመጣሁ በኋላ ጉሬዛና ዋልያ የተረዳዱበትን አንድ ተረት አውቅ ነበር..." ሲል ተሰምተዋል፡፡ ( ሊግ ጋዜጣ በታህሣስ 6 ቀን 2005 ዓ.ም ዕትሙ እንደዘገበው) ግን ግን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን በአፍሪካ ዋንጫ በተመደበበት የዛምቢያ ፣የናይጄሪያ... ክለቦች የሚገኙበት ምድብ ምን ይጠበቅበታል? ለሚለው የየሱፍ ሳሌህ፣የሽመልስ በቀለ፣የሰላህዲን ሰይድና የአቶ ሳህሉ ገ/ወልድ ምላሽ የሚከተለው ነው፡-

**1ኛ፡- የሱፍ ሳሌህ፡፡** ለስዊድን ወጣት ብሔራዊ ቡድን የመሰለፍን ዕድል ያገኘና በዚያው በስዊድን "ሲሪያሲንካ" የተባለው ክለብ ተሰላፊ ነው፡፡ እሱ " የእኛ ተጨዋቾች ያላቸውን ሁሉ ለመስጠት ከተዘጋጁና ጠንክረው ከሠሩ፤በተመደቡበት ምድብ የተሻለ ውጤት የማያስመዘግቡበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም፡፡ለዚህ ደግሞ የዛምቢያ ክለብ ጥሩ ምሳሌ ይመስለኛል፡፡ የዛምቢያ ቡድን ዋንጫ ይወስዳል ብሎ ቅድሚያ ግምት የሰጠው አልነበረም፡፡ ሆኖም ዋንጫውን ማንሳት ችሎአል፡፡ ስለሆነም በፉክክሩ የማይጠበቅ ውጤት ማስመዝገብ እንደምንችል ነው የማስበው፡፡...በበኩሌ የሃገሬን ብሔራዊ ቡድን የምጠቅም ተጫዋች ለመሆን እጥራለሁ" ብሎአል፡፡

**2ኛ፡-ሽመልስ በቀለ፡-** ከብሔራዊ ቡድናችን በጣም ወጣቱ ተጫዋች ነው፡፡ ዕድሜውም ሃያ ሦስት፡፡ ሽመልስ፡-" የተሻለ ዝግጅትና ተደጋጋሚ የወዳጅነት ጨዋታዎች አድርገን ራሳችንን መፈተሽ ከቻልን፤ታሪክ ማስመዝገብ የምንችል ቡድን መሆናችን አይቀርም..." በማለት "ቤስት ስፖርት" ለተሰኘው መጽሔት የጥቅምት ወር 2005 ዓ.ም ዕትም በሰጠው አስተያየት ግልጽ አድርጓል፡፡

**3ኛ፡-ሰላሃዲን ሰይድ፡-** አሁን በግብፅ የሚገኘውና ከሳምንት በፊት ኒካ (ቀለበት) ያሰረውና ከአፍሪካ ዋንጫ በኋላ ጋብቻውን ለመፈጸም ዕቅድ ያያዘው የብሔራዊ ቡድናችን ዋንኛው አጥቂ ሰላህዲን፡- "ዛሬ ላይ ሆኜ ስለደቡብ አፍሪካ ዋንጫ ማሰቡ አስቸጋሪ ነው፡፡ ቢሆንም ብሔራዊ ቡድናችን በደቡብ አፍሪካ ዋንጫ የተሻለ ተሳትፎ አሳይቶና ጥሩ ውጤት አስመዝግቦ ሊመለስ ይችላል የሚል ተስፋ አለኝ..." ሲል "በተመሳሳይ መጽሄት" ለተሰኘው መጽሔት የጥቅምት ወር 2005 ዓ.ም ዕትም አስተያየቱን ሰጥቷል፡፡

**4ኛ፡-አቶ ሳህሉ ገበረ ወልድ፡-** ሰውዬው የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዝደንት ናቸው፡፡ " ብሔራዊ ቡድናችን አቅሙ በፈቀደው መጠን አስገራሚ ሁኔታዎችን በደቡብ አፍሪካ መፍጠሩ አይቀረም፡፡ ይህን የምለው ለፉከራ ያህል አይደለም፡፡ ወደዚያ ለተሳትፎ ብቻ አይደለም የምንሄደው፡፡ ባለን ችሎታና አቅም ሁሉ አስደናቂ ተሳትፎ ለማሳየት ቁርጠኞች ነን..." ሲሉ፤ ረቡዕ ታህሣስ 3 ቀን ፤ የሄኒከን በደሌ ቢራ ፋብሪካ ለብሔራዊ ቡድናችን የ24 ሚሊዮን ብር ስፖንሰር ለመሆን በሂልተን ሆቴል ቃል-ኪዳን በገባበት አጋጣሚ ተሰምተዋል፡፡

## እነማን ከየትኛው ክለብ ተጠሩ?

**ሀ. ከኢትዮጵያ ቡና፡-** ጀማል ጣሰው፣ ዳዊት እስጢፋኖስ
**ለ. ከአርባ መንጭ፡-** ሙሉዓለም መስፍን
**ሐ. ከመከላከያ፡-** መድኃኔ ታደሰ
**መ. ከሰበታ ከነማ ፡-** ደረጀ ዓለሙ
**ሠ. ከሙብራት ኃይል፡-** አሥራት መገርሳ
**ረ. ከሲውድን ክለብ፡-** የሱፍ ሳሌህ
**ሰ. ከጀርመን ክለብ፡-** ዴቪድ በሻህ
**ሸ. ከግብፅ ክለብ፡-** -ሰላሃዲን ሰይድ
**ቀ. ከደደቢት፡-** ሲሳይ ባንጫ፣ ብርሃኑ ቦጋለ፣ዓይናለም ኃይሉ፣ስዩም ተስፋዬ፣ አክሊሉ አየነው፣ ጌታነህ ከበደ፣ ምንያህል ተሾመ፣ በኃይሉ አሰፋ፣ አዲስ ህንፃ
**በ. ከቅዱስ ጊዮርጊስ፡-** ዘሪሁን ታደለ፣ አሉላ ግርማ፣ ደጉ ደበበ፣ ቢያድግልኝ ኤልያስ፣ ያሬድ ዝናቡ፣ አበባው ቡጣቆ፣ ሽመልስ በቀለ፣ አዳነ ግርማ፣ ኡመድ ኡኩሪ፣ ፍፁም ገብረማርያም ናቸው፡፡

# ለፈገግታ .....

[ከገጽ 25 የዞረ]

## ዱለኛው ግብ ጠባቂ


ጌታቸው አበበ

ጌታቸው ዱላ ለረጅም ጊዜ ለጊዮርጊስ ተጫውቷል፡፡ ለህፃናት ቡድን የመለመሉት ይድነቃቸው ነበሩ፡፡ አጥቂ ነበር፡፡ በረኛ ሁን ሲሉት እምቢ ብሎ ሄደ፡፡ ሳይመጣም ቀረ፡፡ ይድነቃቸው ሰው ላኩበት ዱላም መጣ፡፡ በአጥቂነትም ለመቀጠል ነው፡፡ እሳቸውም እንዲህ አሉት፡፡ « አጥቂ መሆን ጥሩ ነው፡፡ ነገር ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ አጥቂ አለ፡፡ ለረጀም ጊዜ መጫወት ከፈለክና ታዋቂ ሆነህ ብሔራዊ ቡድን ለመግባት በረኛ ብትሆን ይሻልኃል አሉት» እሱም በሀሳቡ ተስማማ፤ ታዋቂም ሆነ፡፡ ጌታቸው በአንድ ወቅት በሊብሮ ጋዜጣ ቃለምልልስ ተደርጎለት ስለ ጋሽ ይድነቃቸው የተናገረውን ገጠመኝ ቀንጭቤ አቅርቤላችኋለሁ፡፡

**ሊብሮ፡-** ናይት ክለብ ረብሻ ተነስቶ ታስረህ ታውቃለህ?

**ጌታቸው፡-** በጣም እንጂ ባይገርምህ ናይት ክለብ ረብሻ ተነስቶ ሰው ተደብድቦ ፖሊስ ከመጣ ቀድመው የሚይዙት እኔን ነው፣ ረብሻው ሌላ ቦታ ቢሆንም እኔ ባልጣላም «ወይ ረብሸሀል ወይ እንዲረብሽ ቀስቅሰሃል፣ ወይም አደባድበሃል» ብለው ይይዙኛል፡፡ እንዳውም የተደበደባ ሰው ከፖሊስ ጋር መጥቶ እርሱ አልመታኝም ቢልም ፖሊሶች ለሰውየው አንተ የመታህን አታውቅም ማለት ነው ብለው እኔን ይይዛሉ፡፡ በፐርሰንት እንዴት እንደምገልጽልህ እንጃ እንጂ ለሊት ላይ በብዛት በሚነሳው ረብሻ ፖሊሶች እኔን ይዘው ወደ ጣቢያ ነው የሚሄዱት ብዙ ጓደኞቼ እንዳውም ጌታቸው የት ሄደ ሲሏቸው ወደ ቤቱ ሊያድር ሄደ ይላሉ፣ ጣቢያውን ቤቴ አድርገውታል፡፡

★ ★ ★

ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የአለም ዋንጫ ማጣሪያ ያደረገችው በ1953 ነው፣ የተጋጠመችው ከእስራኤል ጋር ነው፡፡ የአዲስ አበባ ስታዲየም በጥገና ላይ ስለነበረ ሜዳውም ስለታረሰ ማጫወት አልቻለም የደርሶ መልሱ ጨዋታ እዚያው እስራኤል ውስጥ እንዲካሄድ ተወሰነ፡፡ አበበ ቢቂላ ያሸነፈበት አመት ስለነበረ በእግር ኳሱም ታሪክ እንሰራለን ብለው ሄዱ ለቡድኑ ትጥቅ ያመጣው አበበ ቢቂላ ነበር፣]

★ ★ ★

ኢትዮጵያ ውስጥ ሁለት የእግር ኳስ ኢንስትራክተሮች በካፍና በፊፋ ተሹመዋል፡፡ ሥራውም በአፍሪካ ውስጥ እየዞሩ አሰልጣኞችን ማስተማር ነው፡፡ ከሁለቱ ቀድሞ ሹመቱን ያገኘው መንግሥቱ ወርቁ ሲሆን ጊዜውም 1970ዎቹ መጀመሪያ ነው፡፡ ካሣሁን ደግሞ የተሾመው በ1980ዎቹ አጋማሽ ነው፡፡ መንግሥቱ ወርቁ ከዚህ አለም በሞት ተለየ፡፡ ካሣሁንም ኑሮውን በአሜሪካ ለማድረግ ሄዷል፡፡ ኢትዮጵያ አሁን ምንም ኢንስትራክተር የላትም፡፡

★ ★ ★

በኢትዮጵያ ሻምፒዮና ኮከብ ተጫዋቾ ሽልማት በህጋዊነት የተጀመረው በ1976 ዓ.ም ነው፡፡ ከዚያ በፊት የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ኮከቦችን መርጦ አይሸልምም ነበር፡፡በ1976 ዓ.ም ሽልማት ሊጀመር የቻለው ተጫዋቾችን መሸለም ፈልገው ሳይሆን ከ3 ወራት በኋላ የኢ.ሠ.ፓን ምስረታ ምክንያት በማድረግ ፌዴሬሽኖች ልዩ ዝግጅት ያድርጉ ተባለ በዚህ የተነሳ የዋንጫው ስያሜና ለሽልማት የተዘጋጁት ሜዳሊያዎች « የ10ኛው አብዮት በዓልና የኢ.ሠ.ፓ ምስረታ» የሚል ጽሁፍ ታትሞባቸው ነበር፡፡ፌዴሬሽኑ ለየት ያለ ነገር ማቅረብ አለበት ስለተባለ ባለቀ ሰዓት ውድደሩ በተገባደደበት ጊዜ ለምስረታው ድምቀትና ለበዓሉ ልዩ ፕሮግራም «ኮከብ ተጨዋቾና ግብ አግቢ እንሸልማለን» በሚል አሳወቁ፡፡ እናም ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያ ኮከብ ተጫዋቾች ምርጫ ተደረገ፡፡በ1976 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሻምፒዮናው ሲጠናቀቅ በኮከብ ተጫዋችነት ለመሸለም 3 ተጫዋቾች በእጩነት ተያዙ፡፡ ከድሬዳዋ ጨርቃጨርቅ ዳኛቸው ደምሴ ፣ ከመድን አብይ ነጋሽ ፣ ከምድር ጦር ሙሉጌታ ብርሃኔ ነበሩ፡፡የኮከብ ተጨዋችነቱን ምርጫ ለዳኛቸው ደምሴ እንዲሰጥ ተወሰነ፡፡ እሱ ሲሸለም በስታዲየም የነበረው ተመልካች ድጋፉን በሙሉ በጭብጨባ ነበር የገለጸው፡፡ የተሰጠው ደብዳቤ ነው፤ ሽልማቱ ምን እንደሆነ ስላልታወቀ ብዙ ቀን ወደ ፌዴሬሽን ተመላለሰ፡፡ በመጨረሻም ግምጃ ቤት ተጠርቶ እግሩ ረጅም ኮቱ ደግም በጣም ሰፊ የሆነ ቱታ ተሰጠው፡፡ ዳኛቸው ሰውነቱ ቀጠን ያለ ነው፣ ቱታው ደግሞ ሰፊ ሲሆን ዳኛቸው የቱታውን ጃኬት አድርጎ ሲቀመጥ ድንኳን ውስጥ ያለ ነው የሚመስለው፡፡ ************************

# የአፍሪካ የስፖርት አባት ...

ከገጽ 13 የዞረ

ከአቶ ይድነቃቸው ተሰማ አኩሪ አህጉራዊ ተግባራት አንዱ በዘረኛዋ ደቡብ አፍሪካ ላይ በግንባር ቀደምትነት እንዲወሰድባት ያደረጉት ማዕቀብ አይነተኛ ሆኖ ሁሌም የሚዘከር ብቻ ሳይሆን ይድነቃቸው የደቡብ አፍሪካ ህዝብ ከአፓርታይድ አገዛዝ ለመውጣት በሚያደርገው ትግል ውስጥ ከጎኑ በመቆም ያሳዩት ጥንካሬና ቆራጥነት የሀገራቸው የኢትዮጵያ የቀዳማዊ ሃይለ ሥላሴ መንግሥት የማያወላውል ድጋፍ ያለቸው ነበርና በእሳቸው ትግል

በመንግሥታቸው ድጋፍ ደቡብ አፍሪካን በዓለም ዐቀፍ አሎምፒክ ኮሚቴ በኩል ከዓለም ዐቀፍ ስፓርት ውድድር እንድትታገድ ማድረግ ችለዋል።

በ1968 ሜክሲኮ ላይ በተዘጋጀው የኦሎምፒክ ውድድር የሜክሲኮ መንግሥት የዓለም ዐቀፉን የኦሎምፒክ ውሳኔ ጥሶ ደቡብ አፍሪካ በውድድሩ እንድታሳተፍ በወሰነ ጊዜ አቶ ይድነቃቸው ደቡብ አፍሪካ በሜክሲኮ አሎምፒክ የምትሳተፍ ከሆነ ኢትዮጵያ ከውድድሩ እንደምትወጣ ለጋዜጠኞች መግለጫ ሰጡ። የአቶ ይድነቃቸውን መግለጫ ተከትሎ ሌሎች አርባ አንድ አገሮችም የኢትዮጵያን አቋም እነደሚደግፉና ደቡብ አፍሪካ ተሳታፊ ከሆነች ከውድድሩ ራሳቸውን እንደሚያገሉ አስታወቁ። የግንባር ቀደሙ ተፋላሚ የአቶ ይድነቃቸው አቋም የድጋፍ ሃይሉ ስለበረታ ሜክሲኮ የደቡብ አፍሪካን በውድድሩ መጋበዝ ለመሰረዝ ተገዳለች።

አቶ ይድነቃቸው በህይወት ዘመናቸው ላበረከቱዋቸው ተግባራት ከኢትዮጵያ መንግሥትና ከተለያዩ ሀገራት መንግሥታት አያሌ ሽልማቶችንና ሜዳሊያዎችን አግኝተዋል።

ይድነቃቸው ተሰማ ኢትዮጵያ ካፈራቻቸውና አህጉሪቷንና ዓለምን በቅንነት፤ በፍፁም ታማኝነትና አርቆ አሳቢነት ካገለገሉ ልጆቿ መካከል የበኸር ልጇ ናቸው ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ሀገራዊ፤ አህጉራዊና ዓለም ዐቀፋዊ ተልዕኮ አንግበው ዕድሜያቸውን ሙሉ ያለመታከት የሰሩት አቶ ይድነቃቸው ተሰማ በተወለዱ 66 ዓመታቸው አገስት 19 1987 አረፉ።

አቶ ይድናቸው ቢያልፉም ህያው ሥራቸው ግን ከዘመን ዘመን እየተሻገረ በየትውልዱ ሁሉ የሚታወስና የሚነገር የአኩሪ ኢትዮጵያዊ አንፀባራቂ ታሪክ ሆኖ ይኖራል።

# ለፈገግታ .... [ከገጽ 33 የዞረ]

## በሰፈሩት ቁና......!

ጊዜው በ1960 ነው፡፡ ወሩ ታህሳስ ነበር የማዳጋስካር ቡድን ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ አበባ የመጣበት ወቅት ነው፡፡ ውድድሩ ለሜክሲኮ አሎምፒክ ማጣሪያ ነው፡፡ የመጀመሪያው ጨዋታ አንታናናሪቭ ላይ ተካሄደ፡፡ ማዳጋሰካር አሸነፈ፡፡ የመልሱን ጨዋታ ለማሸነፍ አዲስ አበባ ላይ ምን ይደረግ ? ተባለ፡፡ ማዳጋስካር ደረቅ ሜዳ ላይ እንጂ ጭቃ ላይ መጫወት አይችልም የሚል መረጃ ተገኘ፡፡ ወቅቱ ደግሞ ፀሐይ የጠነከረበት፤ ሜዳው የደረቀበት አዋራ የበዛበት ጊዜ ነበር፡፡ በሰው ሰራሽ ዘዴ ሜዳውን እናጨቅየው ተባለ፡፡ ውሃ ማመላለሻ ባልዲ ተፈለገ፡ በበቂ ሁኔታ አልተገኘም፡፡ የፌዴሬሽኑ የጥገና ሐላፊ አቶ ቪቼንሶ ዩሪያ «ለብሔራዊ ቡድኑ ዋጋ እንክፈል» በሚል የስፖርት ቤተሰቡን አሰባሰቡ፡፡ የተነገረውም ሰው ተስማማ፡፡ከየአካባቢው ባልዲ ይዞ ከተፍ አለ፤አላማው ሜዳውን አጨቅይቶ ማዳጋስካርን እጅ ለማሰጠት ነው ፤የተሰበሰበው ሰው ጉባኤ ጀመረ፤ ውሃው በስንት ሰዓት ይፍሰስ አለ፡፡ ጥዋት ከፈሰሰ ፀሐዩ ይመታውና ተመልሶ ይደርቃል ተባለ፡፡ ከምሳ በኃላ ይሁን በሚለው ተስማሙ፡፡ ማዳጋስካር ወደሜዳ ሳይመጣ ዳኛና ኮሚሽነሩ ሳያዩ ‹በዘመቻ ባልዲ› ስራው ተጀመረ፡፡ የዛሬ 40 አመት ውሃውን ካፈሰሱት ውስጥ አንዱ አቶ ደበበ እንግዳወርቅ እንዲህ ይላሉ « የፌዴሬሽኑን ሻይ ቤት ኮንትራት የያዘው አቶ ወልዴ ይባላል፡፡ እኔ ባልዲውን ያመጣሁት ከእሱ ቤት ነው፡፡ አቶ ቪቼንሶ ቶሎ በሉ እያሉ በባልዲ እያመላለስን ማፍሰስ ጀመርን፡፡ በተለይ በረኛው አካባቢና የእነሱ ጎበዝ የሚባለው ልጅ የሚጫወትበት ቦታ ትከሻችን እስኪላጥ ድረስ አፈሰስን፡፡ የጀመርነው 7 ሰዓት ነው አጨቅይተን ወደማብቂያችን ላይ ተመልካቹ እየገባ ነበር፡፡ በጎን ደግሞ ሰጋቱራ እናፈሳልን ምክንያቱም እንዳይታወቅብን ለዘዴ ነው፡፡ ያፈሰስነው ውሃ ለእኛ የሚመች ለእነሱ የሚያስቸግር አደረግነው፡፡ በእርግጥም ማዳጋስካር በጭቃ መጫወት አቃተው፡፡ ቡድናችንም አሸነፈ፡፡ ባልዲ ስራውን ሰራ፡፡ አንድ ቀን ግን ለእኛም መጥፎ ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ ሱዳን በጭቃ መጫወት ሐይለኛ ነው፡፡ ቡድናችን 1ለ0 እየመራ ከባድ ዝናብ ጣለ፡፡ ሜዳው ውሃ ሆነ አሰልጣኙ ሉቻኖ ነበር፡፡ እሱ ከእኛ ጋ ሆኖ ውሃውን ከሜዳው ጠርጎ ለማውጣት ብዙ ደከምን፡፡ ግን ውሃውን ማስወጣት አልቻልንም፡፡ ሱዳን በውሃ ላይ ጨዋታ ሐይለኛ ሆነ፡፡ ሁለት ጎል አስቆጥሮ በሜዳችን ላይ ነጥብ አስጥሎን ሄደ» ፡፡በሰፈሩት ቁና ይሆን?

————///————

# ......... ለማ ክብረት

ከገጽ 28 የዞረ

የኛ አራተኛው ተመታ፤ አገባን። እነሱ 5 ኛውን መቱ አሁንም አዳንኩ። ስለዚህ እኛ 5ኛ መምታት ሳያስፈልገን አሸነፍን፡፤ ከ5 ፍጹም ቅጣት ምት 4 አዳንኩ፡፤

__ኢ.ቶ__ ከዚያስ አጠፋፋችሁ ምን ይመስል ነበር፡፤

__ለማ__ አጠፋፋችን ደግሞ ባጋጣሚ እየተጫወትን ሳለ አንድ የኢትዮጵያን ባንዲራ የያዘ ሰው በሩቁ አይተን ስለነበር ኢትዮጵያዊ አገኘን ብለን ጨዋታው ሲያልቅ ወደሱ ሄድን። ለካ እሱ የዛው አገር ሰው ነው። ኢትዮጵያን የሚደግፍበት የራሱ ምክንያት ነበረው፡፤

ያም ሆነ ይህ ለመጥፋት ማሰባችንን ነገረነው ። ሆቴል መጥቶ እቃችንን ተቀብሎ ወሰደልን፡፤ እኛም ከሌሎቹ ተጫዋቾች ጋር ከተማ ስንወጣ የሆነ ቦታ ሰውየውን ቀጥረነው ከተጫዋቾች ተለይተን ወደ አሜሪካ ኤንባሲ ወሰደን፡፤ ከዚያ ወደ ዩ ኤን ተወሰድን ከ13 ወራት ቆይታ በኋላ ወደ አውስትራሊያ 1984 ሜይ ላይ መጣን።

__ኢ.ቶ__ ሞርሽስ ላይ የነበሩ የብሄራዊ ቡድናችን ተጫዋቾች እነማን ነበሩ።

**ለማ** ከኛ ወደ አውስትራሊያ ከመጣነው ከ 4ታችን ሌላ ክብሮም፤ ሙሉ ዓለም እጅጉ ፤ ዮሃንስ ሳህሌ፤ ንጉሴ ገብሬ፤ ሰሎሞን ጋሜ፤ ጸጋዬ ፋንታሁን፤ ታምራት ታደሰ፤ ተስፋ ሚካኤል እነኚህን ነው የማስታውሰው;

**ኢ.ቶ** እስኪ አሁን ደግሞ አቅጣጫ ልለውጥና ወደ አሜሪካው የፌዴሬሽኖች ውዝግብ ልውሰድህ። አምና ስለተፈጠረው ችግር ምን የምትለው አለ? እኛስ ምን እንማራለን?

**ለማ** በጣም የሚገርምህ አሜሪካ በተፈጠረው ችግር በጣም ነው ያዘንኩት። ችግር ፈጣሪዎቹ ደግሞ በጣም የቅርብ ጓደኞቼ ናቸው፡፤ ሁለቱ ደግሞ በጣም የሚቀርቡኝ ናቸውና በጣም ነው ያሳዘኑኝ። ነገር ግን ህዝብ የደገፈው ሁሌም ያሸንፋልና አንዲትም ጉድለት ሳይደርስ ችግሩ ተወገደ። እንዲያውም ህዝቡ እልህ ውስጥ ስለገባ ዳላስ ላይ በጣም በደመቀ ሁኔታ መከበሩን አይተሃል።

በተለይ በተለይ ጓደኞቼ እንደ ነገሩኝ ጋዜጠኛ አበበ በለው ትልቅ ሚና እንደተጫወተ ነው። ሚዲያ ቀላል አይደለም ሚናው፡፤ 29 አመት ለፍተው የገነቡትን ፌዴሬሽን ሁለት ሶስት ሆነው ለመውረስና ለማፍረስ መሮጣቸው በጣም የሚያሳዝንና የሚያሳፍር ነው።

እኛም መማር ያለብን ሁሌም ከኮሚኒቲውና ከህዝብ ጋር መሆን እንዳለብን ነው። ህዝብን የያዘ ምንም ነገር ቢሆን አይወድቅም።

በድጋሚ በጣም አመስግናለሁ ለማ

እኔም አመሰግናለሁ። ....////.......

# የሐዘን መግለጫ



## አቶ አለማየሁ እሸቴ
## ከ1951 –2005

አቶ አለማየሁ እሸቴ ከአባቱ ከአቶ እሸቴ ሃብተወልድ ከእናቱ ከወይዘሮ በላይነሽ ገብረ አምላክ በ1959ዓ.ም ተወለደ።የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በአዲስ አበባ ኮልፌ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ካጠናቀቀ በኋላ በመምህርነት ተሰማርቶ ወገኑን አገልግሏል። አቶ አለማየሁ ከሃገሩ በስደት እንደወጣ በካይሮ ለጥቂት ዓመታት ቆይቶ በ1995 ወደ አውስትራሊያ መጥቶ ህይወቱ በድንገት እስካለፈበት እስከ 8/12/12 በሜልበርን ነዋሪ ነበር።አቶ አለማየሁ የአንድ ልጅ አባት ነበር።

አቶ አለማየሁ ከሰው ተግባቢ፤ ቅን፤ ትንሽ ትልቁን አክባሪ፤ ትሁት ሰው ነበርና ድንገተኛ እልፈቱ በሜልበርን የምንገኝ ወገኖቹን አስደንግጧል ። ሃዘናችንም መሪር ሆኗል። በዚህ አጋጣሚ የወንድማችን ድንገተኛ ሞት አብዝቶ የጎዳችሁ ቤተሰብና ዘመዶቹ መጽናናትና ብርታቱን ይሰጣችሁ እንላለን።

አሌክስ ነፍስህን በቀኙ ያኑራት

በሜልበርን የምንገኝ ወገኖቹ

# R.I.P



ለ29ኛው አፍሪካ ዋንጫ ያለፈው የኢትዮጵያ ብሄራዊ እግር ኳስ ቡድን